ውዳሴ አምላክ

ቁጥር 2

1984

በጌጃ መሠረተ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
ሥነ ጽሁፍ ክፍል የተዘጋጀ

ስልክ 13 15 70
የ መ ሣ 6 9 8
አዲስ አበባ

ማ ው ጫ

	ገጽ
ሁሉን የምትገዛ	7
ሃሌ ሉ ሃሌሉያ	27
ላደረግህልኝ የምመልሰው	23
ልናርፍ ነው	139
ልገዛልህ ጌታዬ	81
ሕዝብህን አበዛህ	110
ሕዝቦች ሆይ ደስ ይበላችሁ	17
ሕይወት ያለ ጌታ	85
መልስ ነው	150
መልካም ሊቀኘህን	87
መራራ ኑሮዬን	84
መቃብሩን ፈነቃቀለው	135
መቼ ነው ነቅቼ	77
መንፈስ ቅዱስ	117
መከናወንን ሰጠኸን	13
ማለዳ ስነሣ	78
ማን እንዳንተ	37
ማየቱ ተስኖን	98
ምስጋና ለአዳኛችን	21
ምስጋና የሚገባውን	33
ምን ይከፈልሃል	19
ሞኝ ነው አልተማረም አሉኝ	70
ራሴን ልመልከተው	66
ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው	48
ሰምቶ የሚመልስ	79
ቀኑ ደርሷል	142
ቃላችንን እንደቃልህ	61
በምስጋና ሆሆ	2
በምስጋና ላይ ምስጋና	12
በረከትና ክብርም ጥበብም	144

ገጽ

በሮች ይከፈቱ	34
በኀዘኔ በጭንቀቴ	93
በኢየሱስ ነው ነጻነቴ	149
በእምነት እኖራለሁ	99
በእውነት አሳድገን	106
በኩርንትህን ለምን ሸጥከው	88
በድንቅ አጠራርህ	20
በጭንቁ ተጨንቆ	86
ብሩክ ይሁኑ	45
ብርቱ ነው	47
ተመስገን ጌታዬ	9
ተራራ ስወጣ ስበረታ	71
ተራራው ሸለቆው	65
ተስፋ ቁረጥ	50
ተነሥ ተነሥ	115
ተነሥቷል	136
ተነሥቷል ጌታ ተነሥቷል	133
ተጠፍሬ ያየኝ	11
ኅብረት አለን	108
ኃዘንተኛን ያጽናናው	96
ኃይልህን ቀምሼ	62
ነገር ሁሉ ባይሳካ	104
ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ	31
ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔር አምላክ ነውና	29
ኑሮ ያለ ጌታ	64
ናና ጌታችን	49
ና የጥንቱ ኢየሱስ	111
ና ፊት ፊታችን ውጣ	55
አለኝ ወዳጅ	141
አልረሳውም ጌታ	130
አመስግኑት	25

ገጽ

አመጣጡ የንጉሥ ዘር ነው 127
አማኑኤል 128
አሜን በሉ ስገዱለት 41
አሜን ኢየሱስ 28
አሜን ክበር 57
አምላኬ ያደረገውን ነገር 22
አቤቱ መባረክን ባርከን 80
አቤንኤዘር 101
አንድ ነገር በልቤ ሆነ 132
አዲስ ሰው ሆንኩኝ 90
አዲስ ዘመን 148
ኢየሱስ ለእኔ 100
ኢየሱስ የቀራንዮ ኢየሱስ 113
ኢረኛችን ይጠብቀናል 59
እሰይ እሰይ 124
እስከዛሬ የጠበከን 72
እስከ ዛሬ ድረስ 53
እስኪ ና ጌታ 73
እስኪ ዛሬ 67
እንደሎጥ እንደኖኅ ዘመን 83
እንደ ማርያም ልሁን 122
እንደ ቃልህ እንዳስተማርከን 121
እንዲያው መሮጡ 52
እንዳልተውህ እንዳልረሳህ 63
እንጓዝ የእግዚአብሔር ልጆች 145
እናመልከዋለን 43
እዚህ ነን 119
እጄን ይዞ መራኝ ጌታዬ 38
እግዚአብሔር ትልቅ ነው 16
እግዚአብሔር ነው ታዳጊያችን 58
እግዚአብሔር ይመስገን 30
እረኞች በድንገት 123
ከአምላካቸው በቀር 103
ከዚህም የሚበልጥ 118
ከጣሪያዬ በታች 82
ከፍ ከፍ በል 26

ክበር ክበር ብዬ 36
ክብሩ ይስፋ 14
ክብር ልዕልና 32
ክብር ለስሙ 3
ክብር ለዘለዓለም ይሁንልህ 15
ክብር ክብር 4
ክብር ይሁን ክብር 10
ከፋው የኃጢአት ቀንበሬን 91
ወደር የማይገኝልህ 42
ወደ እግዚአብሔር ቤት 112
ውለታው እጅግ ብዙ ነው 6
ውዴ ውዴ 8
ዓይኔን ከሰው አነሣቸለሁ 147
ዕድሜ ልኬን 68
ዙሪያችንን ስናይ 69
የር ብዬ ሳየው 102
ዘመ ስዋዕቱን በግ 94
የመከራን ቀንበር 60
የመጽናናት ዘመን 95
የሚቋቋምህ ማንም የለም 46
የምሥራች ቃል 125
የምስጋናን መሥዋዕት እንሰዋለን 35
የምድር ፍጥረታት 137
የሠራልኝን ድንቅ 54
የኃያላን ሁሉ ኃያል ነህ 40
የኤልያስ አምላክ ወዴት ነህ ? 74
የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ ተነሥ 120
የዘላለም አምላክ 44
የድል ዘንባባ 140
ነፍሴ የምትወድህ 89
ያንን ታላቅ ክብር 116
ያዲስ ኪዳን በግ 143
ይመለሳል 138
ይመስገን ጌታ 24
ይቅርታን ለማድረግ 146
ይኼ ሁሉ ሕዝብህ 109

ገጽ

ደሙ በመቃኑ ላይ ነው	18
ደሙ እንደ ውኃ	129
ደስ ደስ ይለኛል	5
ደግመህ ደግመህ ባርከን	114
ድምጽህ ይሰማኝ	75
ጌታ ባንተ ተማምኜ	97
ጌታ ነህ	39
ጌታን እናመስግን	1
ጌታ ያውቃል	92
አቤን ኤዘር እስከ ዛሬ ደረስ	151
ሠሸሸጊያሻ	152
እንደተቀበልከት ምህረት	153
ክብር ለኢየሱስ ይሁን	154
አንተ ትሻለኛለህ	155
ጋሻ ጦርህን አንሣ	56
ግሩም ድንቅ ነው	126
ግን አንድ ነገር አውቃለሁ	105
ጩኸቴን ስማ	70
ጽኑ ጦር	57
ፈነቀለው ጌታ	134
ፍቅሩ የማያቋርጥ ጅረት ነው	107
ፍቅር ይዞት	131

የመዝሙር ርዕስ

	ገጽ
የምስጋና	1—35
የውዳሴ	36—47
የውጊያና የድል	48—60
የክርስትና ሕይወት	61—72
የጸሎት	73—80
የንስሐ	81—84
የደኅንነት	85—88
የመለወጥ	89—91
የመጽናናት	92—96
የእምነት	97—101
የጽናት	102—104
የፍቅር	105—107
የእግዚአብሔር ሕዝብ	108—110
የእግዚአብሔር ጉባኤ	111—113
የእግዚአብሔር በረከት	114—120
ከእግዚአብሔር መማር	121—122
የልደት	123—128
የሕማማት	129—132
የትንሣኤ	133—136
የምጽአት	137—142
የዘላለም ተስፋ	143—145
ልዩ ልዩ	146—155

ጌታን እናመስግን

1 ጌታን እናመስግን በምስጋና
አሆሆሆ በምስጋና
ከሰይጣን መንጋጋ አድኖናልና
አሆሆሆ በምስጋና
ድል ይገኛልና።

2. ጌታን እናመስግን በዝማሬ
አሆሆሆ በዝማሬ
አድኖናልና ከጨካኙ አውሬ
አሆሆሆ በዝማሬ
የድል ቀን ነው ዛሬ ።

3. ጌታን እናመስግን በጭብጨባ
አሆሆሆ በጭብጨባ
አድኖናልና ከጨካኙ ሌባ
አሆሆሆ በጭብጨባ
ይመስገን አባባ ።

4. ጌታን እናመስግን በሽብሸባ
አሆሆሆ በሽብሸባ
የሚገዳደረን ወደ ጥልቁ ገባ
አሆሆሆ በሽብሸባ
ይመስገን አባባ ።

5. ጌታን እናመስግን በእልልታ
አሆሆሆ በእልልታ
ልጆቹ አድርጎናል የሠራዊት ጌታ
አሆሆሆ በእልልታ
ለሠራዊት ጌታ ።

በምስጋና ሆ ! ሆ !

1. ጨለማ ሲከብድ ምስጋና ምስጋና
ያበጀሁት ሲናድ ” ”
ኑሮ ቁልቁል ሲወርድ ምስጋና ምስጋና
እግዚአብሔር ከኔ ጋር ነውና ።

በምስጋና ሆ ሆ በምስጋና
በምስጋና ሆ ሆ ድል አለና
እግዚአብሔር ከኔ ጋር ነውና ። (4)

2. ዙሪያው ገደል ሲሆን ምስጋና ምስጋና
ልብን ጭንቅ ሲለው ” ”
ጠላት ደስ አይበለው ” ”
እግዚአብሔር ከኔ ጋር ነውና ።

በምስጋና . . .

3. ወዳጅ ከዓይን ሲርቅ ምስጋና ምስጋና
ለምለሙ ሲደርቅ ” ”
ከብትም ከጋጣ ሲያልቅ ” ”
እግዚአብሔር ከኔ ጋር ነውና ።

በምስጋና . . . .

4. ተስፋ ሲጨላልም ምስጋና ምስጋና
እምነትም ሲጠፋ ” ”
እግዚአብሔር ይመስገን ምስጋና ምስጋና
እግዚአብሔር ከኔ ጋር ነውና ።

በምስጋና . . .

ክብር ለስሙ

1. በመስቀል ሞቶ መድኃኒቴ
ሊያድነኝ ብሎ ከጥፋቱ
ሊመልሰኝም ከኃጢአቱ
ክብር ለስሙ ።

ክብር ለስሙ (2)
ነጻ ስላወጣኝ በደሙ
ክብር ለስሙ ።

2. በመስቀሉ ከኃጢአት ዳንሁኝ
እምላክም ልጁን ለወጠልኝ
ከኃጢአት አርነት ሊያወጣኝ
ክብር ለስሙ ።

ክብር ለስሙ . . .

3. አ ብሩክ ምንጭ ከኃጢአት ያዳነኝ
ያ ምንጭም አንጽቶ አጠበኝ
ያማልደኝ ዘንድ ተስፋ አለኝ
ክብር ለስሙ ።

ክብር ለስሙ . . .

4. ያ ምንጭም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው
ለኃጢአታችን ሲል የሞተው
በሶስተኛው ቀን የተነሳው
ክብር ለስሙ ።

ክብር ለስሙ . . .

ክብር ክብር

ክብር ክብር ክብር (2)
ጌታ ላንተ ይሁን
በሰማይ በምድር

1. መካኒቱን በልጅ የባረካት
ደስ የተሰኘች ሴት ያደረካት
ምስኪኑን ከአመድ ያነሳኸው
ለሹመት ሽልማት ያበቃኸው
ክብር ላንተ ይሁን ።

ክብር ክብር . . .

2. ባሕሩን ለሁለት የከፈልከው
ሾላውን ከሥሩ የነቀልከው
ለደካማው ኃይል የሰጠኸው
በከፍታዎች ላይ ያራመድከው
ክብር ላንተ ይሁን

ክብር ክብር . . .

3 ዘንዶውን የወጋህ የቆራረጥከ
ጠንካራውን አለት የሰነጠከ
የተራበችውን ነፍስ ያጠገብከ
የተበተኑትን የሰበሰብከ
ክብር ላንተ ይሁን ፤

ክብር ክብር . . .

4 የእስረኞቹን ጩኸት አዳምጠሃል
የወኅኒውን መዝጊያ ሰባብረሃል
ሰው የረሳቸውን አስታውሰሃል
የአልጋ ቁራኞችን ፈውሰሃል
ክብር ላንተ ይሁን ።

ክብር ክብር . . .

ደስ ደስ ይለኛል

1. በጌታ ጥላ ውስጥ በክንፉ አድሬ
የእርሱን ድንቅ ሥራ አውርቼ መስክሬ
ልጨርስ ልፈጽም አቅቶኛልና
እንዲያው በዝማሬ እላለሁ ምሥጋና ።

ደስ ደስ ይለኛል እግዚአብሔርን ስጠራ (2)
በምስጋና ሆኜ ከልቤ
ፍቅሩን ምሕረቱን አስቤ ።

2. ምንም አላደረኩ ምንም አልሰጠሁት
አምላኬ ነው ብዬ ዋጋም አልከፈልኩት
እንዲያው በጸጋው ኃይል ጠብቆኛልና
ለዚህ ፍቅር ጌታ ይድረሰው ምስጋና ። (2)

ደስ ደስ ይለኛል . .

3. ተስፋ እየቆረጥኩ ስወድቅ ስነሣ
ሸለቆ ገብቼ ውለታውን ስረሣ
ጌታ ይባርከኛል በጸጋው እንደገና
ሕያው አምላኬ ነው ልቅረብ በምስጋና ። (2)

ደስ ደስ ይለኛል . . .

4. ምስጋና ሲያንሰው ነው ዝማሬውም ጭምር
በምስኪኑ ልጅ ውስጥ እንደዚህ ሲከብር
ታዲያ ምን ልክፈለው ለዚህ መድኃኒቴ
ዝማሬዬን ውሰድ ከዚች አንደበቴ ። (2)

ደስ ደስ ይለኛል . . .

ውለታው እጅግ ብዙ ነው

ውለታው እጅግ ብዙ ነው
አልችልም በቃል ልገልጸው
ተመስገን ብቻ ልበለው ፡፡

1. ከቀራንዮ ሞቱ ጀምሮ
እኔን እስከ ሞት አፍቅሮ
ነፍሴን በነፍሱ ለውጦ
ደሙን ከእንባው ቀይጦ
እኔን ሊያበለጽግ ደህይቶ
ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ
ንጹህ የደም ላብ ያላበው
ይህ ሁሉ ድካም ለኔ ነው ፡፡

ውለታው እጅግ ብዙ ነው . . .

2. ይከሰኝ የነበረ ባለፈው
ጠላት በግንባሬ የጻፈው
የዕዳን ጽሕፈት ደምስሶ
ጭንቀቴን አጥቦ አድሶ
ሰው አደረገኝ ረድኤቴ
ሰላሙን ሞላ በቤቴ
የከሳሼም ግንባር ተመታ
እኔም እዘምራለሁ በደስታ ፡፡

ውለታው እጅግ ብዙ ነው . . .

3. ድካሜ ብዙ ነው ጉድለቴ
በጸጋ ነው አለሁ ማለቴ
በድፍረት ስሙን መጥራቴ
ጌታ የሠራውን ማውራቴ
ሰው ሆኜ በምድር መኖሬ
በሰላም ወቶ ማደሬ
እግሬም ጸንቶ ሊቆም የቻለው
ይህ ሁሉ በእርሱ ጸጋ ነው ፡፡

ውለታው እጅግ ብዙ ነው . . .

ሁሉን የምትገዛ

ሁሉን የምትገዛ ያለህ የነበርህ
ትልቁን ኃይልህን ለብሰህ የከበርህ
ስምህ ለዘለዓለም ይመስገን ይባረክ
ጉልበት ሁሉ ላንተ ጌታ ሆይ ይንበርከክ ።

1. የጽድቅ ሥራህን ጌታ ሠራህና
በጨለማ ላሉ ፀሐይ ወጣችና
ከዘለዓለም ጥፋት አንተ ያዳንካቸው
በታዳጊነትህ እጅግ ደስ አላቸው ። (2)

ሁሉን የምትገዛ . . .

2. የመስቀል ፍቅርህን ለሰው ይነግራሉ
የቅድስናህን ክብር ያወራሉ
በክንፎችህ ጥላ ታምነው ይኖራሉ
የማዳን ክንድህን ሁልጊዜ ያያሉ ። (2)

ሁሉን የምትገዛ . . .

3. ከስም ሁሉ በላይ ስምህ የከበረ
ከሰው ልጆች ይልቅ ውበትህ ያማረ
የሚመስልህ የለም እጅግ ልዩ ነህ
ከፍ ብለህ ንገሥ ግርማን ተሞልተህ ። (2)

ሁሉን የምትገዛ . . .

4. ክብርህ በምድር ሁሉ ይታይ አምላካችን
ምላስም ይመስክር ታላቅነትህን
በሰማይ በምድር ትሰለጥናለህ
ሁሉን ከእግርህ በታች አንተ ትገዛለህ ። (2)

ሁሉን የምትገዛ . . .

ውዴ ውዴ

1. ግርም ግርም አለኝ
ድንቅ ድንቅ አለኝ
ጌታን ሳስበው ደስ አለኝ
ፍቅሩን ጥልቀቱን መመዘን አቃተኝ ።

ውዴ ውዴ ውዴ
ፍቅርህን ሳስበው ተንበረከኩ እኔ
ውለታህን ሳስበው ተንበረከኩ እኔ
ጥበቃህን ” ” ”
ጸጋህን ” ” ”
ሁሉንም ትቼ ተመስገን ልበልህ ወገኔ ።

2. እንባን አፈሰስኩኝ
አሳቤን ሞላሁኝ
የጌታ ፍቅር ደስ አለኝ
እረ አውጥቼ መናገር አቃተኝ ።

ውዴ ውዴ . . .

3. ጌታ ጌታ አልኩት
ውዴ ውዴ አረግሁት
ኢየሱስ ኢየሱሴ ነህ አልኩት
ከዚህ በላይ መስጠት ስላልቻልኩ ።

ውዴ ውዴ . . .

4. ራሴን ነቀነቅሁኝ
ፍቅሩ አስገደደኝ
ኢየሱስ ፍጹም ተለየብኝ
በመጨረሻ ሕይወቴን ሰጠሁኝ ።

ውዴ ውዴ . . .

ተመስገን ጌታዬ

1. ማን ለኔ አስቦ እንዳንተ ተጨንቆ
ማን ከጭቃ አነሣኝ በመውደቄ ወድቆ
ኑሮዬን ማን መራ በችግሬ ገብቶ
ማን ከቶ አዘነልኝ መሳለቄን ትቶ ።

ተመስገን ጌታዬ መቆም ባንተ ቻልኩኝ
ባንዴ በመንበርከክ በእንባ ተጠገንኩኝ ።

2. ማን ደክሜ ረዳኝ በከንቱ ስለፋ
ወደ ሞት ሳዘግም አጥፍቼ ልጠፋ
ማን ገባው እንባዬ ከቶ ካንተ ሌላ
ማንስ ጋሻ ሆነኝ ለኑሮዬ ጥላ ።

ተመስገን ጌታዬ . . .

3. ማነው የታገሰኝ ባጠፋም ባለማ
ማን ከቶ አጠጣኝ ፍቅርህን ስጠማ
ማን ሀብቴ ሆነልኝ በድህነቴ ገብቶ
በፈጠረው ፍጥረት በሰዎች ተጠልቶ ።

ተመስገን ጌታዬ . . .

4. ማነው አጽናኝዬ በከንቱ ስለፋ
ማነው መካሪዬ አውቄ ሳጠፋ
ማን ቻለኝ እንዳንተ ሳይፈርድ በሕይወቴ
የሆነ ምርኩዜ ኑሮዬና ቤቴ ።

ተመስገን ጌታዬ . . .

ክብር ይሁን ክብር

ክብር ይሁን ክብር (2)
በላይ በሰማይ ዙፋኑ ላይ
በታች በምድር ለእግዚአብሔር
ክብር ይሁን ክብር (4)

1. ኃጢአተኛውን አስበኸዋል
በደምህ አጥበህ አንጽተኸዋል
ከጻድቃን ማኅበር ቀላቅለኸዋል
ከሳሹ ጠላት ዲያቢሎስ አፍሮአል
ለዚህ ለሥራ ምን ይከፈላል ።

ክብር ይሁን . . .

2. በጠላት ቀስሎ የደከመውን
ሸለቆ ወድቆ ያለቀሰውን
ዛሬ በደስታ ሲዘምር በቅቷል
አንተ ድንቅ ነህ ምን ይሳንሃል
ጌታዬ ላንተ ክብር ይገባሃል ።

ክብር ይሁን . . .

3. ደረቁን ምድር አረሰርስሃል
የተራቆተውን አንተ አልብሰሃል
በታሪክ ማኅደር ያልታወቀውን
አንተ አስጠግተህ አገነንክ ስሙን
ጌታዬ ክብሩ ለአንተ ይሁን ።

ክብር ይሁን . . .

4. ዙፋንህ ከጥንት የዘለዓለም
ብርቱ ተዋጊ እንዳንተ የለም
የጠላት ምክርን አፍርሰኸዋል
በአንድ ላይ መጥተው ተበትነዋል
ጌታዬ ላንተ ክብር ይገባሃል ።

ክብር ይሁን . . .

ተጠፍሬ ያየኝ

1. በጉልበቴ ያለሁ ገና ያልተነካሁኝ
በመንገድ አጠገብ በውጭ የታሰርኩኝ
ነጻነት የሌለኝ ውርንጫ ነበርኩኝ
ሳላውቅህ አውቀኸኝ አንተ ግን ፈታኸኝ ።

ተጠፍሬ ያየኝ ያለውዴታዬ
ነጻነት የሰጠኝ ወዳጅ አለኝታዬ
ማነው ካንተ በቀር ባለውለታዬ
ሌላ ምን እላለሁ ተመስገን ጌታዬ ።(2)

2. በዚህ በጉልበቴ ላንተ ክብር ሮጠው
እባብና ጊንጡን በስምህ ረግጠው
መሸለሜን ሰምቶ ጠላት አኮረፈ
አንተን በላዬ ሲያይ ጥላው ተገፈፈ ።

ተጠፍሬ ያየኝ . . .

3. ከእስራት ፈተኸኝ በእኔ ልትቀመጥ
ይህን ታላቅ ዕድል ለምስኪኑ ልትሰጥ
ለመሆኑ እኔ እረ እኔ ማነኝ
ይገባኛል እንዴ ለዚህ ልትመርጠኝ ?

ተጠፍሬ ያየኝ . . .

4. ሆሳዕና በአርያም እያሉ ቢጮኹ
ልብሳቸውንና ቅጠል ቢያነጥፉ
የእኔ እግር ቢረግጠው አንተ በላዬ ነህ
ክብሩ የራስህ ነው ኑር ዘለዓለም ክብረህ ።

ውርንጫው ተፈትቶ የክብር ዕቃ ሆኗል
ነጻነትን ሰጥቶት ጌታው ከብሮበታል
የተፈታውን ተውት የፈታውን አክብሩ
ሆሳዕና በሉ መንገሡንም አውሩ ። (2)

በምስጋና ላይ ምስጋና

በምስጋና ላይ ምስጋና
በምስጋና ላይ ምስጋና
ይገባሃልና ።

1. በከብቶች በረት ምስጋና አድረሃልና ምስጋና
እስከ መስቀል ሞት ምስጋና ታዘሃልና ምስጋና
ለኔ ያደረግከው ምስጋና ብዙ ነውና ምስጋና
ለስምህ ምስጋና ።

በምስጋና ላይ . . .

2. አምላክ ስትሆን ምስጋና ታስረሃልና ምስጋና
የፈጠርከው እጅ ምስጋና ገርፎሃልና ምስጋና
ይህ ሁሉ ውርደት ምስጋና ለኔ ነውና ምስጋና
ለስምህ ምስጋና ።

በምስጋና ላይ . . .

3. ሁሉ እያለህ ምስጋና ተንከራተሃል ምስጋና
በቁር በሐሩር ምስጋና ወጥተህ ወርደሃል ምስጋና
ይህ ለኔ እንዲሆን ምስጋና ጌታ ገብቶኛል ምስጋና
ክብር ይገባሃል ።

በምስጋና ላይ . . .

4. በምድር እምብርት ምስጋና ሶስት ቀን አድረሃል ምስጋና
እስከ ሲኦልም ምስጋና ወርደህ ዘምተሃል ምስጋና
በዚህ ሁሉ ላይ ምስጋና ድልን ነሥተሃል ምስጋና
ክብር ይገባሃል ።

በምስጋና ላይ ምስጋና . . .

መከናወንን ሰጠኸን

መከናወንን ሰጠኸን ጌታ መከናወንን
አንተ በሥራችን ባርከኸን እጅግ ደስ አለን
ተመስገን ጌታ ተመስገን ተመስገን ኢየሱስ
የቤትህ ሥራ ተሠርቶአል ስምህም ከብሯል ።

1. ዘራችን ይዘን በልቅሶ ወጣን
በጋና ክረምት አንተን ተስፋ አርገን
ዛሬ አሽቶ ለዓይን ያማረውን
መልካሙን ፍሬ በደስታ በላን አንተ ባረከኸን ።

መከናወንን . . .

2. በዐለት በድንጋይ የመሠረትካት
ቅድስት ንጽህት አርገህ ያበጀሃት
ቤተ ክርስቲያንህ ዛሬም በርትታ
የገሀነም ደጅ ከቶ አልቻሉአትም አለች ተፈርታ ።

መከናወንን . . .

3. የተኩላው ብዛት የነጣቂ አውሬ
ከቤትህ ወጥተው የታሉ ዛሬ
ሥራችን በአንተ ተሠርቶ አይተን
ታየን በቤትህ ሕዝብህ ተባርከን በቁጥር በዝተን ።

መከናወንን . . . .

4. ጻድቅ በእምነት እንዲኖር አውቀን
በእምነት ወጣን ጥቂቱን ይዘን
ሁሉቱን ዓሣ አምስት እንጀራ
ለብዙ ባርከህ አንተ አጠገብከን ጌታ ተመስገን ።

መከናወንን . . .

ክብሩ ይስፋ

1. የማልወጣው ይመስለኝና
እምነቴም ፍጹም ይከዳኝና
ደንግጬ ሳለሁ በሥጋ ስፈርስ
አይዞህ ይለኛል ኢየሱስ ።

ክብሩ ይስፋ ለመድኃኒዓለም (3)
ክብሩ ይስፋ ።

2. የታል እግዚአብሔር ብዬ ስናገር
ማየት ሲሳነኝ ዓይኔ ሲታወር
ብርሃን ሆኖ ሁሉን ሊያሳየኝ
ኢየሱስ ብቅ ሲል ይኸው ታየኝ ።

ክብሩ ይስፋ . . . .

3. ያለፈ ውለታው ድጋፍም ሁሉ
ይዘነጋኝና ያብርታት ኃይሉ
መፍገምገም ይዞኝ ምላሴ ሲያዝ
ኢየሱስ ብቅ አለ እኔን ሊያግዝ ።

ክብሩ ይስፋ . . . .

4. ፍቅሩ የሚጣፍጥ ልዩ ነውና
ትእግሥቱም ፍጹም አያልቅምና
እቻ የሚሆነው የለውምና
ለኢየሱስ ይሁን ምስጋና ።

ክብሩ ይስፋ . . .

ክብር ለዘለዓለም ይሁንልህ

ክብር ለዘለዓለም ይሁንልህ
ምስጋናን እንሠዋ እንሰገድልህ
አንተ ታላቅ እግዚአብሔር ነህ (4)

1. በኃይልህና በችሎታህ ብርታት
አንዳች አይታጣ ሁሉን ትረታለህ
የብርቱዎች ብርቱ አንተ አትደክምም
ማስተዋልህ ፍጹም አይመረመርም ።

ክብር ለዘለዓለም . . .

2. በምድር ክበብ ላይ ትቀመጣለህ
ሁሉን በሥልጣንህ ትገዛለህ
የዘለዓለም አምላክ የፍጥረታት ሠሪ
ሁሉም ሲጠወልግ ለዘለዓለም ኗሪ ።

ክብር ለዘለዓለም . . .

3. እጅግ ታላቅ ሳለህ እኛን ወደኸናል
ከሞት ባርነትም ነጻ አውጥተኸናል
ክበር አምላካችን እናከብርሃለን
ምስጋና ምስጋና ይሁን እንላለን ።

ክብር ለዘለዓለም . . .

4. ጌታው በርሱ የኖረ የተገዛለት
እርሱም የወደደው ልቡ ያረፈበት
ምንኛ ታድሏል የረካ ልብ አለው
በዘለዓለም አምላክ ይኖራል በጥላው ።

ክብር ለዘለዓለም . . .

እግዚአብሔር ትልቅ ነው

እግዚአብሔር ትልቅ ነው
ምስጋናውም ብዙ ብዙ ነው
ሥራው ግሩምና ድንቅ ነው ። (4)

1. ከፍታው ዝቅታው ስፋቱ ጥልቀቱ
ኃይሉና ችሎታው ጥበብና እውቀቱ
ለገምት ያቅታል ከአዕምሮ በላይ ነው
ምህረትና ፍቅሩ ወሰን የሌለው ነው ።

እግዚአብሔር ትልቅ ነው . . .

2. ሰማይና ምድርን ሲፈጥር አማካሪ
አላስፈለገውም ረዳትና መሪ
ሁሉን በሥርዓቱ ፍጥረትን በእውቀቱ
ያኖረ እግዚአብሔር እርሱ ብቻ ብርቱ ።

እግዚአብሔር ትልቅ ነው . . .

3. ምስኪኑን ከጉድፍ ድሃውን ከፋንድያ
ከፍ ከፍ ያደርጋል አቅፎ በርሱ ጉያ
የተዘጋውን በር ከፍቶ ያስገባዋል
ጌታ በሥልጣኑ በክብር ያነግሠዋል ።

እግዚአብሔር ትልቅ ነው . . .

4. ሰላምን አድርጓል በወሰናችን
ከስንዴው ስብ በልተን በምህረቱ ጠግበን
በለመለመው መስክ ዋልን ተሰማርተን
ነፍሳችን እረካች ከምንጩ ጠጥተን ።

እግዚአብሔር ትልቅ ነው . . .

5. ቅዱሳን ሁላችሁ ጌታን አመስግኑ
ለክብሩ እልልታን ዝማሬን አሰሙ
የደጆቻችንን መወርወሪያ አጽንቷል
የእጃችን ፍሬ በእርሱ ተባርኳል ።

እግዚአብሔር ትልቅ ነው . . .

ሕዝቦች ሆይ ደስ ይበላችሁ

1. ሕዝቦች ሆይ ደስ ይበላችሁ
አምላክን አመስግኑ
የቆማችሁ በኪዳኑ በአንድነት ቅረቡ ፤

ቅረቡ በእልልታ ዘምሩ ለቸር ጌታ
ቅረቡ በእልልታ ዘምሩ ለቸር ጌታ ።

2. እርሱ ነው የፈጠረን ልጆቹን የጠራን
የጠፉትንም ያዳነ
እስካሁን ያቆመን ።

እርሱ በሰማይ ደስታ አደራጅልን ስፍራ
እርሱ በሰማይ ደስታ አደራጅልን ስፍራ ።

3. ዘምሩለት በበሮቹ
ወድሱት በመቅደሱ
ካገር ሁሉ ተከማቹ
ላባታችን ስገዱ ።

ርኅሩኅ ሆኖ ይጸናል እስከ ሞት ይመራናል
ርኅሩኅ ሆኖ ይጸናል እስከ ሞት ይመራናል ።

ደሙ በመቃኑ ላይ ነው

1. ደሙ በመቃኑ ላይ ነው (2)
የሞት መላእክ እያስፈራኝም
ተሸፍኛለሁ አያገኘኝም ፤
ጠላት ሲንጫጫ በሩቅ እያለሁ
ክብር ለበጉ እደሰታለሁ
አሜን እኔ ድኛለሁ ፥ሆ !

የታረደው በግ ኃይልና
ባለ ጠግነት ጥበብም
ብርታትም ክብር ምስጋናም
በረከትም ሊቀበል ይገባዋል ።

2. ደሙ በጉበኑ ላይ ነው (2)
ይህንን አርማ ማነው የሚጥስ
ከደሙ ምሽግ ከጫፉ የሚደርስ ፤
ለጠላት ለቅሶ የሞት ዕለት ነው
ለኔ የደስታ የመዳን ቀን ነው
አሜን አሜን እላለሁ ፥ሆ!

የታረደው በግ . . .

3. ክብር ክብር ለበጉ ይሁን (2)
ታርዶአልና እኔን ሊዋጀኝ
ከሞት ባርነት ነጻ ሊያወጣኝ ፤
ከበደል ከዓመጽ እስራት ፈቶ
ይኸው አዳነኝ ደሙን ረጭቶ
አሜን ጠላቴን ረትቶ ሆ!

የታረደው በግ . . .

4 ክብር ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን (2)
በውጪ ሳለሁ በጣም ርቄ
በሰው በመላእክት እጅግ ተንቄ
ዛሬ ግርዶሹ ተቀደደልኝ
ይኸው በኢየሱስ ተከፈተልኝ
አሜን መግባት ሆነልኝ ሆ!

የታረደው በግ . . .

ምን ይከፈልሃል

ምን ይከፈልሃል ጌታ ሆይ ምን ይከፈልሃል
ብቻ ተመስገን እንልሃለን ምስጋና ይገባሃል ።

1. ፈቃድህ ሆኖ እዚህ ደርሰናል
ከጠላትም እጅ ታድገኸናል
ዙሪያችን ከበህ አንተ ጠብቅኸን
ጠላት አፈረ እኛም አልጠፋን ።

ምን ይከፈልሃል . . .

2. ጠላት አደባ እኛን ሊያጠፉ
አንተም ተነሣህ የልጆችህ ተስፋ
ስምህን ጠርተን ጌታ አላፈርንም
ጠላት ሊያጠፉን ፍጹም አልቻለም ።

ምን ይከፈልሃል . . .

3. የጠላት ዛቻ ከንቱ ፉከራው
ልባችንን ጌታ ሲያናውጠው
ፍርሃት ከቦን ስናመነታ
ጽኑ ልጆቼ የምትለን ጌታ ።

ምን ይከፈልሃል . . .

4. ጠፉ ስንባል እንበዛለን
አንተ ስለሆንክ ጠባቂያችን
ስለውለታህ ምን ይከፈልሃል
ተመስገን ብቻ ክብር ይገባሃል ።

ምን ይከፈልሃል . . .

በድንቅ አጠራር የጠራኸኝ

በድንቅ አጠራርህ የጠራኸኝ
በእረፍት ውኃ ዘንድ የመራኸኝ
በለመለመ መስክ ያሳደርከኝ
በዓለት ንቃቃት የሰወርከኝ ፣
ተግተህ የጠበከኝ እንዳልጠፋ
መድኃኒዓለም ክብርህ ይስፋ ።

1. በግብጻውያን በደል በዓመጻቸው
ቁጣህ ከላይ ወርዶ ሲፈጃቸው
ደምህ ተቀብቶ በመቃኔ
ምክንያት ሆናልኛል ለመዳኔ
ተጠንቀክልኝ እንዳልጠፋ
ዙፋንህ ከፍ ይበል ይንሰራፋ ።

በድንቅ አጠራርህ . . .

2. በኮሬብ ተራራ በእሳት አምሳል
ለነብዩ ሙሴ ተገልጸሃል
በእኔም ልብ እንድደህ የፍቅር እሳት
ምስኪኗን ሕይወቴን ስታጋያት
አይቻለሁና እንዳቅሜ
አመሰግንሃለሁ ይኸው ቆሜ ።

በድንቅ አጠራርህ . . .

3. ከኃጢአቴ በቀር ከመርከሴ
የማውቀው የለኝም ስለ ራሴ
አንተን ግን አውቃለሁ ስታድነኝ
የድሃ አደግ አባት ስትሆነኝ
በፍቅር ይዘኸኛል በውዴታ
እኔም ላመስግንህ በእልልታ ።

በድንቅ አጠራርህ . . .

4. ኢጋጣሚ አይደለም ያገናኘን
እንደ አባትና ልጅ ያቆራኘን
ስለኔ ያሰብከው ያኔ ዱሮ
ዛሬ ተፈጸመ ዘመን ቆጥሮ
ያረከህ እንደሆን ይኸው መልሴ
ምስጋናና ክብር ከውዳሴ

በድንቅ አጠራርህ . . .

ምስጋና ለአዳኛችን

ምስጋና ለአዳኛችን ምስጋና ለተቤዥን ምስጋና (አሜን)
ምስጋና ዛሬም ነገም ገናና ለሆነው ኢየሱስ ነውና ።

1. ጌታችንን እናክብር በአንድነት
ለሠራው ድንቅ ኑ እንስገድለት
እናመስግን በአፋችን ዝማሬ
የምስጋና የድል ቀን ነው ዛሬ ።

ምስጋና ለአዳኛችን . . .

2. ጌታ ይክበር በቃው ጠላታችን
በኢየሱስ ወድቋል ከሥራችን
በምስጋና የከበረ ዜማ
በሰማያት ሰማያት ይሰማ ።

ምስጋና ለአዳኛችን . . .

3. በአዲስ ቅኔ አመስግኑት ጌታን
እጅግ ብዙ ብዙ ነው ችሎታው
እ የኢየሱስ ክብር ሁሉ ገነነ
ጠላታችን ሥራው ተደፈነ ።

ምስጋና ለአዳኛችን . . .

4. የዘለዓለም ባለውለታ ነው
ከሠይጣን ኃይል ያዳነን ጌታ ነው
በእልልታ እንዘምር በደስታ
አለኝታችን ክብራችን ነው ጌታ ።

ምስጋና ለአዳኛችን . . .

አምላኬ ያደረገውን ነገር

አምላኬ ያደረገውን ነገር ሁሉ ባወራው
ባወራው ፣ ባወራው ፣ ባወራው
ከቁጥር ሁሉ በዛ ታምራቱ ብዙ ነው ባወራው ።

1. ኃጢአተኛ ከፍ ከፍ ብሎ አይቼ
እንደ ሊባኖስ ዛፍ ለምልሞ ፈርቼ
ተመልሼ ከቦታው ፈለግሁት
እንኳን እርሱን ስፍራውን አጣሁት ።

አምላኬ ያደረገውን . . .

2. የክፉ ኃይል በቁጣ ዓይኖቹ እያየኝ
ጥርሱን በላዬ ላይ ሲያንገጫግጭብኝ
እግዚአብሔር ግን አይቶ ስቆበታል
የመጥፊያው ቀን እንደደረሰ አውቆአል ።

አምላኬ ያደረገውን . . .

3. ከመቅደሱ ከሰማይ ከፍታ ላይ ሆኖዋል
ወደ ምድር በታች አሽቆልቁሎ አይቶአል
የእስረኞችን የጩኸት ቃል ሰምቷል
ከሞት አፋፍ ከፍርድ ወጥመድ ፈቷል ።

አምላኬ ያደረገውን . . .

4. ከሰይጣን ኃይል የዳንሁ ወገን ሁሉ ከሰይፍ
ለሚመጣው ትውልድ ጻፍና አስተላልፍ
አምላካችን ይህን ተአምር ሠርቷል
እኔም ባወራው ባወራው በዝቷል ።

አምላኬ ያደረገውን . . .

ላደረግህልኝ የምመልሰው

ላደረግህልኝ የምመልሰው
እንዳች የለኝም እጂም ባዶ ነው
እንካ ተቀበል የአፌን ምስጋና (2)
በእጇ ያለው ይኸው ነውና ።

1. እንደበት የለኝ ስምህን ልጠራ
ምላስም የለኝ ሥራህን ላወራ
ልናገርም ብል ጊዜው አይበቃ
ተመስገን ብዬ ባጭሩ ላብቃ ። (2)

ላደረግህልኝ . . .

2. በፍቅር ቃልህ ልቤን ስትመታ
ነፍስ ሥጋዬን ከእሥር ልትፈታ
ምን አለኝና ምንን ልከፍልህ
ከተቀበልከኝ ክበር ልበልህ ። (2)

ላደረግህልኝ . . .

3. ከትቢያ አንስተህ ሰው ስታደርገኝ
በነፍስ በሥጋ ስትባርከኝ
ሰማያዊ ፍቅርህ ልቤን ሲሞላ
ተመስገን እንጂ የለኝም ሌላ ። (2)

ላደረግህልኝ የምመልሰው . . .

ይመስገን

ይመስገን ጌታ ይመስገን
ይመስገን ኢየሱስ ይመስገን
ይመስገን ይመስገን ይመስገን ይመስገን
ለዚህ ሁሉ ላደረሰን ።

1. እንደ ሰው ፈቃድ ቢሆን
እስከ ዛሬም ባልኖርን
ግን ኢየሱስ ፈቀደና
በድል ቆምን እንደገና ። (2)

ይመስገን . . .

2. ጠላት መች ይህን ወዶ
አቃተው እንጂ ተዋርዶ
ድሉ የአምላክ ሆኖበት
ያለቅሳል በኛ መነሣት ። (2)

ይመስገን . . .

3. ሞትም ቢገጥመን እኛ
ትንግኤ አለን ዳግመኛ
ከእርሱ ፍቅር ሊለየን
ማንም አይችልም ሊያስቀረን ። (2)

ይመስገን . . .

አመስግኑት

1. መች እንዲህ ያልቃል ተነግሮ
የፍቅሩ ሥራ ተሰምቶ
በሰው አንደበት ተነግሮ
ቃላት የለውም መግለጫ
ለፍጥረት ሁሉ ማሰሚያ
የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ።

አመስግኑት አመስግኑት (2)
ከጠላት መሸሸጊያ ለእኛ ያለን እርሱ ብቻ
ስንቱ የታደገንም ከጠላት ዛቻ
ወደር የለውም የሚሆነው እቻ ።

2. ሁሉን የሚችል አምላክ ነው
ወጀብን ጸጥ የሚያደርገው
ሥራው ድንቅ ኃያል ጌታ ነው
ሁሉን በትዕግሥት ይዞ
የጠላትን ኃይል አፍዝዞ
ይመራናል በድል ጉዞ ።

አመስግኑት . . .

3. ስውር ጥበብን ይገልጣል
ኃጢአትን ሁሉ ይጠላል
ቅኖችን ብቻ ይወዳል ።
ሥራውን በቃላት ገልጸን
እንጨርሰውም ተናግረን
የእግዚአብሔርን አሠራርን ።

አመስግኑት . . .

ከፍ ከፍ በል

ከፍ ከፍ ከፍ ከፍ በል ኢየሱስ ከፍ በል
ከፍ ከፍ ከፍ ከፍ በል ጌታችን ከፍ በል

1. ብንወጣና ብንወርድም አናገኝም ለኛ
እንዳንተ ያለ አመል ያለው የሕይወት ጓደኛ
ስለዚህ እንቀርባለን በፊትህ እንደገና
አሁንም አሁንም ይድረስህ ምስጋና ።

ከፍ ከፍ . . . .

2. በገናችንም ይነሣ ቅኔውም ይደርደር
ከበሮው ይመታ ይሁን ላንተ ክብር
በእንቢልታ በእልልታ ክበር የሱስ ጌታ
ሕዝብህን የምትታደግ የእኛ አለኝታ ።

ከፍ ከፍ . . .

3. ሐሩሩንም ተወጣነው ምድረ በዳውን አለፍን
ጠላታችንን ድል ነሣን በአንተ ተደግፈን
እንደበታችን ለአንተ ምስጋና ያወጣል
ተመስገን ከፍ በል ጌታችን ይልሃል ።

ከፍ ከፍ . . .

ሃሌሉ ሃሌሉያ

1. ተመስገን ጌታ ሆይ ተመስገን
አንተ አዳኝ ፈዋሽ ነህና
ይገባሃል ክብር ምስጋና
ምሕረትህ ለዘለዓለም ነውና
ክብር ላንተ ይሁን ምስጋና
የሕይወት በር ነህና ።

ሃሌሉ ሃሌሉያ . . . (4)

2. ፍጥረት ሁሉ ላንተ ይታዘዛል
እውነተኛ ነህ ጻድቅ ኃያል
ልትመሰገን ይገባሃል
ሰማያት ምድርም ሁሉ ያንተ ነው
ግዑዙ ሆነ ሕይወት ያለው
የእጅህ ሥራ ግሩም ድንቅ ነው ።

ሃሌሉ . . .

3. ስፍራና ጊዜያት አይወስኑህም
ጥበብህ አይመረመርም
የምትኖር ለዘለዓለም
ሞገዱን በቃልህ ታዘዋለህ
ጠላትን ትቀጠቅጣለህ
ጌታ ምስጋና ይድረስህ ።

ሃሌሉ . . .

አሜን ኢየሱስ

አሜን ኢየሱስ አሜን ምስጋና
ይህ የእኔ ጌታ ቶሎ የሚሰማ
ኢየሱስ አቤት ሲያጽናና ።

1. በቀውጢ ሰዓት ልቤ እጅግ ዝሎ
ነፍሴ ለጠላት ወዲያ ተጥሎ
አጽናኝ ከመንገድ ተሰውሮብኝ
አይዞህ የሚለኝ ወዳጅ ጠፍቶብኝ
ዞር አልኩኝ መስቀል አይቼ
ፍቅርህን ሰምቼ ።

አሜን ኢየሱስ . .

2. ያ ጽኑ ጉልበት የታመንኩበት
የጠላት ምሽግ ያፈረስኩበት
ድንገት ተሰርቆ ሟሾ አየሁት
የነፍሴ ዕርቃን ሲገለጽባት
ዞር አልኩኝ መስቀል አይቼ
ፍቅርህን ሰምቼ ።

አሜን ኢየሱስ . .

3. የችግረኛን ጩኸት አድምጦ
ኀዘን በደስታ ወዲያው ለውጦ
ዳግመኛ አቆመኝ አገገምኩና
ነፍሴም ዘመረች ቅኔ ምስጋና
ተመስገን መስቀል አይቼ
ፍቅርህን ሰምቼ ።

አሜን ኢየሱስ . . .

ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔር አምላክ ነውና

1. ከጥፋት ጉድጓድ ውስጥ ከረግረግ ጭቃ ያወጣኝ
እግሬን በድንጋይ ላይ አቁሞ ያጸናኝ
በጸጋው ደግፎ በሕይወት ያኖረኝ
ከከፋ ፍላፃ በእጁ የከለለኝ ።

ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔር አምላክ ነውና ስገጂለት
መሃሪው ጌታዬ ምስጋና ይብዛለት
በሕይወቴም ሁሉ እኔም ልገዛለት
ቸርነቱን ልንገር ምህረቱን ልዘምር
ቅኔ ልቀኝለት እ ቅኔ ልቀኝለት ።

2. ድካምን ሕመምን ቁስልን ስብራትን አይቶ
ዘመድ ርቆ ሲቆም ኢየሱስ ተጠግቶ
በፍቅር አክሞ ሕይወትን ያድሳል
ለውለታው ምላሽ ከቶ ምን ይገኛል ።

ነፍሴ ሆይ . . .

3. የጫንቃዬን ሸክም ጌታዬ ሰብሮ ጣለልኝ
የዕዳዬን ጽሕፈት በሞቱ ሻረልኝ
ምህረቱ ድንቅ ነው በኔ ላይ ያሳየው
ከእግሩ ሥር ወድቄ ጌታዬን ላክብረው ።

ነፍሴ ሆይ . . .

እግዚአብሔር ይመስገን

1. ያለፈው አለፈ ላይመጣ እንደገና
ዘንድሮን ተያያዝነው ልንኖር በምስጋና
ያስጨነቀን ማዕበል በእግሩ ተረግጧል
በእግዚአብሔር አምላክ ቁጥጥር ሥር ሆኗል ።

እግዚአብሔር ይመስገን (4)
ሃሌ ሃሌ ሉያ ስሙ ከፍ ከፍ ይበል
ማዕበሉን ጸጥ አርጎ በድል አሻግሮናል ።

2. በአልን አይደለም እኛ የምናመልከው
ለአስታሮት አይደለም እኛ የምንሰግደው
በድንቅ ያየነውን እግዚአብሔራችን ነው
የፍጥረት ገዢውን ኤልሻዳይ አምላክ ነው ።

እግዚአብሔር ይመስገን . . .

3. ቅጥራችን ደኅንነት በራችን ምስጋና
ማን ሊጸቋመን ነው ዳግም እንደገና
እግዚአብሔር ለእኛ መታመኛችን ነው
ታዳጊ አጋራችን ክብራችን ስሙ ነው ።

እግዚአብሔር ይመስገን . . .

4. ስናዝን ስለኛ ልቡ ይታወካል
ስናለቅስ አምርረን ከኛ ጋር ያለቅሳል
በኀዘን አይቀርም ቃሉን ይናገራል
ማዕበሉን ጸጥ አርጎ ፈውሱን ያሳየናል ።

እግዚአብሔር ይመስገን . . .

ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ

ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ
አጥንቶቼም ታላቅ ስሙን ባርኩ
ጠላት ቢደነፋ እያልፍም ከልኩ
ነፍሴም አጥንቴም እግዚአብሔርን ባርኩ ።

1. ሙራው ሲፈነጥቅ ጉሁ ሲቀድ ማለዳ
ገልጠን እናያለን የጠላትን ጓዳ
ሜዳውን የሞላው የአራዊት መንጋ
ከሜካው ይገባል ይህ ሌሊት ሲነጋ
ማን ችሎት ይቆማል ጌታ ከተዋጋ ።

ነፍሴ ሆይ . . .

2. ጀንበሯ ልትወጣ ደቂቃ ሲቀራት
ዓይን ቢወጉ አያሳይ የጨለማው ብርታት
ጌታም ዘንበል ሲል ደቂቃ ሲቀረው
የፈተናው ዓይነት ቁጥሩ እጅግ ብዙ ነው
ቢሆንም ግድ የለም ድሉ የእግዚአብሔር ነው ።

ነፍሴ ሆይ . . .

3. እግዚአብሔር አይቶአል የእንባ ኑሮሽን
አመስግኝው ነፍሴ ተይው እሮሮሽን
አንቺ ስታለቅሺ ጠላት ይደሰታል
መውደቅሽን ሊያውጅ ከበሮ ይመታል
እልል በይ ነፍሴ ፈራጅሽ ተነሥቷል ።

ነፍሴ ሆይ . . .

ክብር ልዕልና

ክብር ልዕልና በሰማይ ላለኸው
ቅድስና ብጽዕና ካንተ ዘንድ ለሆነው
እንቀኝልሃለን በምድር ላይ ያለነው
ከፍ ልናደርግህ አንተው በሠራኸው ።

1. ምስጋና ሊያወሩ ምላሶች ታዘዋል
ክብርህን ለመስጠት እፊትህ ቀርበናል
ውዳሴ ሙገሳ ሁሌ ላንተ ይሁን
አፋችንን ከፍተን ልንሰጥህ ክብርን ።

ክብር ልዕልና . . .

2. አንተን ስላገኘን ሰላም ተሞልተናል
በውስጥህ ስላለን ደስታን አግኝተናል
ፍቅርና በጐነት በአንተ ስላለን
ግንዳችን ስለሆንክ ፍሬያችን አማረ ።

ክብር ልዕልና . . .

3. ራስን የመግዛት ትዕግሥትንም ሁሉ
የመንፈስ ፍሬዎች በውስጣችን አሉ
የነጻ ስጦታ ባንተ ስላገኘን
ጌታ ሆይ ከፍ በል እንወድስ ስምህን ።

ክብር ልዕልና . . .

4. በአንተ ረክተናል ጌታ ሆይ ተባረክ
እውነተኛውን ለውጥ በኛ ስላደረክ
አሁንም ተመስገን እስከ መገለጥህ
ባልተሰማ ዜማ እስክናወድስህ ።

ክብር ልዕልና . . .

ምስጋና የሚገባውን

ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን እጠራለሁ
ከጠላቶቼም እድናለሁ ።

1. የዓመጽ ፈሳሽ ሲያስፈራኝ የሲኦል ጣርም ሲከበኝ
እምላክህ የታለ ሲለኝ ባላንጣዬ ሲያፌዝብኝ
ከመሠረቴ ሲነቅለኝ ቆይ ብቻ ሲል ሲዝትብኝ
የጌታን ስም እጠራለሁ ከጠላቴም እድናለሁ ።

ምስጋና የሚገባውን . . .

2. የጌታ ኢየሱስ ስም ለኔ የጸና ግንብ ነውና
እስከዛሬም እርሱን ጠርቶ ማንም አላፈረምና
በኪሩቤል የሚኖረው ሙሉ ተስፋ ስለሰጠኝ
ታምኜ ስሙን እጠራለሁ ከጠላቴም እድናለሁ ።

ምስጋና የሚገባውን . . .

3. በጨነቀኝ ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔርን ጠራሁት
ስቅስቅ እያልኩኝ በእንባ የሆዴን ብሶት ነገርኩት
ከዚያም በበቀል ወረደ ከሰማይ እንጉደጉዶ
በመብረቁ አወካቸው በፍላፃው በተናቸው ።

ምስጋና የሚገባውን . . .

4. ለጥርሶቻቸው ንክሻ አላደረገኝምና
ከተዘረጋብኝ ወጥመድ ሁሌ አድኖኛልና
እርነቴን ከሚቀማ ከሰይጣን ጋርዶኛልና
ስሙ ይከበር ሃሌሉያ እያልኩኝ ልኑር በርሱ ጉያ ።

ምስጋና የሚገባውን . . .

በሮች ይከፈቱ

1. በድካም ውስጥ ሳለሁ ሁሌ ለምትረዳኝ
በሕይወቴ ሙላት ጌታ ላንተ ልቀኝ
ያኔ ስርበተበት በፍርሃት ውስጥ ስዋኝ
ጌታ ያንተ ድምጽ ነው በልቤ የተሰማኝ ።

በሮች ይከፈቱ ምስጋና እሰዋለሁ
እዘምለታለሁ ቃሌ እርሱን ይጣፍጠው
ለሞተው ሕይወቴ ነፍስን ዘርቷልና
መንግሥቱም ይባረክ ስሙም ይግነን ገና ።

2. ድንግዝግዝታ ውጦኝ መንገዴ ጠፍቶብኝ
ጨለማውን ገፎ ብርሃን አበራልኝ
ማዕበል አስደንግጦኝ ጭንቀቴ እጅግ በዝቶ
ሰላም ላንተ ይሁን አለኝ ልቤን ከፍቶ ።

በሮች ይከፈቱ . . .

3. ብቸኛ ሰው ሆኜ ኃጢአት ሲያባርረኝ
በፍቅሩ ጠራኝና ከሰው ቀላቀለኝ
ዝም ብዬ ስባዝን መድረሻ ሳይኖረኝ
ማስተዋልን ስጠኝ መንግሥቱን አሳየኝ ።

በሮች ይከፈቱ . . .

4. ምኞት አብሰልስሎኝ ሕይወቴ እጅግ ከስቶ
ጥጋቤ ሆነልኝ ኢየሱስ ውስጤ ገብቶ
ያሰብኩት ተሟልቶ እርካታ ሳይኖረኝ
ጌታ ግን ሲመጣ ሕይወት ፈለቀልኝ ።

በሮች ይከፈቱ . . .

የምስጋናን መሥዋዕት እንሰዋለን

የምስጋናን መስዋዕት እንሰዋለን
ከልብ ምስጋና በዜማ ቃና
በመንፈስ ሕብረት በደሙ አንድነት
እንሠዋለን አሜን ለበጉ ክብር እንዘምራለን ።

1. አንድ አርጐናልና ኢየሱስ በደሙ
አስተሳስሮናል በሕመሙ
ከጠላት ወጥመድ ያመለጡ ሁሉ
ክብር ለበጉ ይመስገን እሉ ።

የምስጋናን መስዋዕት . . .

2. የሞቱ አጥንቶችን ኢየሱስ ሰብስቦ
ሕይወት ዘራባቸው መንፈሱን ሰጥቶ
ዛሬ ጠላትን የሚያስፈራራው
የአምላክ ሕዝብ ነው ምስጋና የሰዋው ።

የምስጋናን መሥዋዕት . . .

3. የደሙ ዋጋዎች ተመስገን እሉት
በመንፈሱ ኅብረት በደሙ አንድነት
ምርኮኞች ሁሉ በጌታ ያሉ
በምሥጋና ቃል ወጡ ሆ እያሉ ።

የምስጋናን መሥዋዕት . . .

ክበር ክበር ብዬ

ክበር ክበር ብዬ ጌታዬን ላከብረው (2)
ውለታው ብዙ ነው ።

1. ኢየሱስ ጌታዬ ለኔ ስላረገው
መላእክት ባድናቆት በርሱ ዙሪያ ከበው
ሁሉም በአንድነት በእግሮቹ ሥር ወድቀው
ክብር ለታረደው ሲሉ እንደዚህ ሰማሁ ። (2)
ክበር ክበር . . .

2. በመስቀል ላይ ሞቶ ሕይወት የሰጣቸው
በፈሰሰው ደሙ እጥቦ ያነጻቸው
ከመላእክቱ ጋራ ተዋኸዶ ድምጻቸው
ቅዱስ ቅዱስ ብለው ሲሰግዱ አየኋቸው ።

ቅዱስ ቅዱስ ብዬ ጌታዬን ልባርከው (2)
ማደሪያው ንጹሕ ነው ።

3. መላእክት ሳይሆኑ ባለቤቱ እኔ ነኝ
ከሙታን መካከል ሕይወት ያገኘሁኝ
ቃሌና ዜማዬም ባይሆን እንደመላእክት
ግድ የሚለኝ አለ አልቻልኩም ዝም ማለት ።

ንጉሥ ንጉሥ ብዬ ጌታዬን ላንግሠው (2)
ሞገሱ ትልቅ ነው ።

4. ሠሪ ሆኖ ሳለ የሰማይ የምድር
ዝቅ ብሎ አጠበ የሰዎችን እግር
ያላደረገልኝ የቱ ነው ምንድር ነው ?
እንደምን ልግለጸው ከቋንቋም በላይ ነው ።

ክበር ክበር ብዬ ጌታዬን ላከብረው (2)
ትህትናው ግሩም ነው ።

5. ይገባችኋል ወይ የዚህ ጌታ ነገር
ከዙፋን ተነሥቶ እላም በረት ሲያድር
ሰዎች ምን እንበለው እስኪ አሳብ አምጡ
እኔስ ቃል አጠረኝ የሚገልጽ ማንነቱን ።

ክበር ክበር ብዬ ጌታዬን ላከብረው (2)
ፍቅሩ እጅግ ታላቅ ነው ።

ማን እንዳንተ

ማን እንዳንተ እረ ማን እንዳንተ
ጌታ ሆይ ማን እንዳንተ
እንኳን ሊመስልህ
ጭራሽ ሚደርስህ አይገኝም ።

1. ነገሥታት ቢበዙ እንዳንተ አይፈርዱም
ጠቢባን ቢበዙ እንዳንተ አኮ አያውቁም
ሐኪሞች ቢበዙ እንዳንተ አይመረምሩም
የልብን አዋቂ አንተ ብቻ ጌታ ።

ማን እንዳንተ . . .

2. ቸሮችም ቢበዙ እንዳንተ አይለግሱም
ርኅሩሆች ቢሞሉ ያንተን ያህልም አያዝኑም
አሳቢዎች ቢመጡ የልብን አያደርሱም
ከሁሉም የምትበልጥ አንተ ብቻ ጌታ ።

ማን እንዳንተ . . .

3. ጌጣጌጥ ቢበዛ እንዳንተ አያሳምርም
ገንዘብም ቢሆን ያላንተ ብር አይሆንም
ውድ ነገር ሁሉ እንዳንተ አይወደድም
ከሁሉም የምትልቅ አንተ ብቻ ጌታ ።

ማን እንዳንተ . . .

እጄን ይዞ መራኝ

1. አንዳንዴ ሳስታውስ የዓለም ኑሮዬን
እንደ ተሰቃየሁ ሳላገኝ ጌታዬን
ሰላም ስሻ ስከንፍ ስቀር በየቦታው
ፈልጐ አገኘኝ የሰላሙ ጌታ ።

እጄን ይዞ መራኝ ጌታዬ
የዘለዓለም ባለውለታዬ
አንስቶኛል ከዓለም ገበያ
በተራዬ ልበል ሃሌ ሉያ ! ሃሌሉያ ።

2. በጭንቀት ገደልን ልወጣ ስቧጥጥ
ወጥቼ ወጥቼ ተመልሼ ስወድቅ
እጁን ሳከ ለኔ መጠለያ ሆነኝ
ከረግረጉ ኃጢአት ባህር ውስጥ አወጣኝ ።

እጄን ይዞ መራኝ . . .

3. ስሙን ኢየሱስ አሉት አዳኝ ስለሆነ
ኃጥአን ሊድኑበት እርሱ መነመነ
እኔን አሰቃዩኝ እነርሱን ተዋቸው
ብሎ እነጴጥሮስን ከጉድ አዳናቸው ።

እጄን ይዞ መራኝ . . .

ጌታ ነህ

ጌታ ነህ ጌታ ነህ ለዘለዓለም
ኢየሱስ ጌታ ነህ ለዘለዓለም ።

1. ጌታ ማዳንህን አይቻለሁ
የምሕረት ክንድህን ቀምሻለሁ
በመላ አይደለም ጌታ ያልኩህ
በእውነት የምትሠራ ጌታዬጌታ ነህ ።

ጌታ ነህ . .

2. ለሁሉ እንደ ሥራው ትከፍላለህ
ዳግመኛ በክብር ትመጣለህ
ከዙፋንህ ሆነህ ትፈርዳለህ
ለዘለዓለም አንተ ትነግሣለህ ።

ጌታ ነህ . . .

3. ክንድህ ጠንካራ ነው የሚረታ
እስረኞችን ከእስር የሚፈታ
ስምህም ኃይል አለው የበረታ
የጨለማን ሥልጣን የሚገታ ።

ጌታ ነህ . . .

4. የሕይወት ምንጭ ነህ ለተጠማ
ነጻ የምታወጣ ከጨለማ
ሕዝብህን በብርሃን የምትመራ
የንጋት ኮከብ ነህ የሚያበራ ።

ጌታ ነህ . . .

የኃያላን ሁሉ ኃያል ነህ

1. ሰማይን የሠራ የምድር ፈጣሪ
በዘለዓለም ዙፋን ለዘለዓለም ኗሪ
ገናናነትህን ሰማያት ያውቃሉ
ምድርና ሞላዋም ይመሰክራሉ ።

የኃያላን ሁሉ ኃያል ነህ
የነገሥታት ሁሉ ንጉሥ ነህ
የጌቶችም ሁሉ ጌታ ነህ
ባለ ታላቅ ግርማ ኤልሻዳይ ነህ ።

2. በነገሥህ ጊዜ ክብርህን ስትለብስ
ለተጠቃው ህዝብህ ፊትህን ስትመልስ
ድንቅ አድራጐትህን በምድር ስታደርግ
በጽድቅም ስትፈርድ ዓመጻን ስትጠርግ ።

የኃያላን ሁሉ . . .

3. ቃልህን ስትሰጥ በሲና ተራራ
በልጆችህ ሰፈር በበረሃው ሥፍራ
በክብር እሳትህ ተራራውን አጤስከው
በመረጥካቸው ፊት ክብርህን ገለጥከው ።

የኃያላን ሁሉ . . .

4. የተዳፈሩህን የተነሡብህን
ልክህን ሳያውቁ የታጠቁብህን
እየቀጣሃቸው ተረቶች ሆነዋል
ተፈርተህ ተከብረህ አንተ ግን ኖረሃል ።

አሜን በሉ ስገዱለት

1. ባህር ተናወጡች ተራሮችም ጨሱ
የሰማያት አምላክ ወጣ ከመቅደሱ
ክብሩ ምድርን ሞላ ቁጣውም ነደደ
ለልጆቹ ሊያግዝ ጌታችን ወረደ ።

አሜን በሉ ስገዱለት
ለዚህ አምላክ እኛን ለረዳን
ውርደትን በክብር ለውጦ
ጠላታችንንም ቀጥቅጦ
እኛን ላበዛን

2. እግዚአብሔር ነገሠ አሕዛብ ይነገጡ
በኪሩቤል ዙፋን ላይ በመቀመጡ
እነዚያ በፈረስ በሠረገላቸው
በታመኑበትም ጌታ አሳፈራቸው ።

አሜን በሉ ስገዱለት . . .

3. ድምጹ እንደ ነጐድጓድ ክብርን የለበሰ
መልኩ ሰባት ጊዜ ከፀሐይ የባሰ
ፊነጠቀባቸው የብርሃኑን ጮራ
እንዳለ ሊያስታውቅ ከልጆቹ ጋራ ።

አሜን በሉ ስገዱለት . . .

4. ምድርና ሞላዋ ለአምላካችን ናት
ዓለምና በርሷ ሁሉ የሚኖሩት
እግዚአብሔር ወረደ በተራሮች መሃል
በክብር ተሞልቶ እኛን ለመከለል ።

አሜን በሉ ስገዱለት . . .

ወደር የማይገኝልህ

ኢየሱስ ሆይ ከፍ ከፍ በል ልበልህ
ጌታ ሆይ ክበር ተመስገን ልበልህ
ወደር የማይገኝልህ ከሞት ያድናል ስምህ (2)

1. ስምህ እንደሚፈስ ዘይት ነው ጠልቆ ወደ ውስጥ ይገባል
የደረቀን አጥንት አረስርሶ ስብራትን ይጠግናል
ሸባውንም አዘልለህ የዛለን ጉልበት ታፀናለህ
ልብን ኩላሊትን መርምረህ ለደካማው ኃይልን ትሰጣለህ ።

ኢየሱስ ሆይ . . .

2. በነፍስ በሥጋ ሥልጣን አለህ የበሽታን ሥር ነቅለህ ትጥላ
የታወረውን ዓይን አብርተህ የጐበጠውን ታቃናለህ
ፍጹም ድንቅ ነው ስምህ ያድናል የተጨነቁትን ከሕመም
ከድቅድቅ ጨለማ ያወጣል ወደ ማይደነቅ ብርሃን ።

ኢየሱስ ሆይ . . .

3. ጌታዬ ስምህ ኃይል አለው አጋንንትን ይቀጠቅጣል
በስሜትም ከመገዛት ከማይረባ ልማድ ያላቅቃል
ጥላቻንም አስወግዶ ሁሉን አንድ ያደርጋል በፍቅር
መራራን ሕይወት ለውጦ ያጣፍጠዋል እንደ ማር ።

ኢየሱስ ሆይ . . .

4. በእምነት ወዳንተ የቀረበ በሕያው ስምህ ይድናል
ከሞት ባሻገር ያለውን የዘለዓለምን ሕይወት ይወርሳል
ቸሩ የኔ ጌታ ኢየሱስ በእውነት አንተ ፍቅር ነህ
ልዑል እግዚአብሔር ሆይ ከፍ ከፍ በል ልበልህ ።

ኢየሱስ ሆይ . . .

እናመልከዋለን

እናመልከዋለን ለዘለዓለም
እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም ።

1. ብዙ አማልክት አሉ ዛሬ በምድር ላይ
ውስጣቸው ባዶ ነው ምስጢራቸው ሲታይ
እኛስ አምላካችን ስንሰማም ስናየው
ምንም አይጉለውም ሁሉም በሁሉም ነው ።

እናመልከዋለን . . .

2. ስመጥር ነበሩ ብርቱ የተባሉ
ፍጹም የማይወድቁ ጽኑ የሚመስሉ
ነገር ግን አለፉ አብቅቶ ጊዜያቸው
እግዚአብሔር ግን አለ ዛሬም በላያቸው ።

እናመልከዋለን . . .

3. የሰማይ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ
ሁሉንም በጊዜው ውብ አድርጎ ሠሪ
እንዲህ ያለ አምላክ ከቶ የት ይገኛል
ቀድሞ ካልነበረ ዛሬስ ከየት ይመጣል ?

እናመልከዋለን . . .

4. እግዚአብሔር ትልቅ ነው ከሁሉም ይበልጣል
በሰማይ በምድር ሁሉንም ይገዛል
ዘመን ሲለዋወጥ ሁሉም ሲቀየር
በሥፍራው ይኖራል በዘለዓለም ክብር ።

እናመልከዋለን . . .

የዘለዓለም አምላክ

የዘለዓለም አምላክ የዘመናት ንጉሥ
ሁሉ በሁሉ ነው የናዝሬቱ ኢየሱስ

1. ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው ኢየሱስ
አይሰለችም ከቶ አንተ እንኳን ብታምጽ
የመስቀሉ ቃል ፈውስ ነው ለሕይወት
አምነው ለተጠጉት ይሆናል መሠረት ።

የዘለዓለም አምላክ . . .

2. ለሠልፍ አዘጋጅቶ ኃይልን ያስታጥቃል
በላይ የቆሙትን ከበታች ይጥላል
በትንግሌው ሥልጣን ውጊያን አካሂዶ
ምርኮን ሰብስብ አለው ጠላቱን አሳዶ ።

የዘለዓለም አምላክ . . .

3. ፍላፃን ወርውሮ ምሽግን ነደለ
በአምላኩ ተማምኖ ውጊያውን ቀጠለ
በደም ጉዳና ላይ የኢየሱስ ነው ድሉ
ብሎ ዘምሮለት ቆመ በዕጣ ክፍሉ ።

የዘለዓለም አምላክ . . .

ብሩክ ይሁን

1. እኛን ያዩ ዓይኖችህ ብሩክ ይሁኑ ለዘለዓለም
እኛን የዳሰሱ እጆችህ ብሩክ ይሁኑ ለዘለዓለም
ብሩክ ይሁኑ ለዘለዓለም ። (4)

2. እኛን የሰሙ ጆሮችህ ብሩክ ይሁኑ ለዘለዓለም
ወደኛ ያቀኑ እግሮችህ ብሩክ ይሁኑ ለዘለዓለም
ብሩክ ይሁኑ ለዘለዓለም ። (4)

3. ዓለም የማትሰጠውን ሰላም የሰጠን ጌታ ስሙ ይባረክ
ከመንፈሱ አፍስሶ ያረካን ለዘለዓለም ስሙ ይባረክ
ለዘለዓለም ስሙ ይባረክ ። (4)

4. መጽናናት የሰጠን እግዚአብሔር ስሙ ይባረክ ለዘለዓለም
ያጋንንትን ምሽግ አፍርሷል ስሙ ይባረክ ለዘለዓለም
ስሙ ይባረክ ለዘለዓለም ። (4)

የሚቋቋምህ ማንም የለም

የሚቋቋምህ ማንም የለም
ፈቃድህ በእኛ ይሙላ ይፈጸም
ታላቅነትህም ይነገር
ጌታዬ ሆይ አንተ ብቻ ክበር ።

1. ሕዝብን ከምድር ዋጅተሃል
ታላቅ ሥራን ጀምረሃል
አሳብህ አይከለከልም
ጽድቅህ እውነትህ ይለምልም

የሚቋቋምህ . . .

2. በየደረስንበት ሥፍራ
ሥራችንን አንተ ሥራ
እጃችን ሳይዝል ሳይደክም
ዛሬም እንደ ወትሮው ቅደም ።

የሚቋቋህም . . .

3. ስለተነቀፈው ስምህ
በምርኮ ስላለው ሕዝብህ
ይዘርጋ ያ ጽኑ ክንድህ
ዛሬም ይንሰራራ ክብርህ ።

የሚቋቋምህ . . .

4. ወድቀን በፊትህ ስንሎህ
ክንድህ ከፍ ይበል ጌታ ሆይ
ሰማይ ምድሩ ያከብርሃል
ሁሉም በፊትህ ይሰግዳል ።

የሚቋቋምህ . . .

ብርቱ ነው

1. በኃይል የበረታ ጥበቡ የላቀ
ፍቅሩ ከአእምሮ በላይ የጠለቀ
ለሰው መሻት ሁሉ አጥጋቢ መልስ ነው
ስሙን አስከባሪ እግዚአብሔር ብርቱ ነው ።

ብርቱ (3) ነው እግዚአብሔር እርሱ ብርቱ ነው
ሁሉን ችሎ ሁሉን የሚያስችለው እግዚአብሔር ብርቱ ነው ።

2. በጠላት ድንፋታ ሕዝቡ ሲርበተበት
መንጋው ተደናግጦ ሲበታተንበት
ደርሶ በመሰብሰብ አጽንቶ የሚያቆመው
የቤቱ ጠባቂ እግዚአብሔር ብርቱ ነው ።

ብርቱ ነው . . .

3. በበረሃ ስፍራ ምንጭን ያዘጋጃል
በሙታን ሸለቆ ትንሣኤን ያውጃል
የፍጥረት መሠረት ሁሉን ቻይ የሆነው
ክንዱ የማይላላ እግዚአብሔር ብርቱ ነው ።

ብርቱ ነው . . .

4. ቃል ኪዳን አክባሪ ዋስትናው የጸና
ዘመን የማይሽረው ታማኝ ባለዝና
እግዚአብሔር ብርቱ ነው መቼ ይሸነፋል
በርሱ የሚታመን ሁሉን በድል ያልፋል ።

ብርቱ ነው . . .

ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው

ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው
ውጊያው የእግዚአብሔር ነው
ድሉ የእግዚአብሔር ነው
ባሪያው ምስክር ነው ።

1. እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው
የሚያስፈራኝ ማነው ?
እግዚአብሔር ለሕይወቱ መታመኛዋ ነው
አስደንጋጩስ ማነው ?
ክፉዎቹ አስጨናቂዎቹ
የነፍሴ ብርቱ ጠላቶቼ
ተሰነካክለው በጽኑ ወደቁ
በጌታ በኢየሱስ ስም ደቀቁ ።

ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው . . .

2. ሠራዊትም ቢሰፍርብኝ ልቤ አይፈራም
ሰልፉም ቢያስገመግም
እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለምኜዋለሁ
እርስዋን እጠብቃለሁ
በሕይወቴ ዘመናት በሙሉ
በቤቱ ኖሬ እንድቃሉ
ጌታዬ ደስ ያለውን ሲሠራ
አይቼ ስለ ክብሩ ላወራ ።

ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው . . .

3. በመከራዬ ቀን በድንኳኑ ሰውሮኛል
በዐለቱ አጽንቶኛል
ዙሪያዬን ባሉ ጠላቶቼ ፊት አቆመኝ
ከፍ ከፍ አረገኝ
አባቴና እናቴም ሲተዉኝ
እግዚአብሔር ወዶ ተቀበለኝ
የእልልታ መሥዋዕት እሠዋለሁ
ለአምላኬ ክብር እዘምራለሁ ።

ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው . . .

ናና ጌታችን

ናና ጌታችን ናና
ዳመናትን ሰንጥቀህ ውረድ
ለኛ ተዋጋ
የዲያቢሎስን ምሽግ አፈራርስ ።

1. ቀስትህን ወርውር ጠላትህን ውጋ
የዲያቢሎስን ሰፈር ምሽጉን አናጋ
ኃይላችን አንተ ነህ ጉልበታችን
ቅደምልን ጌታ ፊት ፊታችን ።

ናና ጌታችን . . .

2. ሰይፍህን ምዘዝ ኃይልህ ይገለጥ
እሳትህን አውርድ ጠላታችን ይቅለጥ
በስምህ ወጥተናል ወደ ጽዮን
በደምህ ቅጠረን አንተ ምራን ።

ናና ጌታችን . . .

3. ከአንተ እንጠብቃለን ከታላቅ ክንድህ
የአጋንንትም ጭፍሮች ይውደቁ በእጅህ
መሠረታችን ሁን ምሰሶአችን
እስክንገባ ጽዮን አገራችን ።

ናና ጌታችን . . .

ተስፋ ቁረጥ

1. ተስፋ ቁረጥ ሰይጣን
   እኔን አትፈትነኝ
   ተስፋ ቁረጥ
   በጣም የሚያጸናኝ ጠባቂ እረኛ አለኝ
   ተስፋ ቁረጥ ።

2. ተስፋ ቁረጥ ሰይጣን አትምጣ ወደኔ
   ተስፋ ቁረጥ
   የዓለም ሁሉ አዳኝ ነውና መድኅኔ
   ተስፋ ቁረጥ ።

3. ተስፋ ቁረጥ ሰይጣን መከራ አታከማች
   ተስፋ ቁረጥ
   የኔ አምባ የኔ ኃይል አይደለምና ሟች
   ተስፋ ቁረጥ ።

4. ተስፋ ቁረጥ ሰይጣን ወንጌሉ ተዘራ
   ተስፋ ቁረጥ
   ነፍሳት አመለጡ ከገሃነም መከራ
   ተስፋ ቁረጥ ።

5. ተስፋ ቁረጥ ሰይጣን አትችልም ልትይዘኝ
   ተስፋ ቁረጥ
   በጌታ በኢየሱስ በደሙ ውስጥ ነኝ
   ተስፋ ቁረጥ ።

6. ተስፋ ቁረጥ ሰይጣን ኢትዮጵያችን ዳነች
   ተስፋ ቁረጥ
   የወንጌልን ቃል በመመገብ ላይ ነች
   ተስፋ ቁረጥ ።

7. ተስፋ ቁረጥ ሰይጣን ነፍሳት ተከማቹ
   ተስፋ ቁረጥ
   የኢየሱስ አዳራሽ ስለሆነ ምቹ
   ተስፋ ቁረጥ ።

አሜን ክበር

አሜን ክበር ጸሎታችን ተሰምቷል
ጠላት ቅስሙ ተሰብሯል
በአዲስ ኃይል በፍቅር ጉዞ ጀምረናል ።

1. አሜን ክበር ጌታ ስምህም ይባረክ
ለእኛ ኃጢአተኞች ኃይልህን ገለጽክ
ጸሎታችንን ሰማህ አዲስ ኃይል ሰጠኸን
በጠላታችን ፊት ከፍ ከፍ አረግኸን ።

አሜን ክበር . . .

2. ጩኸታችንን ሰምቷል ጌታ ፈውሶናል ።
ፍቅሩን አገናጽፎ በድል አቁሞናል
መቼ አየኸንና እንደ በደላችን
በትእግሥት እያየህ ያን ከፉ ሥራችን ።

አሜን ክበር . . .

3. እኛን የገረመን የጌታ ፍቅር ነው
በርከክ ስንል ጭራሽ ጸሎትን ሲሰማው
ትዕግሥተኛው ጌታ ፍቅር ያስገደደው
ያዝንልናል እኮ ድካማችንን ሲያየው ።

አሜን ክበር . . .

4. ጠላትም ቢከሰን ከአንተ ሊለየን
እግዚአብሔር ተመስገን ቅስሙን ሰበርክልን
ይህ እኛን ሲገርመን አዲስ ኃይል ሰጠኸን
የጠላት ድል መምቻ ኃይል አገናጸፍከን ።

አሜን ክበር . . .

እንዲያው መሮጡ

እንዲያው መሮጡ ጠላቴ አለመታከቱ
ጌታን ማስቆጣቱ ከአምላክ መጣላቱ
ላያገኘኝ ከንቱ ።

1. የማይታዩ ጭፍሮች አሉኝ
ከእረኛው ኢየሱስ የታዘዙልኝ
በእሳት ነበልባል ይጋረፉሉ
ተንኮለኛውን ከእኔ ያርቃሉ ።

እንዲያው መሮጡ . . .

2. ፈርኦን መስጠሙን አልሰማ ይሆናል
ተራው ሲደርሰው ያኔ ይማራል
ዮርዳኖስ ሞልቶ ኋላ እንደ ቀረው
ደርሷል መሰለኝ ጠላቴም ተራው ።

እንዲያው መሮጡ ጠላቴ . . .

3. ይታገለኛል ዛሬም ሰድብቶ
ያ ሟች ጠላቴ ቀራንዮን ረስቶ
ሺ ዓመት ታስሮ ወደ ፍርድ ሊባል
ደርሷል መሰለኝ ጊዜው ቸኩሏል ።

እንዲያው መሮጡ . . .

እስከ ዛሬ ድረስ

1. የጠላት ከበባ ሠልፉ ተበትኗል
ለቅሶ ተለውጦ የምሥራች ሆኗል
አይቻልም ያልነው ብዙ ነገር ነበር
ሁሉ ግን ተችሏል እግዚአብሔር ይክበር ።

እስከ ዛሬ ድረስ ረድቶናል
በድንቅ በተዓምር መርቶናል
ከእንግዲህም ቢሆን ጌታ ያውቃል
ሁሉም በእርሱ ያልቃል ።

2. ታሪክን መለወጥ ጌታ ልማዱ ነው
ውጊያው ቢበረታም እርሱ አሸናፊ ነው
ባለፉት ዘመናት እግዚአብሔር ያሳየን
ብዙ የተከማቸ የድል ታሪክ አለን ።

እስከ ዛሬ ድረስ . . .

3. ጥርጥር ሲጠፋ እምነት ሲሆንልን
ጨለማ ሲገፈፍ ብርሃን ሲበራልን
ቁስላችን ሲፈወስ ሰባራው ሲጠገን
አሁንም አሁንም እግዚአብሔር ይመስገን ።

እስከ ዛሬ ድረስ . . .

4. እረፍት አግኝተናል መንፈሳችን ሰክኗል
እዬዬ ተረስቶ ሃሌሉያ ሆኗል
ማልቀስ አቁመናል እንባችን ታብሷል
ጠላት በመጣበት አፍሮ ተመልሷል ።

እስከ ዛሬ ድረስ . . .

5. አምናና ካቻምና ዛሬም ትናንትና
ድንቅን ያደረገው እግዚአብሔር ነውና
ነገም በሚሆነው አምላክ አይተወንም
እርሱን ከማያይ በቀር ሌላ ዓይን የለንም ።

እስከ ዛሬ ድረስ . . .

የሠራልኝን ድንቅ

የሠራልኝን ድንቅ ታሪኩን ላውጋችሁ
ሰዎች እስኪ ስሙ ትምህርት ይሁናችሁ
በጌታ ይታመን ያጽናና ልባችሁ

1. በዕለት እርምጃዬ እግሬ ኢየሱስ ቀደሞ
ምህረቱን አብዝቶ ታምራቱን ደግሞ
አሳየኝ አምላኬ የከበረ ነገር
እንደዚህ ሊመራኝ ወደ ጻድቃን አገር (2)

የሠራልኝን ድንቅ . . .

2. በቀኝ በግራዬ አድፍጦ አድብቶ
መልካም መሰል አጥቂ ወጥመዱን ዘርግቶ
ጌታ ግን ባያድነኝ በደንብ ተደራጅቶ
ዲያብሎስ ሊያጠቃኝ ነበር ተሰናድቶ (2)

የሠራልኝን ድንቅ . . .

3. እርሱ ቅጥር ሲቀጥር በአምላኬ እየዘለልኩ
ወጥመድ ሲዘረጋ እኔም እያመለጥኩ
በኔ ብርታት ሳይሆን በጌታ እየታመንኩ
ሩጫ እቀጥላለሁ ሁሉን እያሸነፍኩ (2)

የሠራልኝን ድንቅ . . .

4. በዘለዓለም መድኅን ከጥልቁ ወጥቼ
ከአባት ከእናት ዘመድ የሚበልጥ አግኝቼ
በአሕዛብ መካከል ለርሱ ዘምራለሁ
የከበረ ስሙን አመሰግናለሁ (2)

የሠራልኝን ድንቅ . . .

ና ፊትፊታችን ውጣ

ና ፊት ፊታችን ውጣ ጌታ (2)
ያላንተ መቆም አንችልምና
በሠልፉ ሜዳ ና ቀድመህ ተዋጋ
በሠልፉ ሜዳ ና ተዋጋ ።

1. እንደ ኤልሳዕ ባሪያ ዓይናችንን ክፈት
ዓይናችንን ክፈት ጌታ እንድንቆም በድፍረት
ወደ ሠልፉ ስንሄድ አንተ ቀድመህ ውጣ
አንተ ቀድመህ ውጣ ጌታ እኛ እንዳንረታ ።

ና ፊት ፊታችን . . .

2. የአብርሃም የይስሃቅ የያዕቆብም አምላክ
አንተ ቀድመህ ውጣ ጌታ እኛ እንድንባረክ
እኛ በምስጋና ሆ እያልን ስንዘምር
አንተ ተዋጋና ጌታ በጦር ሜዳው ክበር ።

ና ፊት ፊታችን . . .

3. እኛ ጌታ አንችልም አንተ ካልተዋጋህ
ነበልባል ሠይፍህን መዘህ ከኛ ፊት ካልወጣህ
ጌታ አንተ ድል አርገህ በድል ስንመለስ
በምስጋና ዜማ ሆነን በፊትህ እንድንደርስ ።

ና ፊት ፊታችን . . .

ጋሻ ጦርህን አንሣ

ጋሻ ጦርህን አንሣ እግዚአብሔር
የዲያብሎስን ምሽግ አፈራርስ ምሽጉን አፈራርስ
ቀስቱን ስበርልን ፍላፃውን መልስ
በታላቅ ስምህ የዲያብሎስ ሰፈር ይተራመስ ።

1. ጦርን አስከትቶ የከበበንን
በቀኝ በግራ የወረሩንን
የሚያውከንን የዲያብሎስ መንጋ
በታላቅ ስምህ በጦርህ ይወጋ ።

ጋሻ ጦርህን አንሣ . . .

2. በነጐድጓድ ውረድ በኃይልህ ተነሣ
የአጋንንትን ሠፈር አሳጣው መድረሻ
በደምህ የተዋጀውን ሕዝብህን የሚያውክ
በኢየሱስ ደም በስሙ ይድቀቁ ።

ጋሻ ጦርህን አንሣ . . .

3. በግርማህ በክብርህ በኃይልህ ውረድ
ምድር ትገዛልህ ተራራም ይናድ
ና አግዘን ጌታ ጠላት ይደናገጥ
በመስቀሉ ኃይል ዲያብሎስ ይረገጥ ።

ጋሻ ጦርህን አንሣ . . .

4. የወንጌልን እውነት የሚከላልስ
ሕዝብን የሚያለያይ የክፉ መንፈስ
በምድር የዘራውም የጨለማ ሥራ
በመስቀሉ ኃይል ይብነን እንዳቧራ ።

ጋሻ ጦርህን አንሣ . . .

ጽኑ ጦር ብርቱ ኃይል

1. ጋሻ ጦሩን ይዞ ሠይፋን መዞባቸው
ነፍሴን ከሚዋጉት ጌታ ተዋጋቸው
የጦር ሜዳ አዝማች ቆራጥ ጦረኛ አለኝ
እግዚአብሔር ተነሣ ሠይፋን መዘዘልኝ ።

ጽኑ ጦር ብርቱ ኃይል ከጌታ
ጠላቴን አሳዶ ምሽግ የሚመታ
ጋሻውን አንግቦ ሠይፋን ነቀነቀ
ይህን ሲያይ ጠላቴ በቅጽበት ወደቀ ።

2. የአሳዳጇን መንገድ በሠይፍ ስለት ዘጋ
ጉዳቴን የማይወድ ጌታ እጁን ዘረጋ
የከበቡኝ ሁሉ ኃፍረት ከበባቸው
የጌታ ኢየሱስ ደም ስለ ተዋጋቸው

ጽኑ ጦር . . .

3. የመላእክት ጠባቂ አምላኬ ሰጥቶኛል
የደም እሳት ቅጥር ዙሪያዬን ከቦኛል
የስውር ጦር አለኝ ጌታዬ የሰጠኝ
ሁሉን እችላለሁ ኃይልን በሚሰጠኝ ።

ጽኑ ጦር . . .

4. ጦር ሜዳው ሥጋዬምሽጌም እምነት ነው
መዋጊያዬም ቃሉ ስለታም ሰይፍ ነው
በጌታ ኢየሱስ ስም ምሽግ እሰብራለሁ
ኃይልን በሚሰጠኝ ሁሉን እችላለሁ።

ጽኑ ጦር . . .

እግዚአብሔር ነው ታዳጊያችን

እግዚአብሔር ነው ታዳጊያችን ፥
በጦር ሜዳ መዋጊያችን
በድካም ውስጥ ምርኩዛችን
በስደት ውስጥ መጽናኛችን
እሱን ይዘን የትም ብንወጣ
የፈለገው ነገር ቢመጣ
ኢየሱስ ብለን ስንጮኽ በእምነት
እንወጣለን በአሸናፊነት ።

1. በታላላቅ ነገሥታት ፊት
ስንከበብ በጠላት ሠራዊት
ኢየሱስ ብለን በእምነት ስንጠራ
ጠላት ብትን ይላል እንዳቧራ ።

እግዚአብሔር ነው . . .

2. ከየአራቱም ማዕዘናት
ቢያስጨንቀንም ጦርነት
ብርቱ ስለሆነ ታዳጊያችን
ያለመጠን ሰፍተዋል ድንበራችን ።

እግዚአብሔር ነው . . .

3. ከግራ ከቀኝ ከዚህም ከዚያ
ሲያዋክበንም የዓለም ውጊያ
ሁሉን በጌታ ችለን አልፈናል
ለምዕዓቱ ዋዜማ ደርሰናል ።

እግዚአብሔር ነው ታዳጊያችን . . .

እረኛችን ይጠብቀናል

እረኛችን ይጠብቀናል
ከአዳኝ ወጥመድ አስጥሎናል
ወጥመድ ተሰብሮ እኛ አምልጠናል
ረድኤታችን ተዋግቶልናል ። (3)

1. የጠላትን ፍላፃ ሰብሮ
እኛን የከለለ ፈጥኖ
ከቅጥራችን ኋላ የቆመው
የእሳት ነበልባል የሆነልን
ዘንዶውን ደርሶ ቀጠቀጠው
ወጥመዱን ሰብሮ ከእግራችን በታች ጣለው

እረኛችን . . .

2. ሰልፍ ደርቶ ውጊያው ጠንክሮ
የጦሩ ሜዳ ደም ተነክሮ
ጠላት ሲያይል ጌታን ጠራነው
በውጊያው ሜዳ ቅደም አልነው
እርሱም በበቀል ከፍ አለልን
በአምላካችን ኃይል ከቅጥሩ በላይ ቆምን ።

እረኛችን . . .

3. ሃሌሉያ ጌታ አድኖናል
ኢየሱስ በደሙ ሸፍኖናል
ከእርሱ ሽተን ትርፍ አላጣንም
በጠላት ወጥመድ አልገባንም
ዘንዶውን ደርሶ ቀጠቀጠው
ወጥመዱን ሰብሮ ከእግራችን በታች ጣለው ።

እረኛችን . . .

የመከራን ቀንበር

1. መንሹን በእጁ ይዞ ገለባን ሲያጠራ
ስንዴውን ሊከተው ከጻድቃን ጕተራ
ጊዜውን ቆጠረ ሰዓትና ቀኑን
ሊያውጅ ሊመለስ ነው ክርስቲያን ማረፋን ።

የመከራን ቀንበር ታግሶ ቆይቷል
ክርስቲያን ሊያርፍ ነው አምላኩ አዝኖለታል ።

2. ምሳር ከዛፍ በታች ከዋለ ሊቆርጠው
ጻድቁ ተከፍቶ ኃጥእ ደስ ካለው
ፍርዱ አይዛባም አምላክ ይመዝናል
ገለባን ከስንዴው መርጦ ያቃጥላል ።

የመከራን ቀንበር . . .

3. እንክርዳድ ቢዘራም ጠላት ለብልሃቱ
ቢዝልና ቢደክም ክርስቲያን ጉልበቱ
የዕንባውን ጕርፍ ብዛት ለመከሩ አዝንቦ
አብቦ አሸተለት አምላክ ለርሱ አስቦ ።

የመከራን ቀንበር . . .

4. የንጋትን ጮራ ናፍቆና ጠብቆ
መከራውን ችሎ ችግሩን ደብቆ
ክርስቲያን ሳቅ አለ ትንቢቱ ትዝ ብሎት
የሕይወቱ ጌታ መምጫው ተቃርቦለት ።

የመከራን ቀንበር . . .

ቃላችንን እንደ ቃልህ

ባንተና በሕዝብህ ፊት ቆመናል
ላንክድህ በስምህ ምለናል
ብዙ ቃል ኪዳኖች ገብተናልና ጌታ
ቃላችንን እንደ ቃልህ አጽና ።

1. ሊለካ እምነታችን ሸንጎ ለመቅረብ ደርሰናል
እምነት ወይስ ክህደት ምረጡ ልንባል
ኢየሱስ ላንክድህ ቃል ኪዳን ገብተናል
ብለናልና ጌታ ቃላችንን እንደ ቃልህ አጽና ።

ባንተና በሕዝብህ /. . .

2. አሟሟታችን እንዲያምር በጸሎት ለምነንሃል
እስከአሁንም ድረስ በጸጋህ ቆመናል
መስቀልህ ሥር ሞታችን ይሆናል
ብለናልና ጌታ ቃላችንን እንደ ቃልህ አጽና ።

ባንተና በሕዝብህ . . .

3. ስንዘምር የገባነውን ቃል ኪዳን አልረሳነውም
የችግራችን ገመድ ቋጠሮው ቢጠብቅም
እኛ ከእምነታችን አንነቃነቅም
ብለናልና ጌታ ቃላችንን እንደ ቃልህ አፅና ።

ባንተና በሕዝብህ . . .

4. እሳት ሲንቦለቦልበት የሰላሙን ጊዜ ቃል ኪዳን
እምነታችን ሲነጠር እንደ ወርቅ ሲፈተን
በተጋድሎ ቆመን እስከ ሞት ልንፀና
ብለናልና ጌታ ቃላችንን እንደ ቃልህ አፅና

ባንተና በሕዝብህ . . .

ኃይልህን ቀምሼ

1. ኃይልህን ቀምሼ ክንድህን አይቼ
ክብርህ ተንሰራፍቶ በዓይኔ ተመልክቼ
ያን ሁሉ ዘነጋሁ ዓለምን አይቼ
ልሄድም ተመከርኩ ካንተ ተለይቼ ።

    አንተ ግን ጌታዬ ጠብቀኝ ልጅህን
    እግሬን ልትመልሰው ልትረዳኝ ፍጠን ። (2)

2. ፍቅርህ ግድ ይለኛል እንዳልለይህ
ኮብልዬም ብጠፋ ከጸሎት ደጅህ
ከችንካርህ ሌላ ጸጋህ ምህረትህ
አያስደፍሩኝም ትዝታዎችህ ።

    ከፊትህ ሸሽቼ ወዴት እደርሳለሁ
    ከመንፈስህ እርቄ ወደማን እሄዳለሁ ። (2)

3. ብርክ ይዞ አንገላታኝ ዓላማዬን ስቼ
ወደ ግራና ቀኝ ዓይኖቼን አንስቼ
ኃጥእ ሲለመልም ሲቀናው አይቼ
ፍጻሜውን ሳላይ በሥራው ቀንቼ ።

    ፍሬ የሌለው ከንቱ ለካስ ባዶ ኖሯል
    ግን የእኔው ደስታ ከዓለም ይልቃል ። (2)

4. ነፍሴ ተንገድግዳ ልትወድቅ ነበረ
ግን ድጋፍ አገኘች ጠላቴም አፈረ
የምን መቃለል ነው ጉዳቴስ የቱ ነው
ተደላድያለሁ ኢየሱስ በቀኜ ነው ።

    አረጋግጦልኛል ጌታ እንደማይተወኝ
    ጠላት ተስፋ ቁረጥ አትችልም ልትጥለኝ (2)

እንዳልተውህ እንዳልረሳህ

እንዳልተውህ እንዳልረሳህ ጌታ
ጣርህን አስታውሰኝ በዚያች ጐልጐታ ።

1. ሙት እንኳን ብሆን ለመንቃት የማልችል
የቃልህን ምስጢር ጌታ ሆይ ልቀበል
በድካሜ ብዛት ኢየሱስ ሆይ እንዳልወድቅ
የመስቀልህን ምስጢር ጠለቅ ብዬ ልወቅ ።

እንዳልተውህ . . .

2. ጸጋህ እንደማይለየኝ አምላኬ ሆይ ባውቅም
መውደቅም ስለ አለ በመቆሜ አላምንም
ስለዚህ ጌታ ሆይ በጸጋህ አቁመኝ
ብቻዬን የማልችል እኔ ደካማ ነኝ ።

እንዳልተውህ . . .

3. በስደትም ቢሆን ለስምህ ለመሞት
ኃይልን ብትሰጠኝ ከመንፈስህ ሙላት
ይህን አረስቼ እንዳልመለስ
እንደ ሳምሶን ኃይልን በላዬ ላይ አፍስስ ።

እንዳልተውህ . . .

ኑሮ ያለ ጌታ

1. ኑሮ ያለ ጌታ ታከቶኝ
ኃጢአቴ አስመርሮኝ
ወደ ኢየሱስ ብመለስ የእርሱ ደግነት ማርኮኝ
በድል ጉዳና ብገባ ፍቅሩ ነፍሴን ቢገዛ
ግንባሬን ለጠላት ላልሰጥ ቃል ገባሁኝ ለጌታ ።

በመከራና በጭንቀቴ ሁሉ ጌታን አመልከዋለሁ
ኑሮ ያለ እርሱ ጉዳት ነው ከእርሱ ጋር ግን ደስታ
የመልካም ሁሉ መሠረት ይመስገን የኛ ጌታ ።

2. ስንጨነቅ የሚራራ ስናዝን ፈዋሻችን
በበረሃ ዓለም እያለን ስንጠማ እርካታችን
ዞሮ መግቢያችን ኢየሱስ ማረፊያችን አንተ ነህ
ብንከዳህ እያዋጣንም የድሃ ጉጅአችን ነህ ።

ጌታ ጌታችን ጌታችን አስታውሰን (2)
ብለን ተጣርተን ሳናፍር እስከአሁን ተጉዘናል
በነገር ሁሉ መጽናትን ከጌታ ተምረናል ።

3. የማያሳፍር ስም አይደለም የሰጠኸኝ ጌታችን
ክርስቲያን ጀግንነት እንደሁ ይረዳልን ልባችን
ከፉውን ሁሉ ተቃውመን ከኃጢአት ጋራ ታግለን
ጉዞአችን በድል ያከትማል የጌታን መስቀል ይዘን ።

ክብር ክብር ሃሌሉያ (2)
የነፍሳት ሁሉ ምስጋና ዙፋንህን ይከበበው
በቸርነትህ ተገርሟል በልጅህ የዋጀኸው ።

ተራራው ሸለቆው

1. ጋሬጣው ለምለም ሳር ይሆናል
ሞገዱም ወጀቡም ጸጥ ይላል
ሐሩሩ መልካም ጠል ይሆናል
ጉዞ ካንተ ጋራ ያመቻል ።

ተራራው ሸለቆው ወንዙ ወንዛ ወንዙ
ምቹ ነው ጌታ ሆይ ካንተ ጋር ሲጓዙ
ካንተ ጋር ሲጓዙ (2)

2. ዐለቱ መልካም ምንጭ ይሆናል
አሸዋው በለስን ያበቅላል
ጨለማው ብርሃን ይሆናል
አንተን ይዞ ጉዞ ያመቻል ።

ተራራው ሸለቆው . . .

3. ነፋሱ ክብርን ይሰጣል
መርከቡም በሰላም ይጓዛል
ተራራው ድልድል ሜዳ ይሆናል
አንተን ይዞ ጉዞ ይሳካል ።

ተራራው ሸለቆው . . .

እራሴን ልመልከተው

እራሴን ልመልከተው አጥርቼ
ሌላውን ትቼ
ዓይኔን ወደ አንተ መልሰው
ምን አለኝ ከሰው (አንሳልኝ ከሰው)

1. ኧረ እስቲ እባካችሁ ሰዎች አንድ በሉ
ዓይኔ ሰውን ሊያይ ምነው መቸኮሉ
ፍሬ የሞላው ወይን ኢየሱስ እያለ
ሸንበቆን ለማየት ዓይኔ ከበለለ (2)

እራሴን ልመልከተው . . .

2. የሰዎችን ጉድለት አንድ ሁለት እያሉ
አይጠቅምም በወሬ ጊዜ ማቃጠሉ
የሌላውን ጉድፍ ማየት ይቻለኝ ዘንድ
ትልቁ ምሰሶ ከእኔ ዓይን ይወገድ ። (2)

እራሴን ልመልከተው . . .

3. አጠፋ ለራሱ አበጀም ለራሱ
ሁሉ ለፍርድ ቀን ይዘጋጅ ለመልሱ
እኔም ከእንግዲህ ዓይኔን ከትቻለሁ
ከሰው ላይ ነቅዬ ወደ አንተ አንስቻለሁ ። (2)

እራሴን ልመልከተው . . .

4. ሁለመናህ ንጹህ እንከን የሌለብህ
ቅንጣት ታህል ጉድፍ የማይገኝብህ
አንተን ማየት ቢችል ዓይኔ ተስተካክሎ
ጠላት ባልሳቀብኝ ነፍሴን አጉሳቁሎ ። (2)

እራሴን ልመልከተው . . .

እስኪ ዛሬ

1. መለወጥ ሳይሆን እንዲያው መኖሩ
ማደግም ሳይሆን እድሜ መቁጠሩ
እምኑ ላይ ነው አዋቂነቱ
እድሜውን ፈጅቶ ከእነ እትብቱ
እምኑ ላይ ነው አዋቂነቱ ።

እስኪ ዛሬ ሰብስብ ምላስክን
ሌላውን ሳይሆን እየው እራስክን
እስኪ ዛሬ ልሰብስብ ምላሴን
ሌላውን ትቼ ልየው እራሴን ።

2. ሌላው ሲሳደብ ከተሳደበ
ምኑን ተካነ ምኑን ቀረበ
ሌላው ሲጠጣ አብሮ ከጠጣ
አይሻልም ወይ በዚያው ቢወጣ
እግዚአብሔር አምላክ መቼ ሰው አጣ ።

እስኪ ዛሬ . . .

3. ያነበቡትን ማስተማር ብቻ
የአንገት ሃብል ጀሮ ጉትቻ
ክርስቶስ ጌጥ ነው ከላይ ተሰቅሏል
ውስጡ ግን በኃጢአት ተቃጥሎ ከስሏል
ምነው ከዚህ ሁሉ ቢቀር ይሻላል ።

እስኪ ዛሬ . . .

4. የክርስቶስ ፍቅር ገመድ አይደለም
ተፈታ እንጂ ታሰር አላለም
ወዶ መከተል ጠልቶ መለየት
<u>ነጻነት አለህ ሁሉን ለማየት ።</u> (2)

እስኪ ዛሬ . . .

5. እገሌ እገሊት ወንድሜ እህቴ
አሰናከሉኝ ጉዳኝ በሕይወቴ
ምክንያት አታድርግ ሰበብ አታብዛ
በክርስቶስ ፍቅር እራስህን ግዛ
ሕይወት ሕይወት ነው አይደለም ዋዛ ።

እስኪ ዛሬ . . .

ዕድሜ ልኬን

አንድ ነገር እናፍቃለሁ
ይህንንም እንጓለሁ
ዕድሜ ልኬን በቤትህ እኖር ዘንድ ። (4)

1. ባገኝ ባጣ ምን ልጐዳ
መኖር እመርጣለሁ ባንተ ጓዳ
ደጃፍህ ተጥሎ ክብርን ሁሉ አጥቶ
መኖር ይሻለኛል በቤትህ ተጠልቶ ።

አንድ ነገር . . .

2. በዓለም ሆኜ ብገኝ ገናና
ኑሮዬ ቢደላኝ ባገኝ ዝና
አንተ ካልኖርክበት በዕለት ኑሮዬ
ሁሉ ወደ ጥፋት ይሆናል ሩጫዬ ።

አንድ ነገር . . .

3. ፍቅርህ ማርኮኝ መጥቻለሁ
ከእንግዲህስ ወዴት እሄዳለሁ
በዓመታት መካከል ድንቅህን አይቻለሁ
ጸጋህ ስለበዛ ዛሬንም ቆሚያለሁ ።

አንድ ነገር . . .

4. ዝዬ ልወድቅ ስንገዳገድ
አንተው አሳየኸኝ የድልን መንገድ
ጠላቱን በድፍረት እንዳየው ረዳኸኝ
በሕያዋን መንገድ በብርሃን መራኸኝ ።

አንድ ነገር . . .

ዙሪያችንን ስናይ

ዙሪያችንን ስናይ የከበበንን
እጅግ ደስ አሰኘን በአንተ መሆናችን
በድቅድቅ ጨለማ ታላቅ ሰላም አለን
ከብዙ ፍላጻ ጌታ ጠብቆን ።

1. እረኛው አንድ ነው የበጐች ጠባቂ
ከተኩላና ከድብ ከአንበሳ አራቂ
እጅግ ደስ አሰኘን የአንተ መሆናችን
በዙሪያችን ካለው በመጠበቃችን ።

ዙሪያችንን ስናይ . .

2. ከኛ ጋር ያሉትን የአምላክ ሠራዊትን
በዙሪያችን ካለው ሲጠብቁን አየን
ጌታ ስላሳየን ልባችን ተጽናንቷል
በሚሆነው ሁሉ ታላቅ ሰላም አለን ።

ዙሪያችንን ስናይ . . .

3. በለመለመ መስክ መሪያችን ኢየሱስ
ከፋውን መለሰው ወደኛ እንዳይደርስ
ስለዚህ ደስ አለን የጌታ ስለሆን
በዙሪያችን ካለው ጠባቂ ስላለን ።

ዙሪያችንን ስናይ . . .

ምን ነው አልተማረም አሉኝ

1. የማመልከው አምላክ ሳይንስ አይጨብጠው
የፈደላት ብዛት እውቀት አይገምተው
መንፈሳዊ ዓይኖች ተከፍተው ካላዩት
ቃሉ ሞኝነት ነው አውቀናል ለሚሉት ።

ምን ነው አልተማረም አሉኝ
ለእግዚአብሔር አድሬለት ቢያዩኝ
ትርፌንና ጥቅሜን ባለማወቃቸው እኔ አዘንኩላቸው ፣
ይልቅ ሳይጨልም መዝገያው ሳይቆለፍ የሰው ልጅ
ይመለስ
ለሚጠፋው ዓለም ጉልበቱን ከማፍሰስ ።

2. የሚጠፉ ቅሪት ማከማቸት ትቼ
ዘለዓለማዊውን ለማግኘት ተግቼ
ጌታዬን የሙጥኝ ብዬ በመወሰኔ
ከአዋቂዎች በላይ አልሆንኩም ወይ እኔ ።

ምን ነው . . .

3. ምድርና ሰማይን ያበጀ ፈጣሪ
አይመረመርም ገብቶ ላብራቶሪ
ቁጥርን ከቁጥር ጋር ሲያጋጩ ቢኖሩ
አያዩትም ጌታን እሩቅ ነው አገሩ ።

ምን ነው . . .

4. ሰዓቱ ገና አለ ጊዜያችን አልከፋም
እግዚአብሔር ደጁን በሰው ልጅ አልዘጋም
ከማንቀላፋቱ ነቅቶ ለታረመ
ብርሃን ነው ገና ቀኑ መች ጨለመ ።

ምን ነው . . .

ተራራ ስወጣ ስበረታ

ተራራ ስወጣ ስበረታ
ጠላቴን በቅጽበት ድል ስመታ
ደግሞም በድርቀት ውስጥ በሸለቆ
እምነቴ ተሟጦ ፍጹም ደርቆ
ቆሚያለሁኝ ባንተ እስከዛሬ
ስምህን ልወድሰው በዝማሬ ።

1. በጺጋ ስጦታ መበልጸጌ
ቃልህን እየተመገብኩ ማደጌ
ለማጉረምረም ሕይወት ስፍራ ለቆ
ገፍትሮ ሲጥለኝ በሸለቆ
የምህረት እጅህን ስለተደገፍኩ
ኃይል ያንተ ነውና ሁሉን አለፍኩ ።

ተራራ ስወጣ . .

2. የምስጋና ሕይወት የዝማሬ
ጭራሽ እልም ሲል ከመንደሬ
ተስፋ ያደረኩት ሲርቅብኝ
ጉም እንደ መጨበጥ ሲሆንብኝ
በወጀብ ውስጥ መንገድ ያለህ ጌታ
ዛሬ አደረስከኝ ሳልረታ ።

ተራራ ስወጣ . . .

3. ከጠላት ጉሮሮ ተናንቄ
ውጊያ በርትቶብኝ ተጨንቄ
ጩኸቴን ከሰማይ አድምጠሃል
ጥርሱን በመንጋጋ ውስጥ ሰብረሃል
ጽኑ ተዋጊ ብርቱ ጠረኛ
የታምራት አምላክ ታምረኛ ።

ተራራ ስወጣ . . .

እስከዛሬ የጠበከን

እስከ ዛሬ የጠበከን
ከፍላፃ የሸፈንከን
ጻርቻችንን ያሰፋህልን
እንባችንን ና አብስልን ።

1. በማይገሰስ ጉልበትህ
በማይሞከረው ኃይልህ
አንተነትህን አሳየኸን
ለእኛም ከለላ የሆንከን ።

እስከ ዛሬ . . .

2. የጠላትን ቁጣ አይተን
ልባችንን ስንመዝን
ተስፋ ቆርጠን ወየው ስንል
አማኑኤል ደረስክልን ።

እስከዛሬ . . .

3. በማባበል ሊያቅማማ
ካልተሳካም ሊያስፈራራን
ጠላት ሲጥር ሊያሸካክብን
ሴራውን ያከሸፍክልን ።

እስከ ዛሬ . . .

4. የድልን ኑሮ የኖረ
ከእግዚአብሔርም የተማረ
ቢማቅቅም ያሸንፋል
የአምላኩንም ስም ያስጠራል ።

እስከ ዛሬ . . .

እስኪና ጌታ

1. በሰው ፊት አልቅሼ
አላገኘሁ መላ
ወዳንተ እመጣለሁ
አንተም ወደእኔ ና ።

እስኪና ጌታ እስኪ ና ኢየሱስ
እስኪና ጌታ (2)
የማጫውትህ ብዙ አለኝና
እስኪና ጌታ ። (2)

2. እስኪ ና ማለቴ
የሚያደምጠኝ ባጣ ነው
ሰው ለኔ አይረባኝም
ሰምቶ ዝም ባይ ነው ።

እስኪና ጌታ . . .

3. ድምጼ ባይሰማህ
አብዝቼ አለቅሳለሁ
በምድር ሰሚ የለኝ
ላንተው እነግራለሁ ።

እስኪና ጌታ . . .

4. ለሰው የማልነግረው
ብዙ አለ በውስጤ
አንዴ ናልኝና
ላጫውትህ የልቤን ።

እስኪና ጌታ . . .

የኤልያስ አምላክ ወዴት ነህ ?

የኤልያስ አምላክ ወዴት ነህ ?
የያዕቆብ አምላክ ወዴት ነህ ?
ዛሬም እኔን ተመልከተኝ
ባህሩን ክፍለህ አሻግረኝ ።

1. መንጋዜን አይቶ ወደ ጽዮን
ይከተለኛል ፈርኦን
አንተው እየው ተመልከተው
የኤርትራን ባህር ክፈለው ።

የኤልያስ አምላክ . . .

2. አሶር ቢመጣ ጭፍራውን ይዞ
ጠላት ቢነሣ ሰይፉን መዞ
ጌታ ተዋጋ ቅደምና
ኃይላችን ሆነህ እንደገና ።

የኤልያስ አምላክ . . .

3. ከፊቴ ያለው ኤርትራ ነው
ወደኋላም ባይ ጠላቴ ነው
መሄጃው ጠፍቶኝ ደንግጬአለሁ
ባህሩን ምታው ክፈለው ።

የኤልያስ አምላክ . . .

4. የፈርኦን አሳብ ትዕቢቱ
ታየ በሥራ ምኞቱ
አሳቡ ነበር ለባርነት
ጌታ ይሰጣል ነጻነት ።

የኤልያስ አምላክ . . .

ድምጽህ ይሰማኝ

1. እኔ ያንተ በግ አንተ የኔ እረኛ
ከመንጋህ ኮብልዬ ብሆን እልከኛ
የምድረበዳ ኑሮ እንደማይመች አውቃለሁና
ሰብስበኝ ኢየሱስ ብቻዬን ነኝና
አደራህን ጌታ ።

ድምጽህ ይሰማኝ (2) ለኔ
ድምጽህ ይሰማኝ
መመሪያ እንዲሆነኝ
ከክፉም እንዲጠብቀኝ
ድምጽህ ይሰማኝ ለኔ ድምጽህ ይሰማኝ ።

2. መስሎኝ ነበር ያኔ በግል የምገፋው
ከቤትህ ወጥቼ መሞቴን ሳላውቀው
ያ ትምክህቴ ሁሉ አሁን ከኔ ዘንድ የለምና
መባዘን በቃኝ ሰልችቶኛልና
አደራህን ጌታ ።

ድምጽህ ይሰማኝ . . .

3. ምንም አላተረፍኩ ከቤትህ ወጥቼ
ያለኝን ከመክሰር ለዓለም ሰጥቼ
ይህች አጭር ዘመኔ እንደ ጥላ ከኔ ላይ ሳታልፍ
ስትጠራኝ ልሰማ በክንድህ ላይ ልረፍ
አደራህን ጌታ ።

ድምጽህ ይሰማኝ . .

4. አውቄያለሁ አሁን ነፍሴ እንደተጐዳች
ወደ ሞትም ማጀት ቁልቁል እንደሮጠች
መቅበዝበዜ ታይቶት መንፈስህ በኔ እጅግ አዝኖአልና
ወደ ዕረፍት መግባት ናፍቄአለሁና
አደራህን ጌታ ።

ድምጽህን ይሰማኝ . . .

ጩኸቴን ስማ

ጩኸቴን ስማ ይኸውና
ድምጽህን አሰማኝ እንድጽናና (2)

1. በልቼ ጠገብኩ ለሥጋዬ
ነፍሴ ተራበች አ ጌታዬ
ለሥጋ ብቻ በማሰቢ
አጥንቴ ታየ በመራቢ ።

ጩኸቴን ስማ . . .

2. እጄ ደንዝዞ የያዝኩበት
ለአንተ ዘርግቼ የጮኸኩበት
እጄን አወረድኩ በመድከሜ
በዝቶ ኃጢአቴና ሕመሜ ።

ጩኸቴን ስማ . . .

3. ክብሬ ተገፎ ተዋርጄ
ኃጢአቴን ቆጠርኩ ከእጆቼ
በማደግ ፋንታ ጫጭቻለሁ
ያንን የድል ክንድ እመኛለሁ ።

ጩኸቴን ስማ . . .

4. መገንባት የለም አፈርሳለሁ
የእምነት ቤቴን እንዳለሁ
ጌታ ሥራልኝ ስልችቶኛል
ባንተ መታመን ይሻለኛል ።

ጩኸቴን ስማ . . .

መቼ ነው ነቅቼ

1. ማለዳ እየመጣህ ስታነቃኝ
ጆሮዬን ከፍተህ ስትናገረኝ
በማስተዋል መንገድ ስትመራኝ
ከሕይወት ምንጭ ውኃ ስታረካኝ ፤
ለምልሞ ነበር ሕይወቴ
እንዲህ አልዛለም ጉልበቴ
እባክህ አስበኝ አንተ ነህ መድኃኒቴ ።

መቼ ነው ነቅቼ ድምጽህን የምሰማው
የነፍሴ መጉብኘት መጽናናቴ የሚመጣው ። (2)

2. በለሊት ስነሣ ከእንቅልፌ
ስምህ ነው የሚመጣው ፊጥኖ ባፌ
ሕመሜን ለአንተ እናገራለሁ
ድምጽህን አሰማኝ እማራለሁ ፤
ጌታ ሆይ መቃተቴን ስማ
ነፍሴ እንደዚህ ተዳከማ
እንደምን ትዘልቃለች ትካዜን ተሸከማ ።

መቼ ነው . . .

3. የተወሰነው ሰዓትህ ሞልቶ
የኀዘኑ ጊዜ አብቅቶ
ድካም ድንዛዜ ተወግዶ
ኃይልህ የሚሞላኝ ከላይ ወርዶ ፤
መቼ ነው ደስ የምሰኘው
በጉብኝትህ የምጽናናው
ጉልበት ተመልሶ በእግሬ የምቆመው ።

መቼ ነው . . .

ማለዳ ስነሣ ጭንቀቴን ላዋይህ

ማለዳ ስነሣ ጭንቀቴን ላዋይህ
ነፍሴን ያዛላትን ችግሬን ላሳይህ
ግራ ቀኙም አልል ምስጢረኛም የለኝ
ኢየሱስ ፈጥነህ ናና ከጎዘኔ ገላግለኝ ። (2)

1. ምነው መጨነቄ ረዳት እንደሌለው
አህዛብ ያውቃሉ በአንተ እቅፍ እንዳለሁ
አጥፍቼም እንደሆን ቅጣኝ እንደልጅህ
የለፋህብኝ ነኝ ፈሶልኛል ደምህ ። (2)

ማለዳ ስነሣ . . .

2. በዓይን የማይታዩ ሠራዊቶች አሉኝ
ጠላቴን ከእግሬ ሥር የሚያንጋልሉልኝ
ብዬ ተናግሬ ለዓለም ዙሪያ ሁሉ
አሁን ብንቀጠቀጥ ታዲያ ምን ይላሉ (2)

ማለዳ ስነሣ . . .

3. ጉድለቴን አውቃለሁ እኔው ነኝ ምክንያቱ
ለሥጋም ለነፍሴም እሾክ የሆንኩቱ
አንተ ግን አንተው ነህ ምህረት የተሞላህ
ጠግነኝ በቁጣህ አስተምረኝ እንዳሻህ ። (2)

ማለዳ ስነሣ . . .

ሰምቶ የሚመልስ

1. ሁሉን ቻይ የሆነ ነው ጌታዬ
ድጋፍ መከታ ነው ለሕይወቴ
በመከራዬ ሁሉ የሚያጽናናኝ
ከጠላት ታዳጊ አምላክ አለኝ ። (2)

ሰምቶ የሚመልስ አይቶ የሚራራ
አምላክ እኔስ አለኝ አባት እኔስ አለኝ ።

2. ወደእርሱ ሳነባ ስንበረከክ
የልቤን ትርታ የሚያዳምጥ
በእሳት የሚመልስ ጌታ አለኝ
ክብርና ውዳሴ ለርሱ ይሁን ። (2)

ሰምቶ የሚመልስ . . .

3. ስለዚህ ጠላቴ ደስ አይበልህ
አምላኬ ዝም ያለኝ አይምሰልህ
የሚሆነው ሁሉ ለበጐ ነው
ያለ እርሱ ፈቃድ የማይደርስ ነው ። (2)

ሰምቶ የሚመልስ . . .

አቤቱ መባረክን ባርከን

1. ያቤፅንም ሰምተሃል እንደዚህ ሲለምንህ
ነፍሱን ባርከህለታል አገሩንም አስፍተህ ።

አቤቱ መባረክን ባርከን አገራችንን አስፋ
እጅህም በኛ ላይ ትሁን አንተ ነህ የኛ ተስፋ

2. በልጅህ ስቃይና በጣር የተወለድን
እኛም ፍሬዎችህ ነን አሰባስበህ ጠብቀን ።

አቤቱ . . .

3. ከፊትህ አትጣለን እንማጸንሃለን
በሞገስህ አስበን በመድኃኒትህ ጐብኘን ።

አቤቱ . . .

4. ሰማያቱም ይከፈት መንፈስህ ይፍሰስልን
ሕይወታችን ትረስርስ ነፍሳችን ትጥገብልን ።

አቤቱ . . .

5. ብቻችንን አንቅር አብዛን እየባረክኸን
አበልጽገን በጸጋህ አሳድገን በቃልህ ።

አቤቱ . . .

6. እግዚአብሔርን በማወቅ ምድር እስክትሞላ
ምልጃችን ይቀጥላል ጉልበታችን ሳይላላ ።

አቤቱ . . .

ልገዛልህ ጌታዬ

1. እንደማርያም ከእግሮችህ ሥር እቀመጣለሁ
ክብሬን ዝናዬን ያለኝን ሁሉ ከታች እጥላለሁ
ክብሬን ዝናዬን ሁሉ እጥላለሁ ጌታ እገዛልሀለሁ ።

ልገዛልህ ጌታዬ
እርሜን ነቅዬ
ሌላው አሳቤን ከኋላ ጥዬ
ልገዛልህ ጌታዬ ።

2. የማሳዝንህ የማጸይፍህ ብሆን ወራዳ
ልጅ ከአባቱ ቤት የሚሻለውን ወዶት ያገኛል
ይኸው ጀርባዬን እሰጥሃለሁ ብትገርፈኝ እወዳለሁ ።

ልገዛልህ ጌታዬ . . .

3. መንገዳቸውን እንደማያውቁት ተላላፊዎች
ነፍስ ስከተል ያለ አሳብ ሮጬ እንዳልሳሳት
ሥጋዬን ግዛው ጌታ እባክህ ልገራ በልጓምህ

ልገዛልህ ጌታዬ . . .

4. ዝና ይቅርብኝ ሀብትም አይረባኝ ክብርም አይጠቅመኝ
ከፀሐይ በታች ምን ትርፍ ይገኛል ሁሉም ከንቱ ነው ።
እድል ፈንታዬ አንተ ነህና ጌታ ላንተ ልገዛ ።

ልገዛልህ ጌታዬ . . .

ከጣራዬ በታች

ከጣራዬ በታች ጓዳዬ
መቼ ነው የማከብርህ ጌታዬ (2)

መቼ ነው (3) በኑሮዬ ክብርህ የሚታየው ፣

1. እንደ በሽተኛ የቃል ሰው መሆኔ
መቼ ይሆን የሚድነው በሽተኛው ጐኔ
ብዙ ብዙ ነገር ስለአንተ አወራለሁ
በሬን ስታንኳኳ ዞር በል እልሃለሁ ። (2)

ከጣራዬ በታች . . .

2. ለአፌ በጉባኤ እጅጉን ውዴ ነው
ከጣሪያዬ በታች በቤቴ ባዕድ ነው ።
ከሚወዱህ ጋር ከንፈሬን እመጣለሁ
ለብቻዬ ቤቴ ለጣእት እሰዋለሁ ። (2)

ከጣራዬ በታች . . .

3. ባለህበት አብራ ነበረ ትእዛዙ
ጭራሽ ከኔ ሆነ የጥፋት መዘዙ
ምላሴ በመቅደስ ጌታ ጌታ ይላል
ኑሮዬ ጦር ይዞ አንተን ያሳድዳል ። (2)

ከጣራዬ በታች . . . .

4. አልገባኝም ላልል ላስተምር እላለሁ
አልሰማሁም ላልል እያሰማሁ አለሁ
በግሌ ለራሴ ቤቴ ሳላመልክህ
ራሴን ሳታልል ደረሰ ምጽአትህ ። (2)

ከጣራዬ በታች . . .

እንደሎጥ እንደኖኅ

እንደ ሎጥ እንደ ኖኅ ዘመን
ኃጢአትን እጅግ አበዛን
ጌታ ሆይ እባክህ ገስጸን
አባት ነህና ቆንጥጠን
<u>ስንጠፋ ዝም አትበለን</u> (4)

1. ልባችንን የመንፈስህ ማደሪያው
ኃጢአት አሸገተው
መቅደስህን ተነሥ ጌታ ሆይ አጽዳው
ሥጋችንን ቅጣው ።

እንደ ሎጥ . . .

2. ደግመህ ደግመህ ስቀለው ሥጋችንን
እንምሰልህ አንተን
በመንፈስህ የጀመርነው ጉዞአችን
ለሕይወት ይሁንልን ።

እንደሎጥ . . .

3. ቅዱስ ስምህን አረግነው መነገሻ
ብር ወርቅን ማትረፊያ
መኖራችን ነበር ለዓለም ብርሃን
ጨለማ ሆነናል ።

እንደሎጥ . . .

4. በሰናዖር ግንባችንን ሠርተናል
እጅግ ተኩራርተናል
ኃጢአት ለብሰን ዓመጸን ደርበናል
ፈውስ ያስፈልገናል ።

እንደሎጥ . . .

መራራ ኑሮዬን

መራራ ኑሮዬን አጣፍጠው
ጠማማውን ልቤን ለውጠው
በቃልህ መዶሻ ቀጥቅጠው
በመንፈስህ እሳት አቅልጠው ።

1. እሽታን የማያውቅ ዓመጸኛ
መሸነፍ የማይወድ እልከኛ
እስከ መቼ ድረስ ልትሸከም
ዓይድን በሽተኛን በማስታመም
አረንቋ ሰርዶውን ነቅለህለት
አንተስ እፎይ ብትል ምን አለበት ?

መራራ ኑሮዬን . . .

2. እግሬ ከወይኑ ግንድ ተገንጥሎ
ወደ ጥፋት መሮጥ ሞያ ብሎ
እጅም ያልታዘዘውን እየሠራ
አፌም ያልተላከውን እያወራ
እንከርዳድ ሲዘራ እንደበቴ
እንደምን ትሠራ በሕይወቴ ?

መራራ ኑሮዬን . . .

3. ጆሮዬ ድምጽህን የማይሰማ
ሐሜትና ወሬ የተጠማ
ዓይን ነው ተብሎ የተሰጠኝ
ከፋት ብቻ እያየ ያስቸገረኝ
መላ እኔነቴን ብትለውጥ
ኑሮዬ ይሆን ነበር የሚጣፍጥ ።

መራራ ኑሮዬን . . .

ሕይወት ያለ ጌታ

ሕይወት ያለ ጌታ ሕይወት ያለ ኢየሱስ ሕይወት መራር እሬት

ኑሮ ከጌታ ጋር ሕይወት ከኢየሱስ ጋር ሕይወት አቤት እረፍት

ኢየሱስን የያዘ በሕይወቱ አቤት እረፍቱ መጽናናቱ (2)

1. ሲያገኝ ደስ ሲለው ሲያጣ እሮሮ
ሲጠፋ ለቅሶ ነው የዓለም ኑሮ
ጥሬ በልቶ ማረፍ በኢየሱስ ነው
ከጌታ ጋር መኖር መታደል ነው ።

ሕይወት ያለ ጌታ . . .

2. ምናምንቴን ነገር ተስፋ የአረገው
የሚያዋጣ መስሎት የሚያዛልቀው
ሊይዘው ቢሞክር ሊጨብጠው
ተስፋው ሁሉ ከንቱ እንደ ጉም ነው ።

ሕይወት ያለ ጌታ . . .

3. እዬዬ ያበዛል ያማርራል
ጌታን ያልያዘ ሰው መቼ ያርፋል
እኛ ግን ሕይወትን እናውቃለን
መዳን በኢየሱስ ነው እመን ብለን ።

ሕይወት ያለ ጌታ . . .

4. የዘለዓለም ሕይወት ለእርሱ አለው
ኢየሱስን ላመነ ለተረዳው
ያላመነ እርሱ ግን ይጠፋል
በዘለዓለም እሳት ይቃጠላል ።

ሕይወት ያለ ጌታ . . .

በጭንቁ ተጨንቆ

1. የሠራዊት ጌታ ኃያሉ መድኃኔ
ሲጠብቀኝ ሳለ ፍርድና ኩነኔ
በኃጢአት ሐረግ ስኖር ተሳስሬ
ከእስራቴ ፈታኝ መራኝ ወደሃገሬ (2)

በጭንቁ ተጨንቆ መስቀል ላይ ተሰቅሎ
ላልረባሁት ልጁ እንዲያ ተጐሳቁሎ
ደሙን አፈሰሰ በፍቅሩ ተገዶ
ሕይወቴን አዳናት ስለኔ ተዋርዶ ። (2)

2. ፍጹም የማልረባ ማስተዋል የሌለኝ
አዳኜን የማላውቅ ፍርድ የሚጠብቀኝ
የሰይጣን ምርኮኛ ሸክም የተጫነኝ
እንዲህ ያለሁ ነበርኩ ጌታ ሳያገኘኝ ። (2)

በጭንቁ ተጨንቆ . . .

3. ፍርሃት መጠራጠር ክፋትና ርኩሰት
ይወገድ ትዕቢት ቅንአት ምቀኝነት
ተንኮልና ውሸት ሐሜት ክፉ ምኞት
ተደምስሰው ይጥፉ በጽዮን ዐለት ። (2)

ይውደቁ ይፈጩ ይድቀቁ ባንድነት
ቀንበሩ ተሰብሯል ይቅርብኝ ባርነት
ዕዳዬ ተከፍሎ ታውጇዋል አርነት
ሞትም አያስፈራኝ ተሰጥቶኛል ሕይወት ። (2)

መልካም ሊቀ ካህን

1. አብ ያከበረው በእርሱ ደስ ብሎት
የመሰከረለት ከሰማይ ሰማያት
በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጁ
የተባለለትን ተቀበል ወዳጁ ።

መልካም ሊቀ ካህን በአምላክ የተቀባ
ለአንተ ደኅንነት ሲል እራሱን የሰዋ
ይጠራሃል ስማው የናዝሬቱ ኢየሱስ (2)
ዕዳህን መክፈሉን አምነህ ተቀበለው
ይህንን ብቻ ነው ካንተ የሚፈልገው ።

2 ዕዳ የለብህም ዕዳህን ከፍሎታል
መርገምህን ደግሞ ተሸክሞልሃል
ታዲያ ወንድሜ ሆይ የዕዳህን ከፋይ
ዝቅ ብለህ በእምነት አትቀበልም ወይ ?

መልካም ሊቀ ካህን . . .

3. የልብህን መዝጊያ በርህን ያንኳኳል
ዘወትር ሳይታክት ክፈትልኝ ይላል
ጊዜው ሳያልፍብህ እባክህ ክፈትለት
ካንተ ጋር ይገባል ይበላልም እራት ።

መልካም ሊቀ ካህን . . .

በኩርነትህን ለምን ሸጥከው ?

1. ለማያጠግብህ ሮጠህ
ምናምንቴን ነገር ወደህ
ረብ ረድኤት ለማይሆነው
በኩርነትህን ሸጥከው ።

በኩርነትህን ለምን ሸጥከው ?
ኢየሱስን ለምን ለወጥከው
ክብርና ገንዘብ ጠፊ ነው
የማይጠፋውን ምረጠው
ጌታ ይሻልሃል የዘለዓለም ሕይወት የሆነው ። (2)

2. ብዙዎች ወደቁ ተጠልፈው
በገንዘብ ፍቅር ተነድፈው
ብልጽግና ያታልላል
ይሁዳ ጌታውን ሸጦአል ።

በኩርነትህን . . .

3. ሠይፍ ከዋጠው የበለጠ
የኃጢአት ዱር ብዙ ዋጠ
አንተን የዋጠህ ምንድን ነው ?
ነፍስህን አንቆ የያዘው ።

በኩርነትህን . . .

ነፍሴ የምትወድህ

1. እንደርሱ የሚሆን ለኔ የለም
እርሱ ነው ያወጣኝ ከዚህ ዓለም
እያለች ሁሌ ታወራኛለች
ነፍሴ ባንተ ፍቅር ተይዛለች ።

ነፍሴ የምትወድህ አንተ ውዴ
እስኪ ልቀኝልህ እኔም ከልቤ
ኢየሱስ ኢየሱስ እሥሬ ትላለች
ነፍሴ ባንተ ፍቅር ተይዛለች ።

2. ከማንም አንተ ስለቀረብካት
ነፍሴን ከመቃብር ስላዳንካት
ስለገባት ይህ ሁሉ ውለታ
ዘምር ትለኛለች ስለ ጌታ ።

ነፍሴ የምትወድህ . . .

3. በዓይኗ ያንተን ሥራ እያታለችና
ትሰዋልሃለች ምስጋና
አንተን ሁሌ እያቆላመጠች
ውዴ እኮ የኔ ነው ትልሃለች ።

ነፍሴ የምትወድህ . . .

4. እኔ እንኳን ልከድህ ባሰብኩ ቁጥር
ነፍሴ አያስችላት ያንተ ፍቅር
ልቧ ጥፍት እስኪል ወዳሃለች
በውዴ አትምጣብኝ ትለኛለች ።

ነፍሴ የምትወድህ . . .

5. ያለፈው ታሪኳን ስታስበው
ከአሁኑ ጋራ ስታስተያየው
ሲበዛባት የአንተ ውለታ
ትለኛለች ምን ላርገው ይሄን ጌታ ።

ነፍሴ የምትወድህ . . . .

አዲስ ሰው ሆንኩኝ

አዲስ ሰው ሆንኩኝ አዲስ ፍጥረት
ከቶ ሳይገዛልኝ ኃጢአት ወይም ሞት ።(2)

1. ከማይጠፋ ዘር ተወልጀአለሁ
በእግዚአብሔር መንፈስ ተለውጫአለሁ
እንደ ልጅ እኔም አድጋለሁ
እንዲሁ እንዳልቀር ተረድቻለሁ ።

አዲስ ሰው ሆንኩኝ . . .

2. ሐዳን ነኝና ዝቅ እላለሁኝ
የጌታዬን ቃል አደምጣለሁኝ
ጥሪውን ሰማሁ ታዝዣለሁ
እርሱ ያለኝን አደርጋለሁ ።
አዲስ ሰው ሆንኩኝ . . .

3. ምንም አላየሁ ጥልቀት ስፋቱን
የጸጋውን መጠን ስፍር ብዛቱን
ፍቅሩን ለማወቅ እጣጣራለሁ
ዓይኔ እስኪከፈት እጠብቃለሁ ።

አዲስ ሰው ሆንኩኝ . . .

4. ስሜቴ ጠፍቶ ቃሉ እስኪገዛኝ
ትዕቢቴን ነቅሎ እርሱ እስኪሰብረኝ
እራሴን መካድ እስኪያስተምረኝ
በጌታዬ ፊት እቆያለሁኝ ።
አዲስ ሰው ሆንኩኝ . . .

5. ስለ ድካሜ ተስፋ አልቆርጥም
እርሱ ቢቀጣኝ አላማርርም
ኃጢአት ባደርግም እልህ አልይዝም
ያነጻኝን ደም ከቶ አላረክስም ።

አዲስ ሰው ሆንኩኝ . . .

ከፉውን የኃጢአት ቀንበሬን

ከፉውን የኃጢአት ቀንበሬን ጥዬ
መልካሙን ያንተን ቀንበር ጌታዬ
እሸከማለሁ ። (2)

1. መልካም ያልሆነውን የከበደኝን
በላዬ ሆኖ ያስጨነቀኝን
በድል ጥዬ አልፌዋለሁ
ያንተን ቀንበር እሸከማለሁ ።

ከፉውን የኃጢአት ...

2. በምህረትህ እየኝ ለአንድ ጊዜ
ወድቄአለሁ በድንዛዜ
ላስከብርህ ከቶ አልቻልኩም
ለመዋረድ አልፈለኩም ።

ከፉውን የኃጢአት ...

3. ምንኛ ጉስቋላ ደካማ ሰው
እንደሆንኩኝ ጌታ አውቀኸው
ከእስራቴ ፍታኝና
በድል ልገዝ እንደገና ።

ከፉውን የኃጢአት ...

4. የልማድ ሕይወቴን አንተ ፋቀው
ለኑሮዬ የማይጠቅም ነው
ሥር እንዳይሰድ ቁረጥልኝ
በድል መንገድ አሰማራኝ ።

ከፉውን የኃጢአት ...

ጌታ ያውቃል

ጌታ ያውቃል ሁሉን እርሱ ያውቃል
ሰው በከንቱ ይጨነቃል ጌታ ያውቃል ። (2)

1. በአሳብ መጨነቅ በከንቱ
ላይሞላ የአሳብ ብዛቱ
ለአምላክ ችግርን ትቶ
መንገዝ ነው በእምነት ተሞልቶ ።

ጌታ ያውቃል . . .

2. ይህን ሲይዙት ያ ሊቀር
የሰው ልብ አያጣ ችግር
እንዳሻው ጌታ ያድርገው
ብሎ መተውን ማወቅ ነው ።

ጌታ ያውቃል . . .

3. በጥበብ በሥጋ በብርታት
አይቻል አሳብን መግታት
እሱ ያለው ይበጃል
ሰው በከንቱ ይጨነቃል ።

ጌታ ያውቃል . . .

4. በኢየሱስ መታመን ታላቅ ነው
ጭንቀትን ሲያስወግድ ብጽዕ ነው
ተከዞ ምንም ላይጨምር
ይቅር በከንቱ መማረር ።

ጌታ ያውቃል . . .

በጎዘኔ በጭንቀቴ

በጎዘኔ በጭንቀቴ አስባለሁ በረከቴን
በጎዘኔ በጭንቀቴ አይዘንጋኝ በረከቴ ።

1. ከማይረባ ስፍራ እዚህ በመድረሴ
በረከቷን ትቁጠር ደስ ይበላት ነፍሴ
ማንም ባያስበኝ አስቦኛል ጌታ
በረከቴን ልቁጠር የአምላኬን ውለታ ።

በጎዘኔ በጭንቀቴ ...

2. በጩኸቴ ባርኮ በለቅሶዬ አጽናንቶ
በድካሜ ድጋፍ በረከትን ሰጥቶ
ዛሬ እንድዘነጋው ሰይጣን ቢከጅልም
በረከት መቁጠሬን ሌት ከቀን አልተውም ።

በጎዘኔ በጭንቀቴ ...

3. እሪታና ዋይታ በዝቶ በሕይወቴ
በረከቴ ጠፍቶ ቢዝልም ጉልበቴ
ብደክም ጉልበቴን ኃይሌን አድሳለሁ
ጌታ የሰጠኝን በረከት አውቃለሁ ።

በጎዘኔ በጭንቀቴ ...

4. ጉስቋላ ሕይወቴን በበረከት ሞልቷል
ጌታ ኢየሱስ አሁን እኔን ተመልክቷል
ሁልጊዜ ደስታዬን በረከት ቆጥሬ
ብሞት አይቆጨኝም አምላኬን አክብሬ ።

በጎዘኔ በጭንቀቴ ...

የመስዋዕቱን በግ

የመስዋዕቱን በግ እንደሆን ጌታ ያዘጋጃል
የኔ መጨነቅ መባከን ከቶ ምን ያደርጋል ።

1 አንዲቷን ጥቁር ጸጉር ነጭ ሳላደርጋት
የኔ መውጣትና መውረድ እንዲያው ከንቱ ልፋት
ዝም ብሎ እርሱን መጠበቁ ይበጃል
እንደ ጌታ ፈቃድ ነገር ሁሉ ይሰምራል ።

የመስዋዕቱን በግ . . .

2 ከሁሉ በማስቀደም መሻት የእርሱን መንግሥት
እንደሚሻል ተናግሮታል ጌታ በማስረገጥ
ከዚያም ሁሉም እንዳስፈላጊነቱ
ይሰጣል ሳይዘገይ በጊዜው በወቅቱ ።

የመስዋዕቱን በግ . . .

3 እኔን የሚሰማኝ ሁሉ በርጋታ ይቀመጣል
ከመከራም ሥጋት ድኖ በክንዱ ሥር ያርፋል
ብሎ ጌታ እየተጣራ በቃሉ
የዓለምን ሸክም ሊያሳርፍ በሙሉ ።

የመስዋዕቱን በግ . . .

4 በኔ መሮጥና መድከም ነገሩ ሳይሞላ
ቁጭትና ጸጸትንም ሊያበከትል ኋላ
የሞርያምን ተራራን በኀዘን መውጣቱ
የጌታን ዓላማ ሳያውቁ መልፋቱ ።

የመስዋዕቱን በግ . . .

የመጽናናት ዘመን

የመጽናናት ዘመን ይሁንልን
የመታደስ ዘመን ይሁንልን
እጆችህ ተዘርግተው ሳይዳስሱን (2)
ዘመናችን እንደ ጥላ አይለፈን ።

1. በበደላችን በኃጢአታችን
በምርኮ ሄደን ወደ ባቢሎን
ሰባውን ዓመት ተሠቃይተናል
በምርኮ አገር አሳር አይተናል
ይብቃን ጌታ ሆይ ምህረትህ ትየን
የመታደስን ዘመን አሳየን ።

የመጽናናት ዘመን . . .

2. በባቢሎን ወንዝ አጠገብ ሆነን
ጽዮንን እያሰብን አለቀስን
ማዶ መሻገር ወደአገራችን
የሕልም እንጀራ እየሆነብን
በተስፋ መቁረጥ እንቆዝማለን
ድር አድርቶበት ማስንቆአችንን ።

የመጽናናት ዘመን . . .

3. ምህረትህ ብዙ እስከ ልጅ ልጅ ነው
ትናንትም ዛሬም ሁልጊዜ አዲስ ነው
ገብቶናል ጌታ ይህ ውድቀታችን
በኛ እንደሆነ መቀጣታችን
እውነተኛውን አምልኮ አስተምረን
ለጨለማው ዓለም ብርሃን አድርገን ።

የመጽናናት ዘመን . . .

4. ጌታ ሆይ ላንተ ምን ይሳንሃል ?
የቂርስን ልብ አነሣስተሃል
ዘመንን መሻር ታሪክ መለወጥ
ተራራን መናድ ባህር ማናወጥ
ይህ ሁሉ ላንተ ቀላል ነገር ነው
ጌታዬ እንዳንተ ያለ አምላክ ማነው ?

የመጽናናት ዘመን . . .

ኀዘንተኛን ያጽናናው

1. ኀዘንተኛን ያጽናናው
የመድኃኒታችን ስም
ያንን ቅዱስ ስም የጠራው
ይረዳል ይድናልም ።

ቅዱስ ስም ብፁዕ ስም
የዘላለም ተስፋ ነው ።(2)

2. ብርቱ ጋሻም ይሆንለት
ኃጢአት ሲፈትነው
ልመናውም ይፈጸምለት
ከኢየሱስ የለመነው ።

ቅዱስ ስም . . .

3. ያ ክቡር የኢየሱስ ስምም
ብዕዕናን ይሰጠናል
ሕይወት ደስታም ሰላምም
ከዚህ ስም አግኝተናል ።

ቅዱስ ስም . . .

4. ወደ ሰማያዊ አገር
አድና ሲያደርሰን
ያንን ስም ለአምላክ ክብር
እንዘምር አክብረን ።

ቅዱስ ስም . . .

ጌታ ባንተ ተማምኜ

1. ዘንድሮ ውስጥ ሆኜ ከርሞን ስመለከት
ጨለማ የዋጠው እሾህ የሞላበት
ለመንገዴ ብርሃን ለእግሬ ጫማ
አንተ ስላለኸኝ ልቤም አያቅማማ ። (2)

ጌታ ባንተ ተማምኜ ዋጋዬን ተምኜ
ወጥቻለሁኝና ጎዳናዬን አቅና ።

2. ኃይሌ ከእኔ ቢርቅ በእምነቴም ደክሜ
ሰው እንዲደርስልኝ አልጠብቅም ቆሜ
በእምነት መገስገሱ ሩጫው ባይሆንልኝ
እንበረከካለሁ ኃይልህን ስትልክልኝ ። (2)

ጌታ ባንተ . . .

3. ፍጻሜ ሳታደርስ ደግሞም ሳታጸና
የጠራኸውን ሰው ሜዳ አትጥልምና
ወደ ማንም ጓዳ አያስብም ልቤ
ልብሴ መጠለያዬ አንተ ነህ ቀለቤ ። (2)

ጌታ ባንተ . . .

4. ጠላቴ ከእግሬ ሥር ወጥመዱን ቢሰውር
ወዳጄም በዓይኔ ላይ ጠጠር ቢወረውር
የሚያቅፍ ልብ ስጠኝ ሁሉን እንዳመሉ
እኔ ምን ቸገረኝ ያንተ ነው በቀሉ ። (2)

ጌታ ባንተ . . .

ማየቱ ተስኖን

1. ባዕድ አገር ሆኖ ለምለም ሥፍራ ያየው
ሙሴ ከነዓንን የተመለከተው
ምድረ በዳውን አልፎ ለመግባት የጓጓው
የእምነት ዓይኖችን ከእግዚአብሔር ወስዶ ነው ።

ማየቱ ተስኖን የተሠራልንን
በላይ በሰማይ ቤት የተዘጋጀውን
በዚህ በምድር ኑሮ ልባችን ከብዶብን
እንዳንቀር ጌታ ሆይ የእምነት ዓይኖች ስጠን ፣

2. ከዮርዳኖስ ማዶ አገር አይቷልና
አልተጠራጠረም ሲያገኘው ፈተና
አጥብቆ ቧጠጠው ተራራ ዳገቱን
በምድረ በዳ ውስጥ ሳያጥፍ ጉልበቱን

ማየቱ ተስኖን . . .

3. በሥጋ ዓይን ያየነው ሁሉ ነገር ያልፋል
ትናንት ያስደነቀን ዛሬ ሰልችቶናል
አሁን ግን የምንሻው በእምነት ማየትን ነው
መከራን ታግሰን እንድንጠብቀው ።

ማየቱ ተስኖን . . .

4. ማየት ስለማንችል ሰው ከዛፍ ለይተን
የጥርጥር ሆኗል የየዕለት ጉዞአችን
አጥርተን እንድናይ በሩቅ የሚሆነውን
ደግመህ ዓይናችንን ጌታ ሆይ ዳስስልን ።

ማየቱ ተስኖን . . .

በእምነት እኖራለሁ

1. ከምድር በላይ ቢሆን ከሰማይም በታች
መግባት መውጣታችንን ዘወትር ተመልካች
እንደ ኢየሱስ ያለ ማንን አገኘችሁ
የሕይወት ዋስትና ቤዛ የሚሆናችሁ ።

በእምነት እኖራለሁ ጌታዬን አውቃለሁ
የኔን ጽኑ እምባ ተጠልዬዋለሁ
ወጀቡን ሳልፈራ ታግዬ እረታለሁ
የክብር ሽልማቱን ከእጁ እረከባለሁ ።

2. ለነገ አይጨንቀኝም ጭጋግ ቢሸፍነው
ወይኑም ቢጠወልግ ሐሩሩ ቢያሰጋው
ለእግሬ መብራት ነው ቃሉ በእጂ ያለው
የተፈጥሮ አዛዥ ኢየሱስ ሕያው ነው ።

በእምነት እኖራለሁ . . .

3. ፈቃዱ ሲሞላ ጌታዬ ከብሮ ሳይ
ምድር እልል ስትል ሲያጨበጭብ ሰማይ
መጠለያዬ ልብሴ እንጀራዬ ያ ነው
ነፍሴ ትጠግባለች በክብር በግርማው ።

በእምነት እኖራለሁ ።

ኢየሱስ ለእኔ

<u>ኢየሱስ ለእኔ</u> (2)
ከወርቅ ከዕንቁ ይበልጥብኛል
ይህን አምናለሁ አይቼዋለሁ
ኢየሱስ ለእኔ የበላይ ነው ።

1. በሥጋ አስቤ ዛሬ ብመካ
ያለ ኢየሱስ ነው የማያረካ
ይህን መርምሬ በቅርብ ሳየው
ኢየሱስ ለእኔ የበላይ ነው ።

ኢየሱስ ለእኔ . . .

2. ዋስትና የለው የዓለም ኑሮ
እንዴ ደስታ ወዲያው እሮሮ
ስንቶች ተሞኙ በከንቱ ታምነው
የኢየሱስን ፍቅር ችላ ብለው ።

ኢየሱስ ለእኔ . . .

3. ብር ወርቅ ወይ እንቁ አላተረፍኩም
ጌታን አምኜ ከተከተልኩኝ
ግን ዘለዓለዓለማዊ ሕይወት አገኘሁ
ይህን ተስፋ አድርጌ ቆሜያለሁኝ ።

ኢየሱስ ለእኔ . . .

አቤንኤዘር

አቤንኤዘር የእግዚአብሔር እርዳታ
አቤንኤዘር ፈጥኖ ደርሶልናል
ከፊታችን ላለው ምንም ነገር
ትላንት ያደረገው ለዛሬ እምነት ሆኖልናል ።

1. ነገ ምን ይሆን በሚል ስጋት
ከሚያደናቅፍ ከእንቅፋት
ወድቀን ሳንጠፋ ሳንበተን
ጌታ እረኛችን ደረሰልን ።

አቤንኤዘር . . .

2. ከከሳሻችን የተነሣ
ነፍሳችን አየች ጭንቅ አበሳ
ያ ጠላታችን ያሸበረን
የራሱ ወጥመድ ይዞት አየን ።

አቤንኤዘር . . .

3. የማይገፋ የመሰለንን
ያንን ታላቁን ተራራውን
ደልዳላ ሜዳ ካደረገው
አንጨነቅም ስለነገው ።

አቤንኤዘር . . .

4. ጠውልገን ኖረን ፍጹም ዝለን
ዛሬ ግን መንፈስ አበረታን
ከእንግዲህ ወዲያ በጌታችን
ከድል ወደ ድል እንሮጣለን ።

አቤንኤዘር . . .

ዞር ብዬ ሳየው

1. አጭር ጊዜ አይደለም ለረጅም ዘመናት
በድካም በትግል ለአያሌ ዓመታት
በመውደቅ መነሣት በውጊያ በጥቃት
እንደማያልፍ <u>የለም አለፈ ያ እሳት</u> (3)

ዞር ብዬ ሳየው ያሳለፍኩትን
አባጣ ጐርባጣ ጉድጓድ ገደሉን
ማመን ይሣነኛል ኃይልን ከየት አገኘሁ
ለካስ ኤልሻዳዩ ጠብቆኝ ቆሜያለሁ
ስሙን አከብራለሁ ።

2. መራራ አይታኘክ የመከራ እንጀራ
የብቸኝነት ቤት እኔው ከእኔ ጋራ
እንቅልፌን አጥቼ ብዙ ሌሊት አልፏል
ዛሬ ግን ታሪክ ነው <u>ተረት ነው ይወራል ።</u> (3)

ዞር ብዬ . . .

3. የሕይወቴ ማብቂያ ዛሬ ነው ያልኩበት
ዓይኖቼን ጨፍኜ ሞትን ያሰብኩበት
ቀውጢው ሰዓት አልፎ ማየቴ ደንቆኛል
ለካስ ጌታ ወዶኝ እጅ እግሬን ጠብቋል ። (3)

ዞር ብዬ . . .

4. የአብርሃም አምላክ በክንፉ ሸሸገኝ
ለካ መጐዳቴን ተጐሳቁዬ አየኝ
ያን ሁሉ ችካራ ያን ሁሉ ጐርባጣ
ጌታ ብርታት ሆነኝ ችየው እንድወጣ ። (3)

ዞር ብዬ . . .

ከአምላካቸው በቀር

ከአምላካቸው በቀር ማንንም እንዳያመልኩ
ለወርቁም ምስል እንዳይሰግዱ እንዳይንበረከኩ
ሰውነታቸውን አሳልፈው የሰጡትን
ወዳጆቹን ያዳነ በእርሱ የታመኑትን
የሲድራቅ የሚሳቅ የአብድናጎም አምላክ
ለዘለዓለም ይባረክ ።

1. እንደእርሱ የሚያድን ሌላ አምላክ የለምና
ከእቶኑ እሳት ሊያድናቸው ችሏልና
ማዳን የእርሱ ነውና ። (2)

ከአምላካቸው በቀር . . .

2. ጌታ ተናገረ እኔም ይኸንን ብቻ ሰማሁ
ኃይል የእግዚአብሔር መሆኑን ተገነዘብሁ
እሳቱን ሲያጠፋ አየሁ ። (2)

ከአምላካቸው በቀር . . .

3. ሰውነታችሁን ብትሰጡ ሳትሰስቱ
እግዚአብሔር ይሠራል አይፋጅም ከቶ እሳቱ
ስሙን አስከብሩ በርቱ ። (2)

ከአምላካቸው በቀር . . .

ነገር ሁሉ ባይሳካ

ነገር ሁሉ ባይሳካ ለጌታ መንገር ይሻላል
ተከፍቶ ተስፋ ቆርጦ መቼ ይዘለቃል ።

1. የእንባዬ ክብደት ይሰማሀ ሕዋሀንም ሰንጥቆ
የልቤ ጭንቀት ይታይሀ ዙፋንሀንም ዘልቆ
ግለቱ ይበጃል እንጂ ጌታዬን መለመኑ
በትንሹ ተስፋ ቆርጦ መቼ ይቻላል ለመሆኑ ።

ነገር ሁሉ . . .

2. ነገር ሁሉ ግራ ነው አይዙት አይጨብጡት
ልብ እንዳሰበው አይሆን ቢያወጡት ቢያወርዱት
እግዚአብሔርን ለሚወዱ ነገር ሁሉ ለበጐ
ብሉ መጠበቅ መልካም መንፈስን ረጋ አድርጐ ።

ነገር ሁሉ . . .

3. የያዙት ከእጅ ሲወድቅ የጠበቁትም ሲከዳ
ኀዘን ጭንቀት ሲከብብ ሲተክዝ የሕይወት ጓዳ
ፈቃድሀ ይሙላ ማለት ሁሉን መጣል ከመስቀሉ
እርሱ መልስ ነው ኢየሱስ ለጭንቀትሀ ሁሉ ።

ነገር ሁሉ . . .

4. እምነትሀ እስኪናጋ በረከትሀ እስኪረሳ
የሕይወት ውጣ ውረድ መፈጠር ሲሆን አበሳ
ድፍንፍን ባለ ጨለማ መውጫ ቀዳዳ ሲጠፋ
የት ይገኛል መጠጊያ ካለ ኢየሱስ ተስፋ ።

ነገር ሁሉ . . .

ግን አንድ ነገር አውቃለሁ

1 በምን ወደድከኝ አልልህም
በእርግጥ ወደኸኛል
የፍቅርህ መገለጫ ይኼ ነው ለኔ ተወግተሃል
አንተ ለኔ የሆንከውን ያህል እኔ ላንተ አልሆንኩም
ምን ያህል እንደሆን አላውቅም ለከቼ አላየሁም ።

ግን አንድ ነገር አውቃለሁ
ስለወደድከኝ እወድሃለሁ ።

2. ከእርግማን ስለዋጀኸኝ ሞተህ ሸክሜን ስለወሰድክ
በመንፈስ ቅዱስ ስለሞላኸኝ ነፍሴን ስለባረክ
ጸጋን አብዝተህ ስለሰጠኸኝ ከቶም ስላልተውከኝ
ምን ያህል እንደሆን አላውቅም ለከቼ አላየሁም ።

ግን አንድ ነገር . . .

3. ደስ ላሰኝህ እቀናለሁ በሕይወቴ ላከብርህ
ሆኖም ከቶ አልጠቀምኩህም ሁሌ ሳሳዝንህ
ይልቅ ብዙ አድክሜሃለሁ የትም እየቀረሁኝ
ብዙ ስላላፈራሁ ኢየሱስ ከፍቶኝ አለቅሳለሁኝ ።

ግን አንድ ነገር . . .

በእውነት አሳድገን በፍቅር

በእውነት አሳድገን ጌታ ሆይ በፍቅር
በከንቱ መታበያችን ይቅር
በእውነት አሳድገን ጌታ ሆይ በፍቅር ።

1. በክርስትናችን ዕድሜ ቆጥረን
በልምምዳችን ኮርተን
በትህትና መማሩ ቀረና
እድገታችን ቆመ ታበይንና ።

በእውነት አሳድገን . . .

2. ባስተያየታችን ጠቢባን ነን
ትንሽን እናጠራለን
ራሳችንን ማንጻት ሳይቻለን
የሌላውን ጉድፍ እናያለን ።

በእውነት አሳድገን . . .

3. ማደጋችንን እዩልን እያልን
በከንቱም እየታበይን
አንተንም በዚህ እያሳዘንን
ሳይታወቀን ስንቶችን ጎዳን ።

በእውነት አሳድገን . . .

4. እንደ ሕጻናት የዋሆች አርገን
ንጹህ ልብን መልስልን
ዓይናችንን እየገለጥህ
አንተው አመላልሰን በብርሃንህ ።

በእውነት አሳድገን . . .

5. በቃል በስርአት ሙታን ሆነን
በፍቅር እየታነፅን
በእውነት እንደግ ወደ ኢየሱስ
እየታበይን እንደምን እንነስ

በእውነት አሳድገን . . .

ፍቅሩ የማያቋርጥ ጅረት ነው

1. ፍቅርን ሳስባት ጌታ ኢየሱስን አልማለሁ
መላ አካላቷን አየዋለሁ
ትርጉሟን በውስጤ እረዳለሁ
ለፍቅር ትርጉም
እንደ ኢየሱስ የለም

ፍቅሩ የማያቋርጥ ጅረት ነው አጥንትን ዘልቆ የሚሰማ
ልዩ ጣዕምም የሞላው የብርታት ቅኔ የሚያሰማ ።

2. ነፍስን ከሙስጠት የበለጠ መውደድ የለም
ይህቺ ናትና ፍቅርም
ብርሃን የሆነች ለዚህ ዓለም
ፍቅርን ለማየት
ኢየሱስን መመልከት ።

ፍቅሩ የማያቋርጥ . . .

3. በወልድ ልብ ውስጥ ያለች ፍቅር ነች ፍጹሚቱ
የገለጸልን በሞቱ
ያልተለወጠች በእርዛቱ
ፍቅርን ለመቅመስ
በኢየሱስ መታደስ ።

ፍቅሩ የማያቋርጥ . . .

ኅብረት አለን

ኅብረት አለን እኛ በጌታ
በአምላካችን ቀረ መኖር ለየብቻ
ስሙ ይክበር የኛ ጌታ ።

1. ከምሥራቅ ከምዕራብ ከደቡብ ከሰሜን
ከወገን ከቋንቋም ከነገድ ሰብስቦን
ልጁን በመስዋት አምላክ አስታርቆን
ኅብረትን ሰጥቶናል ፍቅሩን አሳይቶን ።

ኅብረት አለን . . .

2. ማንም ያልሰጠንን አንድነት ሰጥቶናል
ከጥላቻ ሕመም ቁስሉ ፈውሶናል
በመንፈሱ በኩል ፍቅር ፈሶልናል
በኢየሱስ ብቻ ኅብረት አግኝተናል ።

ኅብረት አለን . . .

3. የሕይወትን እንጀራ በአንድ እንቆርሳለን
ከምንጩ ጠጥተን ሁሌ እንረካለን
ስለመስቀሉም ቃል ሕይወታችን ፈሶ
ለመሄድ ቆርጠናል ያ ቀናችን ደርሶ ።

ኅብረት አለን . . .

ይኼ ሁሉ ሕዝብ

1. ኃጢአትን ሊሽር በዓለም ተገለጠ
አይሁድን ብቻ ሳይሆን ዓለምን መረጠ
በሞት በትንሣኤው ይህን ሕዝብ አፈራ
እጅግ ደስ ይለናል በጌታችን ሥራ ።

ይኼ ሁሉ ሕዝብ ዛሬ የምናየው
የኢየሱስ የደሙ ፍሬ ነው
በመስቀሉ ሞት ይህንን አፈራ
የተለያየውን በስሙ ኃይል ጠራ ።

2. እዚህ ቆሞ ብሎ ቃሉን የሚሰማው
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሐሴት የሚያደርገው
በቀራንዮ መስቀል በደሙ የተገዛው
የኢየሱስ ሕዝብ ነው በዝቶ የሚታየው ።

ይኼ ሁሉ ሕዝብ . . .

3. በብርታት አይደለም ወይም በግዴታ
በኃይልም አልሆነም ወይም በድንፋታ
በመስቀል ተጋድሎ ዘንዶውን እረግጠ
ይህን ሕዝብ አፈራ ሞትን ድል አድርጎ ።

ይኼ ሁሉ ሕዝብ . . .

4. በሽንገላ ብዛት በገንዘብ ተታሎ
ሀብትን ታገኛለህ አይደለም ተብሎ
ነገር ግን ፍቅሩን ስለቀመሰው
ተቀምጦ ይታያል ሲያመሰግነው ።

ይኼ ሁሉ ሕዝብ . . .

ሕዝብህን አበዛህ

ሕዝብህን አበዛህ ሕዝብህን አበዛህ
ያገሪቱንም ወሰን አስፋህ
የማዳን እጅህን ለእኛ ዘረጋህ ።

1. ዓላማ ይዞ የተሰለፈ የሚያስፈራ ያንተ ሠራዊት
ጠላትን ሁሉ እያሸነፈ
ባንተ መሪነት ቀንና ሌሊት
ባሕር ተሻግሮ በምድረ በዳ ጊንጡን ረጋግጦ
ጥቂቱ ሕዝብህ ካንተ ጋር ወጥቶ
ርስቱን ጨበጠ ከብዙ በልጦ ።

ሕዝብህን አበዛህ . . .

2. የሰናፍጭዋን ቅንጣት ቢዘራት
ጌታ በምድር እንድትበዛ
ያ ጉልበተኛ መጥቶ ረገጣት
የማትበቅል መስላው ፈዛዛ
ግን አልተሳካም አምልጣው ወጣች ሄደች አደገች
ጌታ ያመስገን ድንበርዋ ሰፋ
ለደካከሙት መጠለያ ሆነች ።

ሕዝብህን አበዛህ . . .

3. ሃሌሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ
እያሸነፈ ዘለዓለም ነዋሪ
እንደአምላካችን ያለ ታዳጊ
ከቶ የት አለ ተወዳዳሪ
ጩኸትን ሰምቶ ምስኪን ድሆችን ዘይት የሚቀባ
ባደባባዩ በቤቱ ተክሎ የሚያለመልም እንደዘንባባ ።

ሕዝብህን አበዛህ . . .

ና የጥንቱ ኢየሱስ

ና የጥንቱ ኢየሱስ ና የናዝሬቱ ኢየሱስ
<u>ተመላለስ በዚህ ጉባኤ ።</u> (4)

1. ስምህን እንጠራለን ከሁለት ሰዎች በልጠን
በነዛ በእጆችህ መዳሰስን ፈልገን
አሁን በዚህን ሰዓት ተመላለስ እንደህ
ክብርህም ቤቱን ይሙላው ይገለጽልን ክንድህ ።

ና የጥንቱ ኢየሱስ . . .

2. ሁለት ሰዎችን እንጂ ሁለት ሺህን አላልክም
ተስማምተው ከቀረቡ አልገኝም አትልም
አሁን እኛም ከሁለት በልጠን እንታያለን
ዳግም ተጨመርና ባርከን እንልሃለን ።

ና የጥንቱ ኢየሱስ . . .

3. ከፍ ባለው ዙፋንህ ተቀምጠህ ያለኸው
የልብስህ ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶ የተረፈው
የሠራዊት እግዚአብሔር ስምህን እንጠራለን
ግርማህም በኃይል ሲያበራ ልናይ እንሻለን ።

ና የጥንቱ ኢየሱስ . . .

4. ግቢውን ተቆጣጠር ጉባኤውንም ግዛ
በመኻከላችንም መንፈስ ቅዱስህ ይሥራ
በዘርፋፋው ልብስህም ጌታችን ተመላለስ
የእያንዳንዳችንንም ጥያቄያችንን መልስ ።

ና የጥንቱ ኢየሱስ . . .

ወደ እግዚአብሔር ቤት

ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ሲሉኝ ደስ አለኝ
ቃሉን እንስማ እንሂድ ሲሉኝ ደስ አለኝ
ናና እንጸልይ እንሂድ ሲሉኝ ደስ አለኝ
ናና እንዘምር እንሂድ ሲሉኝ ደስ አለኝ
ደስ አለኝ ።

1. ይባርከኛል አውቃለሁ
ያስተምረኛል አምናለሁ
ሕይወቴን ለርሱ እሰጣለሁ ። (2)

ወደ እግዚአብሔር . . .

2. ቃሉን ቢሰጠኝ እበላለሁ
መንፈሱን ቢያፈስ እጠጣለሁ
እንዲለውጠኝ እሻለሁ ። (2)

ወደ እግዚአብሔር . . .

3. ሸክሜን ሁሉ አወርዳለሁ
ኃጢአቴን እናዘዛለሁ
በእውነት ታድሼ እሄዳለሁ ። (2)

ወደ እግዚአብሔር . . .

ኢየሱስ የቀራንዮ ኢየሱስ

ኢየሱስ የቀራንዮ ኢየሱስ
ኢየሱስ የጉልጉታው ኢየሱስ
በዚህ ጊዜ በዚህ ቦታ እንፈልግሃለን

1. ማየት መስቀልህን
ማሰብ ችንካርህን
ተሳል ከፊታችን
ሞትህ ትዝ ይበለን ።

ኢየሱስ . . .

2. ጉልበታችን ዝሏል
ኃይልም ከእኛ ከድቷል
እንደ ሳምሶን ሁነን
ጠላት አይሳቅብን ።

ኢየሱስ . . .

3. ፈውስን ፈልገናል
መዳሰስ ሽተናል
እጆችህን ጫንብን
ኃይልህ እኛን ይሙላን ።

ኢየሱስ . . .

4. ኢየሱስ አንዴ ና
ልመናን ስማና
እይ ጉድለታችንን
መለወጥ ለውጠን ።

ኢየሱስ . . .

ደግመህ ደግመህ ባርከን

1. ደግመህ ደግመህ ባርከን አሁንም (2)
እረከተናል ጠግበናል እንዴም (2)
ጽዮን ስንደርስ ብቻ ነው እርካታችን (2)
እስከዚያው ግን መግበን አባታችን ።

2. ደግመህ ደግመህ መግበን ቃልህን (2)
በኛም ዘመን ግለጸው ኃይልህን (2)
እንመልከት ስትሠራ በፊታችን (2)
ኃይሉ ይቅለጥ ይሰበር ጠላታችን ።

3. ደግመህ ደግመህ አሰማን ድምጽህን (2)
ፍጻሜያችን ያማረ እንዲሆን (2)
ከእውነትህ እንዳንስት በጉዟችን (2)
ሕያው ቃልህ ይሁነን ምርኩዛችን

4. ደግመህ ደግመህ አሳየን ክብርህን (2)
ከእሳት ከውኃ አድነን ሕዝብህን (2)
ከእኛ ጋር እንዳለህ በዓለም ይታይ
አንተም ክበር ከፍ በል በምድር ላይ ።(2)

ተነሥ ተነሥ

ተነሥ (4) የእግዚአብሔር ክንድ እንደ ጥንቱ ተነሥ
ኃይልህንም ልበስ እንደ ጥንቱ ተነሥ ።

ሕዝብህ በምድረ ግብጽ ኑሮ ቢመራቸው
ከበግ ጥበቃ ላይ ሙሴን የጠራኸው
የዘመናት ንጉሥ እግዚአብሔር ሆይ
ዘንዶውን የወጋህ አንተ አይደለህም ወይ ?

ተነሥ ተነሥ . . .

የሳተም ይመለስ የዛለም ይበርታ
የኃጢአት ምርኮኛ ከእስራት ይፈታ
ክንድህን ስንጠብቅ በናፍቆት ዝለናል
እስቲ አንድ ጊዜ ጐብኘን ተጠምተናል ።

ተነሥ ተነሥ . . .

ያለፉት ባሮችህ አስከብረውሃል
ኃይልህ ከላይ ሲወርድ ከአንበሳ ገጥመዋል
አንካሶች ሮጠዋል ጋኔኖች ወድቀዋል
ጊዜ አይለውጥህም እኛም አይተንሃል ።

ተነሥ ተነሥ . . .

ያንን ታላቅ ክብር

ያንን ታላቅ ክብር ናፍቀናልና
አባክህ እግዚአብሔር ዘንበል በል
እንደ ቀድሞ ዘመን በክብር ሙላ ቤትህን

1. በውጭም በውስጥም አንተን ያሉ
እረ ጌታ ብዙ ብዙ አሉ
አባክህ እግዚአብሔር ተለመነን
በቀድሞ ክብርህ ከአርያም አስታውሰን ።

ያንን ታላቅ ክብር . . .

2. ዞር ብለን የጥንቱን ስናስተውል
ከቃልህ ስናነብ የሆነውን
እንመኛለን ዛሬም በአንድ ሆነን
አባክህ እግዚአብሔር ክብርህን አሳየን ።

ያንን ታላቅ ክብር . . .

3. አምላካችን ዛሬም ናፍቆታችን
የየደቂቃዋ ጸሎታችን
ያ ታላቁ ክብር ቤትህን ሞልቶት
ሃሌሉያ ማለት በታላቅ በረከት ።

ያንን ታላቅ ክብር . . . .

4. ዛሬም አምላካችን አንተ ያው ነህ
ክብርህን ልታሳየን ትችላለህ
እንደ ሰባ እንቦሳ አስፈንድቀን
ሃሌሉያ እንበል ክብርህን እያየን ።

ያንን ታላቅ ክብር . . .

መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስ (2)
ለኛ የሚያቅተን ላንተ ግን ይቻላል
በዘመናት ሁሉ ላንተ ምን ተስኗል
ብዙ ሰባራ አለን መጠገን የሚያሻን
ብዙ ደንዳና አለን መሰበር የሚያሻን
ይኸው በፊትህ ነን ና እባክህ ጐብኘን ።

1. ከስም ሁሉ በላይ በሆነው ታላቅ ስም
በሰማይ በምድር ሁሉን በሚችል ስም
እንለምንሃለን ዛሬም እንደገና
መንፈስ ቅዱስ አልፈህ ና ሥራህን ሥራ ።

መንፈስ ቅዱስ . . .

2. በጨለማ ላለው ብርሃንህ ይብራለት
በደንዳናውም ላይ በትርህን አንሣበት
በግልጽ ይታይ ሥራህ ሲያበጅ ሲያፈራርስ
እንደ ቀድሞ ዘመን ዘመናችንን አድስ ።

መንፈስ ቅዱስ . . .

3. ስንት የታሠረ አለ የኃጢአት ቁራኛ
ቁስሉን በገል የሚያክ በደዌ የተኛ
አንተን ብሎ መጥቷል ሕዝብህ ፈውስን ሽቶ
ማዳን እንደምትችል ብርታትህን አይቶ ።

መንፈስ ቅዱስ . . .

4. በዘመናት ሁሉ ላንተ ምን ተስኖሃል
አልታዘዝ ብሎ ማን አስቸግሮሃል
ስብራትን ፈውስ ኀዘንተኛን ገላግል
ልትሠራ ብትወድስ ሁሉም ይቻልሃል ።

መንፈስ ቅዱስ . . .

ከዚህም የሚበልጥ

1. ጌታ በመንፈሱ በቃሉ መርምሮ
ሥራችንን ሁሉ ቢነግረን ዘርዝሮ
በእውቀቱ ተደንቀን በኑሮአችን አፍረን
ንስሐ ገብተናል ይቅር በለን ብለን ።

ከዚህም የሚበልጥ
የጌታ ኃይል ሲገለጥ
እናያለን ገና የክብሩን ደመና
ምድር ስትሞላ በጌታ ምስጋና ።

2. ኃጢአታችንን በደሙ አነጻው
የኛ ጌታ ኢየሱስ ምህረቱ ብዙ ነው
ርኩስ መናፍስትን በኃይሉ ያስወጣል
በወንጌሉ ሥልጣን መንግሥቱን ያሰፋል ።

ከዚህም የሚበልጥ . . .

3. ጌታ ሆይ እያለ ለሚቃትተው
ማዳኑ ሊመጣ ጽድቁ ሊገለጥ ነው
የእግዚአብሔርን ምሕረት ለሁሉ አብስሩ
የበረከት ዝናብ ይኸው ዉሽንፍሩ ።

ከዚህም የሚበልጥ . . .

4. ረሃብተኛ ሲመገብ ልዑል ቃሉን ሲሰጥ
በጸድቃን እልልታ ምድር ስትናወጥ
በምስጋና ዜማ በደስታ ዝማሬ
በታላቁ መከር የአገልግሎት ፍሬ ።

ከዚህም የሚበልጥ . . .

እዚህ ነን

እዚህ ነን እዚህ ነን
አንተን እንጠብቃለን
እዚህ ነን (2) እሳት እንጠብቃለን ፡፡

1. ተስፋ እንደ ገባህልን
እሳት ልታወርድልን
በዚህ ቆየ እንዳልከን
ጌታ እንጠብቅሃለን ፡፡

እዚህ ነን . . .

2. ቃልህ እያለ በእጃችን
መውጣት ስላልቻልን ከቤታችን
ሕይወት ተጠማን እያሉ
ብዙ ነፍሳት በግዞት አሉ ፡፡

እዚህ ነን . . .

3. እንዳንሆን የነፍስ ባለዕዳ
ለተጨነቁ እንድንረዳ
አውጣን ከፍርሃት ጓዳ
ወደ ሰማሪያ ወደ ይሁዳ ፡፡

እዚህ ነን (2) አንተን እንጠብቃለን
በኢየሩሳሌም ሆነን
አንተን እንጠብቃለን ፡፡

4. ነበልባል የሚታየን
ሙላት የሚሆንልን
ጌታዬ መቼ ይሆን
የበዓለ ሃምሳው ያ ቀን ፡፡

እዚህ ነን . . .

5. መንፈስ ቅዱስ ሆይ ቶሎ ና
እጅግ ተጠምተናልና
እስከ መቼ እንቆይ
አሥር ቀን አልሞላም ወይ ?

እዚህ ነን . . .

የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ ተነሥ

1. ለእስራኤላውያን እሳት አምድ ሆንካቸው
በደመናም ጋርደህ ከከፉ አዳንካቸው
እናምናለን በኃይልህ በቃልህ
የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ ተነሥ ኃይልህ ይፍሰስ ።

የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ ተነሥ (3) ለእኛ
ከጥንት የነበረ ያ ታላቅ ግሩም ኃይል
ዛሬም ይንቀሳቀስ ለእኛ ።

2. በምድረ በዳ ቢራቡ መናን መግበህ ጠገቡ
ደግሞም እንዳይጠማቸው አስበህ ከአለት ውኃን አፈለቅህ
ልብሳቸው ነበርህ ጌጣቸው
ጉልበት መጠጊያ ኃይላቸው ።

የእግዚአብሔር ክንድ . . .

3. በሙሴ ውስጥ ሆነህ የሠራህ
የኤልያስ አምላክ ወዴት ነህ
አልረሳንም ከቶ ተስፋህን
እንደምትሰጠን ኃይልህን ።

የእግዚአብሔር ክንድ . . .

4. መንገዳቸው ተከቦ በባሕር
በጣም ተቸገሩ ለመሻገር
ሙሴ ወዳንተ ሲጮኽ ሲያለቅስ ሳለ
የኤርትራ ባሕር ተከፈለ ።

የእግዚአብሔር ክንድ . . .

5. ከዚያም ተሻገሩ በደስታ
አንተ ሆንካቸው መከታ
ማነው እንዳንተ ያለ ታላቅ ንጉሥ
እኛንም አትርሳን እግዚአብሔር ሆይ ተነሥ ።

የእግዚአብሔር ክንድ . . .

እንደ ቃልህ እንዳስተማርከን

1. ዛሬ ያስተማርከንን የገለጽከልንን
ማስተዋል እንድንችል ቅዱስ መንፈስ ይርዳን
ዓይናችንም ይብራ ይከፈት ልባችን
ለቅዱሱ ቃል መታዘዝ አስችለን ።

እንደ ቃልህ እንዳስተማርከን
መኖር እንድንችል ጸጋህ ይብዛልን ። (2)

2. ሰሚ ብቻ እንዳንሆን አድራጊም አድርገን
የሰማነውን ቃል በሥራ እንድናውል
ስለ ሰማነው ቃል እንዳይፈረድብን
ማድረግ እንድንችል ጸጋህን አብዛልን ።

እንደ ቃልህ . . .

3. ቃልህ ትርጉም ኖሮት ይሥራ በሕይወታችን
በተናገርከው ቃል ለውጥንም እናግኝ
ማስተዋል ስጠን ለምንሰማው
ቃልህን በሥራ እንድናውለው ።

እንደ ቃልህ . . .

4. ብዙ ተናግረሃል አስተምረኸናል
ለኔ ነው በማለት መቀበል ይገባል
ልብን ኩላሊትን የሚመረምረው
ቃልህ በሕይወታችን በሥራ እናውለው ።

እንደ ቃልህ . . .

እንደ ማርያም ልሁን

እንደ ማርያም ልሁን ልወቅህ ለይቼ
የከበረ ሽቶ በፊትህ አፍስሼ
ሰዎችን ሳልፈራ ይሉኝታ ሳይዘኝ
በፊትህ ቆሚያለሁ ልጇ ማርኩሽ (ህ) በለኝ ። (2)

1. የተደቆሰ ልብ ስጠኝ የደቀቀ
የሚቀረኝ አይኑር ካንተ የተደበቀ
ዝቅ ብዬ እግርህን በእንባዬ ላርሰው
ልስበረው ጠርሙሱን በፊትህ ላፍስሰው ፡ (2)

እንደ ማርያም ልሁን . . .

2. የተሰወረውን በሙሉ ጉድለቴን
በደምህ እጠበው አጥፋልኝ ኃጢአቴን
ሕግህን እንድማር ትእዛዝህን እንዳውቅ
እንደ ማርያም ሆኜ ካአፍህ ቃል ልጠብቅ ። (2)

እንደ ማርያም ልሁን . . .

3. ልቤ ረጋ ብሎ አርፌ በፊትህ
በመንፈስ ዓይን አንተን በቅርብ እያየሁህ
ቁጭ ብዬ ብማር በሕይወቴ አድጋለሁ
እንደማርያም ልሁን ይህን መርጫለሁ ። (2)

እንደ ማርያም ልሁን . . .

4. ሕግህ ለእግሬ መብራት ለልቤ ብርሃን ነው
ይህን ነው በሕይወቴ እኔ የምመኘው
እንደ ማርያም ሆኜ ከእግርህ ሥር ቁጭ ብዬ
እንድማር እሻለሁ አንተ እርዳኝ ጌታዬ ። (3)

እንደ ማርያም ልሁን . . .

እረኞች በድንገት

1. እረኞች በድንገት ታላቅ ብርሃን አዩ
የምስራች ሰሙ ተገልጦ ሰማዩ
የዚህ ሁሉ ደስታ ምንድነው መነሻው
ለካስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ተወልዶ ነው ።

እግዚአብሔር ይመስገን ታላቅ ዜና ሰማን
የዓለም መድኃኒት ጌታ መወለዱን
እግዚአብሔር ከእኛ ጋር አማኑኤል (3)

2. ሰብአ ሰገል መጡ በኮከብ ተመርተው
ለሕጻኑ ኢየሱስ ሊሰግዱለት ወደው
ይኼ ሁሉ ስግደት ከቶ ለምንድን ነው
የጌቶቹ ጌታ ኢየሱስ ተወልዶ ነው ።

እግዚአብሔር ይመስገን . . .

3. አንዱ ኮከብ መርቶት ሌላው በመላእክት
ተመርተው እየመጡ ሁሉም ሰገዱለት
ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን
ሰላምም በምድር ለሰው ሁሉ ይሁን ።

እግዚአብሔር ይመስገን . . .

4. ዛሬም በልባችሁ ጌታን ያላያችሁ
ዲዳዎች ደንቆሮች አንካሶች ሁላችሁ
ኑና ከኛ ጋራ ጌታን አመስግኑት
በሩቅም ያላችሁ ኑና ስገዱለት ።

እግዚአብሔር ይመስገን . . .

እሰይ እሰይ ጌታ ተወለደ

1. ነብያት በቅድሚያ የተነበዩለት
የሰማይ ሠራዊት ክብሩን ያወቁለት
ከአብ የተላከ የዓለም መድኅን
ጌታ ተወለደ ክብር ለርሱ ይሁን ።

እሰይ እሰይ ጌታ ተወለደ
እሰይ እሰይ መድህን ተወለደ
እሰይ እሰይ ጌታ ተወለደ ።

2. በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተጸነሰው
በከብቶች በረት ውስጥ የተወለደው
በሄሮድስ ሊገደል የተፈለገው
ክብር ለርሱ ይሁን አማኑኤል ነው ።

እሰይ እሰይ . . .

3. ከድሃዎች ይልቅ ሆኖ መጻተኛ
ዓለምን አዳነ ከኃጢአት ቁራኛ
ክብር ክብር ለርሱ በምድር በሰማይ
ለልጆቹ ብሎ ሰላየ ስቃይ ።

እሰይ እሰይ . . .

4. ከታላቁ ክብሩ ከዙፋኑ ወርዶ
በበረት ተኛልን ስለኛ ተዋርዶ
በእንስሳት ጋጣ ውስጥ የተኛው ስለእኛ
ችግሩ ሳይኖርበት ሆኖአል ችግረኛ ።

እሰይ እሰይ . . .

የምሥራቹ ቃል

1. ጌታህን አመስግን ክርስቲያን ተነሣ
ልብህን ከእጆችህ ጋር ወደአምላክህ አንሣ
ኢየሱስ ተወልዷል ምሥራች ተናገር
እግዚአብሔር አምላክህን አመስግን በመዝሙር ።

የምሥራቹ ቃል በምድር ተሰማ
በከብቶች በረት ውስጥ ቤተልሔም ከተማ
ምንም ጊዜው ቢረዝም ቢታይም እርቆ
ኢየሱስ ተወለደ ዘመኑን ጠብቆ ።

2. የአዋጅ ነጋሪ ድምጽ በምድር ሲያስተጋባ
የነብያት ትንቢት ፍጹም ሳይዛባ
ኢየሱስ ተወልዷል መዳን ለሰው ሆኖአል ።
እልል በል ተናገር የምሥራቹን ቃል ።

የምስራቹ ቃል . . .

3. የቀደመው አዳም ቢሞት በኃጢአቱ
አምላክ አልተወንም አልቀዐት ምሕረቱ
አማኑኤል ተወልዷል ምድር ታስተጋባ
አመስግን በአፍህ በእጆችህ ጭብጨባ ።

የምሥራቹ ቃል . . .

4. የጠላትን ምሽግ በሥልጣን ሰባሪ
የንጋት ኮከብ ነው ስሙን አስከባሪ
እመን ትድናለህ ኢየሱስ ተወልዷል
ከዚያም አልፎ ተርፎ ለበደልህ ሞቷል ።

የምሥራቹ ቃል . . .

ግሩም ድንቅ ነው

1. የሰማይ ክብርህን ትተህ ወርደሃል
ለኔ በበረት ውስጥ ጌታ ተወልደሃል ።

ግሩም ድንቅ ነው ያንተ ሥራ ። (4)

2. ከድንግል ተወልደህ እኛን ለማዳን
ትህትናን ለብሰህ ምሳሌ ሆንከን ።

ግሩም ድንቅ . . .

3. ከምሥራቅ የመጡ ሶስቱ ጠቢባን
በኮከብ ተመርተው ሰግደውልሃል ።

ግሩም ድንቅ . . .

4. ሰማያዊ ፍቅር አስገድዶህ
ንጉሥ ብትሆንም ለኔ ሞተሃል ።

ግሩም ድንቅ . . .

5. ከሁሉ የሚገርመኝ ስለኔ ብለህ
በረከሰው ልቤ ገብተህ መኖርህ ።

ግሩም ድንቅ . . .

አመጣጡ የንጉሥ ዘር ነው

አመጣጡ የንጉሥ ዘር ነው
ባሕሪው አምላካዊ ነው
ክብሩን ተወ ተዋረደ
ሊሆነን ቤዛ ኢየሱስ ተወለደ ። (2)

1. በአባቱ ጉያ ሲኖር ሳለ
ከእሴይ ዘር ንጉሥ ተባለ
የእኔ ኃጢአት መውደቂ ገዶት
ክብሩን ጣለ ተወልዶ በበረት ። (2)

አመጣጡ የንጉሥ ዘር ነው . . .

2. የቅዱስ ዘር ነው አመጣጡ
ቸር መሃሪ ነው በባሕሪው
በማስተዋል መንፈስ የተሞላ
የዝና ተክል የአሕዛብ ጥላ ። (2)

አመጣጡ የንጉሥ ዘር ነው . . .

3. እረኞች ሰምተው አበሰሩ
ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን እያሉ
ከዳዊት ከተማ ተወልዷልና
ሰላም በምድር ከአርያም ምስጋና ። (2)

አመጣጡ የንጉሥ ዘር ነው . . .

4. ሰብአ ሰገልም ሰገዱለት
ገጸ በረከት አመጡለት
ለኢየሱስ ክብር ወድቀው ሰገዱ
መላእክትም ለስሙ ዘመሩ ። (2)

አመጣጡ የንጉሥ ዘር ነው . . .

አማኑኤል

አማኑኤል አሜን አሜን (2)
እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ።

1. አቤቱ ላከልን ክብሩንም አሳየን
በሞት ጥላ መኻል ብርሃን አበራልን ።

አማኑኤል . . .

2. ከሰማይ ወረደ ከድንግል ተወለደ
ከሙታን ተነሣ ሁሉንም ድል ነሣ ።

አማኑኤል . . .

3. የበጉን ቃል ስሙ በእምነት ተቀበሉ
የመንፈስ ቅዱስን ክብር እንድትወርሱ ።

አማኑኤል . . . .

4. በአባቱ ቀኝ ያለው በመንፈስ ከኛ ጋር ነው
በቃል ይሟገታል ድሉን ያሳየናል።

አማኑኤል . . .

ደሙ እንደ ውኃ

ደሙ እንደ ውኃ (2) ጉረፈ
የጌታ ጀርባ በጅራፍ ተገረፈ
እግሩ እስኪነቃ ተራራውን ነጉደ
እስከ ሞት ድረስ ጌታ እኔን ወደደ ።

1. በዚያ በሌሊት ሲያለቅስ ሲያነባ አደረ
መድኃኒቱ በደም ላብ ተነከረ
ሁሉም እያለው ሆነ ምንም እንደሌለው
የእኔ ፍቅር እጅግ ድኃ አደረገው ።

ደሙ እንደ ውኃ . . .

2. ከብሩ ሳያንሰው ሆነ ለኔ ችግረኛ
ፍቅር አሞኘው እጅግ ወዶኛልና
ቃተተ ለኔ በመስቀል ላይ እንዳለ
የእኔ ጌታ ከሞት ጋራ ታገለ ።

ደሙ እንደ ውኃ . . .

3. ፍጹም ታገሰ መከራውን በሙሉ
እኔ እንድፈወስ በተወጋው ቁስሉ
ተንገላታ ያለ ልክ ጉስቆለ
ያንንም ሁሉ ፍቅር ነውና ቻለ ።

ደሙ እንደ ውኃ . . .

አልረሳውም ጌታ

አልረሳውም ጌታ ያን ሁሉ መከራ
ያደረግኽልኝን በዚያ የጣር ስፍራ ።(2)

1. ጐልጐታን ስትወጣ ያደረጉብህን
መስቀል አሸክመው የዘበቱብህን
የሾህ አክሊል ደፍተው ያላገጡብህን
አልረሳውም ጌታ ያን የደም ላብህን ።

አልረሳውም ጌታ . . .

2. አልረሳውም ጌታ ያንን ጥማትህን
በሰፍነግ የሞላ ሆምጣጤ ያጠጡህን
ከቶ አልዘነጋውም ያን ቅዱስ ጐንህን
ሲወጉህ ደምና ውኃ ያወጣውን ።

አልረሳውም ጌታ . . .

3. ስለኔ ብለህ ነው ጌታ የታረድከው
ልክ እንደ ወንበዴ በእንጨት ላይ የሞትከው
አንተን ያሰቀለህ የሰዎች ፍቅር ነው
ደምህን ያፈሰስከው ስለ በደሌ ነው ።

አልረሳውም ጌታ . . .

4. ይህን ሁሉ ጭንቀት ዘወትር አስታውሰኝ
በስቃይህ ኢየሱስ ሕይወትን እንዳገኝ
የጌቴሴማኒን ጸሎት አስተምረኝ
ስትመለስ ጌታ ተኝቼ እንዳልገኝ ።

አልረሳውም ጌታ . . .

ፍቅር ይዞት

1. ፍቅር ይዞት ይህ ቸር የፍቅር ጌታ
በበረት ውስጥ ስለኔ ተንገላታ
በፍግ መሃል ስለኔ ግልጿል በሴት
ፍጥረት ሁሉ ስለርሱ ያድርግ ሐሴት

ስብራት የሚያውቅ ይህ የሕማም ሰው
ውስጣዊ ልቤን እንዴት ዳሰሰው
ተንቆም ቢኖር በሰው ተጠልቶ
አልተመለሰም ሥራውን ከድቶ ።

2. እንደ ጠቦት በሸላች ፊት ዝም አለ
ሸክማችንን መድኃኒታችን ቻለ
አፉን ሳይከፍት በጠላቶች ሳይዘብት
ፍቅርን ለብሶ መስቀሉን አሸከሙት ።

ጐልጐታን ወጣ ሲድህ ሲወጥጥ
ምድርም ሲፍቀው ገላውን ሲላጥ
የኀዘን ቀን ነው ሆኖም የደስታ
እርሱ ተረግሞ እኛን ሲፈታ ።

3. ዓለም በሌት በታላቅ መዳን ነቃ
ኃይል ወጣና ከዓለም ንጉሥ ሲቃ
ነፍሱን ሰጠ ይህ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ
ከኃጢአት እኔን ፈጽሞ ሊያድን ።

በቀትር ሲጮኽ አባቱን አጥቶ
ጻድቃን ጣሰ ምድር ተከፍቶ
ሥጋውን ከፍሎ ጥልን ከሻረው
ለምን ይሸሻል ሰው ከፈጣሪው ።

አንድ ነገር በልቤ ሆነ

1. አንድ ነገር በልቤ ሆነ
ኢየሱስ ሲያድነኝ (2)
ሕይወቴ በፍቅሩ ጋለ
ክብር ክብር ለስሙ ።

2. አምላኬ በዚያ መስቀል ላይ
በቀራንዮ በቀራንዮ (2)
ለኔ መከራውን አየ
ደሙም እኔን አነጻኝ ።

3. ግንባርህ በሾህ ተበሳ
መራራም ጠጣህ (2)
ጐንህም በጦር ተወጋ
ስለኔ ኃጢአት ብለህ ።

4. የደም ላብም አጠለቀህ
በጸሎት ሜዳ (2)
አሕዛብም ቀለዱብህ
መቱህ ተፉብህ ጌታ ።

ተነሥቷል ጌታ ተነሥቷል

1. ሰይጣን ሲፎክር ብዙ ሲዝናና
ቀበርኩት ብሎ
ኢየሱስ ተነሥቷል መቃብሩንም በድል ፈንቅሎ
እልል እንበል ደስ ይበለን
የድል አምላክ ነው የምናመልከው
ኢየሱስ ጌታችን ።

ተነሥቷል ጌታ ተነሥቷል
ተነሥቷል ሞትን ድል ነሥቷል (2)

የምስራችን እናወራለን
ተነሥቷል እያልን ።

2. የሰይጣን አሳብ ምሽጉ ሁሉ በኢየሱስ ወድቋል
በድል በግርማው በታላቅነት ጌታ ተነሥቷል
እልል እንበል እንዘምር
ኢየሱስ ተነሥቷል ድል ተጐናጽፎ ተሞልቶ በክብር ።

ተነሥቷል ጌታ . . .

3. ሞቶ ተቀብሮ የቀረ ጌታ መች አለን እኛ
ኢየሱስ ነው ኃያል ሞትን የረታ የሁሉም ዳኛ
ስለዚህ እንንቃ በእርሱ እንረፍ
ኢየሱስ ዘግቶታል ለዘለዓለም የሞትን ደጃፍ ።

ተነሥቷል ጌታ . . .

ፈነቀለው ጌታ መቃብሩን

ፈነቀለው ጌታ መቃብሩን
ያንን ድንጋይ እትሙን
ሞት ድል ሆነ ታገደ
ለእግዚአብሔር ወልድ ሰገደ ።

1. ውጊያ ገጥሞ ጌታ ከሞት ጋራ
በዳገት ቁልቁለት በተራራ
ክንዱን አጠንክሮ ጥርሱን ነክሶ
ድል መታው ሲአልን ቅጥሩን ጥሶ ።

ፈነቀለው ጌታ . . .

2. መቃብር ሊገዛው ሞከረና
ተማረከ አቅቶት እንደ ገና
ውጊያው አከተመ በትንሣኤው
ተዘጋበት የሞት መግቢያው መውጫው ።

ፈነቀለው ጌታ . . .

3. እንግዲህ በሞቱ ከመሰልኩት
በትንሣኤው አሁን ተባበርኩት
አ ገሩም ነጻነት ለነፍሴ
የማያበቃ እረፍት ለመንፈሴ ።

ፈነቀለው ጌታ . . .

መቃብሩን ፈነቃቀለው

መቃብሩን ፈነቃቀለው ማኅተሙን ፈታ ሃሌሉያ
ሞትም አልረታውም ኢየሱስ የኛ ጌታ አሜን ።

1. ታላቅ እልልታ ሆነ
ኢየሱስ በዓለም ገነነ
ሰይጣን ዓላማው ከሸፈ
ኢየሱስ ድል መታ ሞትን አሸነፈ ። (2)

መቃብሩን . . .

2. ምድር መደነቅ ሞላው
ጭፍራም መንቀጥቀጥ ያዘው
ከሞት ተነሣ ጌታ
ሁሉን በኃይሉ በሥልጣኑ ረታ ። (2)

መቃብሩን . . .

3. በዓለም ታሪክ ያልታየው
ሁሉ አዲስ የሆነው
ምሥጢር ለሰዎች የሆነው
ሞትን የረታ ጌታችን ብቻ ነው ። (2)

መቃብሩን . . .

4. ሰይጣን ያቀደው እቅድ
ድንገት ቀረ ከመንገድ
የአሕዛብ እስራት ተፈታ
ኢየሱስ ሞትን በሞቱ ሲረታ ። (2)

መቃብሩን . . .

ተነሥቷል

ተነሥቷል (2) የመቃብር ደጃፍ ተከፍቷል
ድንጋዩም በሩቅ ተንከባሏል
ከፈኑ ብቻ ነው አስከሬኑ የታል
በእውነትም ኢየሱስ ድል ነሥቷል ።

1. ኢየሱስ ማሸነፉን ይስማ ኢየሩሳሌም
ይውጣ የምሥራቹ ከዓለም እስከ ዓለም
ይስማ እንጂ ጠላትም መርዶውን አልቅሶ
ጌታ እንደሁ ተነሥቷል አይሞት ተመልሶ ።

ተነሥቷል . . .

2. ይወገድ ድንጋዩ ጠባቂውም ይምጣ
ኢየሱስ ካቃተው ጌታ መውጫ ካጣ
የትኛው ጠባቂ ነው የከለከለው
ጌታ መቃብሩን ሲፈነቃቅለው ።

ተነሥቷል . . .

3. ይነገር ለዓለም ምሥራቹ ይሰማ
ሞትን አሸንፏል ጀግናው ኢየሱስማ
ይህ ሀሰት አይደለም ዘለዓለማዊ እውነት ነው
ይታይ የጌታችን መቃብር ባዶ ነው ።

ተነሥቷል . . .

4. ይኸ ነው እንግዲህ የጐልጐታው ምስጢር
ወንጌላችን ኢየሱስ ከሙታንም በኩር
ሙትን አናመልክም መቃብር የዋጠው
ያሸነፈን እንጂ ሞትን ድል የነሣው

ተነሥቷል . . .

የምድር ፍጥረታት ሕያዋን

የምድር ፍጥረታት ሕያዋን አራዊት ሁሉ በሙሉ
አንድ ቀን ይኼ አይቀርም የእግዚአብሔርን እጅ ያያሉ

1. ታላቁ ነገር ከፍ ያለው እንዳልነበረ ይሆናል
ለእኛ ግን መዳን በጸጋው በእግዚአብሔር ይሆንልናል ።

የምድር ፍጥረታት . . .

2. የሁሉም ሥራ ሲገለጽ እምነት ሲፈተን በእሳት
ይመረመራል ያን ጊዜ የፍጡር ሁሉ መሠረት ።

የምድር ፍጥረታት . . .

3. ተራራው ሲሸሽ ከፊቱ መታሰቢያውም ሲጠፋ
የሰው ልጅ ማንን ያገኛል ያዳነው ሆኖለት ተስፋ ።

የምድር ፍጥረታት . . .

4. ጌታችን ሲመጣ ከላይ ልጆቹን ሲወስድ በአየር
ዓለም መጠበብ ሲሞላት አድናቂ ሆና ስትቀር ።

የምድር ፍጥረታት . . .

5. ታማኝ ነው ጌታ በቃሉ አንድ እንኳ ከእርሱ አይጐድልም
ፍጥረታት ጌታን ያያሉ በክፉም ቢሆን በደግም ።

የምድር ፍጥረታት . . .

ይመለሳል

1. መለከት ንፋ በታላቅ ድምጽ
ኢየሱስ ይመለሳል
ደስ ይበላችሁ ዘምሩም
ኢየሱስ ይመለሳል ።

ይመለሳል ፣ ይመለሳል
ኢየሱስ ይመለሳል ።

2. ተራሮች ጩኹ ሜዳም አብር
ኢየሱስ ይመለሳል
ይገለጣል የታረደው በግ
ኢየሱስ ይመለሳል ።

ይመለሳል . . .

3. አውጅ ባሕር በታላቅ ቃል
ኢየሱስ ይመለሳል
ለባሕር ዳር ይነገራል
ኢየሱስ ይመለሳል ።

ይመለሳል . . .

4. ምድር ሲናወጥ ይታወቃል
ኢየሱስ ይመለሳል
አውሎ ነፋስ ይነግረናል
ኢየሱስ ይመለሳል ፣

ይመለሳል . . .

5. በሕዝብ መቆጣት ይታወቃል
ኢየሱስ ይመለሳል
ሕዝብ ይራወጣል እውቀት ይበዛል
ኢየሱስ ይመለሳል ።

ይመለሳል . . .

ልናርፍ ነው

ልናርፍ ነው ወንድም ልናርፍ ነው
ኢየሱስ ሊመጣ ሊወስደን ነው
ልናርፍ ነው እህት ልናርፍ ነው
ኢየሱስ ሊመጣ ሊወስደን ነው ።

1. መለከት ሊነፋ መላእክቱን ሊያዝ ነው
የልጆቹ ነገር አላስችል እያለው
ጌታችን ይመጣል ከጽዮን ተራራ
ልንሄድ ነው እኛም ልንኖር ከእርሱ ጋራ ።

ልናርፍ ነው . . .

2. መሯሯጥ መባከን ይህ ሁሉ ይቀራል
የሚያስፈልገንን ኢየሱስ አዘጋጅቷል
ዓይናችን ተከፍቶ ጌታን ልናየው ነው
እጆቹን ዘርግቶ እኛን ሊቀበል ነው ።

ልናርፍ ነው . . .

3. እንበርታ እንጽና እንባችንን እንጥረግ
ተስፋችን ሊመጣ ሊያሳርፈን ነው
ኢየሱስ ሊመጣ ነው ከመላእክቱ ጋራ
ልናርፍ ነው እኛም ከዚህ ዓለም መከራ ።

ልናርፍ ነው . . .

የድል ዘንባባ

የድል ዘንባባ ይዤ ስገባ
መንግሥተ ሰማይ በር ላይ
የታረደውን በግ እንዳይ አምናለሁ እገናኘዋለሁ ።

1. ልብሴ እንዳያድፍ እጠነቀቃለሁ
ቢያድፍም በደሙ አጥቤ አነፃለሁ
የመጨረሻው ደወል ሲመታ
በገዛ ስሜ ሲጠራኝ ጌታ
አየዋለሁ እገናኘዋለሁ ።

የድል ዘንባባ . . .

2. ከዓለም ርኩሰት ራሴን ጠብቄ
ጽድቅን ለብሼ በእውነት ታጥቄ
መልካሙን ገድል በእርሱ ተጋድዬ
ሁሉን በሚያስችል ሁሉንም ችዬ
አየዋለሁ እገናኘዋለሁ ።

የድል ዘንባባ . . .

3. ራዕይ ሲፈጸም ምኞት ሲሞላ
ከላይ አውርጄ ሸክሜን በሙላ
ከሕሊና ክስ ከነፍስ ወቀሳ
ተገላግዬ በድል ስነሣ
አየዋለሁ እገናኘዋለሁ ።

የድል ዘንባባ . . .

4. በነአብርሃም ጉባኤ መሃል
እዘምራለሁ እግሬም ይቆማል
በዚህ አይበቃም አገልግሎቴ
እቀጥላለሁ በሰማይ ቤቴ
አየዋለሁ እገናኘዋለሁ ።

የድል ዘንባባ . . .

5. የዚህ ዓለም ምኞት አይደልለኝም
የኃጢአት ጉርሻም አያጓጓኝም
የማጣው ቢኖር ቅርም አይለኝ
የማላጣው ኃብት በላይ ስላለኝ
አየዋለሁ እገናኘዋለሁ

የድል ዘንባባ . . .

አለኝ ወዳጅ

1. የዘለዓለም አምላክ ኃያል ጌታ
በክብር በሥልጣን የበረታ
አዳምን ከአባቱ ያስታረቀ
ፍቅር ታምራቱ የረቀቀ ።

አለኝ ወዳጅ ከንደ ብርቱ (2)
የሚያደርሰኝ ወደቤቱ ።
አለኝ ወዳጅ እሩቅ አገር
የሚመጣ በታላቅ ክብር
የኔ ሙሽራ ጌታ ኢየሱስ
የምጠብቀው የድል ንጉሥ ።

2. ክብሩን ትቶ ከላይ የወረደ
ኃጢአቴን ከላዩ ያስወገደ
ልጁ እንድሆን እንዲያው የመረጠኝ
ከጥፋት ጉዳና የመለሰኝ ።

አለኝ ወዳጅ ከንደ ብርቱ (2)
የሚያደርሰኝ ወደቤቱ።

አለኝ ወዳጅ . . .

3. እውነተኛ ወዳጅ የማይከዳ
በፍቅር ስለኔ የተጎዳ
በኃይልና በክብር የሚመጣው
ገናናው ኢየሱስ ድል አድራጊው ።

ለዘለዓለም ሰላም ደስታ (2)
ሲመለስ ነው የኔ ጌታ ።

አለኝ ወዳጅ . . .

4. እውነተኛ ወዳጅ አፍቃሪዬ
በዘመኔ ሁሉ እረኛዬ
በክብር ይመጣል አየዋለሁ
ቃሉ አይታበልም አምነዋለሁ ።

እንደ ሄደ ይመለሳል (2)
ወደቤቱ ይወስደኛል ።

አለኝ ወዳጅ . . .

ቀኑ ደርሷል

ቀኑ ደርሷል ሊነፋ መለከት
ሕዝብ ይጠራል ካለበት በፍጥነት
ተሰብስበን ልንቆም በጌታ ፊት ።

1. ታላቁ ቀን ቀርቧል ኃይሉ የሚያስፈራ
ምድር ልትናወጥ ሊሸሽን ተራራ
የነገሥታት ንጉሥ ሲገለጽ ከሰማይ
በምድር የቀሩት ይሉለታል ዋይ ዋይ ።

ቀኑ ደርሷል . . .

2. ልጆቹ ሲሄዱ በክብር ታጅበው
ጌታ ብርሃናቸው ሆኖ ሲመራቸው
ደስታ ነው ዘለዓለም የለም ጭንቀት መከራ
መዘመር ነው ሁልጊዜ ከጌታችን ጋራ ።

ቀኑ ደርሷል . . .

3. ፈጽሞ በመትጋት በጾም በጸሎት
ድል እንድናደርገው ዘንዶውን ጠላት
አሸናፊ ሆነን ስንሄድ በተራ
ለዘለዓለም እንኖራለን በጽዮን ተራራ ።

ቀኑ ደርሷል . . .

የአዲስ ኪዳን በግ

የአዲስ ኪዳን በግ ቅዱስ ካህን
የጽድቅ ንጉሥ የዓለም መድኅን
የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ
ቅዱስ ካህን አለን በላይ በሰማይ ።

1. ከብዶን የነበረው የሕግ ጭነት
ፍጥረትን ሲያስጨንቅ ስለ ኃጢአት
የሕዝብን ኃጢአት እንዴ ለማስቀረት
ኢየሱስ ሕይወቱን ሰጠ በመስቀል ስቅላት ።

የአዲስ ኪዳን . . .

2. የኃጢአት መጋረጃ እኛን የለየን
ኢየሱስ ተረተረው መሥዋዕት ሆኖልን
ቅድስተ ቅዱሳን የተሰፋው አገር
በርሱ ልንገባ ቻልን ወደ ሕይወት በር ።

የአዲስ ኪዳን . . .

3. የኮርማ ደም መሥዋዕት ለኛ አያስፈልገንም
እንዴ ተረጭተናል በክርስቶስ ኢየሱስ ደም
ቅዱስ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ
ነፍሱን ወዶ ሰጠ ሊሞት ስለኛ ።

የአዲስ ኪዳን . . .

በረከት ክብርም ጥበብም

በረከትና ክብርም ጥበብም
ባለጠግነት ኃይልም ብርታትም
በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው
ለነበረው ላለው ለሚመለሰው
ለታረደው በግ ምስጋና ይድረሰው ።(4)

1. መጽሐፉን ወሰዶ ማኅተሙን ፈቶ
ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅቶ
ለአምላክ መንግሥት ካህናት ሆነን
በበጉ ሥራ ተመስገንን ።

በረከትና ክብርም . . .

2. በሰማይ በምድር ከምድርም በታች
በእነርሱም ውስጥ ያለን ፍጥረታት
በዙፋኑ ፊት እንወድቃለን
ለበጉ ክብር እንዘምራለን ።

በረከትና ክብርም . . .

3. እልፍ አዕላፋት ብዙም መላእክት
ለታረደው በግ የሚሰግዱለት
እስከ ዘለዓለም ለሚኖር ጌታ
ቅኔን ሲቀኙ ጠዋትም ማታ ።

በረከትና ክብርም . . .

4. ከታላቅ መከራ የመጡ ናቸው
በበጉ ደምም አነጹ ልብሳቸው
በዙፋኑ ፊት ሌት ተቀን አሉ
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ።

በረከትና ክብርም . . .

እንጓዝ የእግዚአብሔር ልጆች

1. ዓለም ሳይፈጠር ለታቀደው ድግስ
ሊታረድ ወረደ ሕያው ታላቅ ንጉሥ
የአምላክ በግ ሆና ሞተ በመስቀሉ
አርነት ወጥተናል ሰዎች እልል በሉ ።

    እንጓዝ የእግዚአብሔር ልጆች
    ወደ ላይ ወደ ቅድስት አገር
    እንጓዝ የእግዚአብሔር ልጆች
    ለመኖር ከጌታ ኢየሱስ ጋር ።

2. ተሠርቷል ድግሱ በሕያው አምላክ ቤት
ድሃ ሃብታም ሳይል ሁሉ የሚበሉበት
ሁሉ እኩል ነው በዚያ የለውም ልዩነት
አብረን እንበላለን በሕያው አምላክ ቤት ።

    እንጓዝ . . .

3. ተነሡ እንገሥግሥ ወደ ቅድስት አገር
ከጌታ ኢየሱስ ጋር አብረን እንድንኖር
እንዘጋጅ አሁን ደርሶናል ጥሪው
በሩ ሳይዘጋ ሳይመጣ ክረምቱ ።

    እንጓዝ . . .

ይቅርታን ለማድረግ

1. ምህረትህ በኔ ላይ እንዲሆን እሻለሁ
እኔ ግን በቀልን ወዳጅ አድርጌአለሁ
ነፍሴ ተጐሳቁላ ፍጹም ሳያምርባት
ተኮንና እንዳትኖር ይቅርታን አስተምራት ።

ይቅርታን ለማድረግ ልቤ አልሆን እያለው
እግሬ የሚራመደው ሸካራ መንገድ ነው
የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ ድካሜን ታውቃለህ
ዳሰኝ እንደገና ትለውጠኛለህ ።

2. ወንድሜን ማክበሬ እጅግ ይረሳኛል
የተበደልኩትን መቁጠር ይጥመኛል
ምናለበት ዛሬም ልቤን ብትሰብረው
መከትከቻው ብረት መዶሻው በእጅህ ነው ።

ይቅርታን ለማድረግ . . .

3. እጄን ላንተ ሰጠሁ አንተ እንድታስተምረኝ
ለውጠኝ ጌታ ሆይ ይኸው በፊትህ ነኝ
የበደለኝን ሰው ይቅር ብዬ እንዳልፈው
በቀልን ሳላስብ በፍቅር እንዳቅፈው ።

ይቅርታን ለማድረግ . . .

ዓይኔን ከሰው እንስቻለሁ

ዓይኔን ከሰው አንሥቼአለሁ
አንተኑ ብቻ እጣራለሁ
ድል እስክትሰጠኝ እጠብቃለሁ
ሁሉም ከንቱ ከንቱ ከንቱ ነው
ካንተ ማግኘት ጥበብ ነው ። (2)

1. ግራ ቀኝም አልል ባይኖቼ
እወድቃለሁና ስልቼ
ለውድቀት ካልሆነ በስተቀር
ይቅርብኝ ሰው ሁሉም ነገር ።

ዓይኔን ከሰው . . .

2. ጌታ አለኝ ብያለሁኝና
በድፍረት ፎክሬአለሁና
ስጠራህ ከተፍ በል ረድኤት
ልኩራብህ እርዳኝ መድኃኒቴ ።

ዓይኔን ከሰው . . .

3. በጕነት ከቶ የት ይገኛል
ትልቁ ትንሹን ረግጦታል
ፍቅርስ ከወዴት ይጋዛል
ሰው ሰውን በጥርሱ አላምጦታል ።

ዓይኔን ከሰው . . .

4. ጕልጕታ እናቱ ላይ ሞቷል
ከጉድጓድ ሽቅብ አርገሃል
ቀና በል እያልሁ አንተን
ቸር ወዳጅ የሌለብህ እንከን ።

ዓይኔን ከሰው . . .

5. ግባ ባዳራሹ በልቢ
አንተ ነህ መኩሪያዬ ጥጋቢ
መስቀልህ ከፊቴ ተስሎ
አጽናኝ ከእንቅፋት ከልሎ

በአዲስ ዘመን አዲስ ነገር

በአዲስ ዘመን አዲስ ነገር
የእግዚአብሔር ስም እንዲከበር
እንጠብቃለን በናፍቆት
ያደርገዋል ምን ተስኖት ።

1. የተዘጋው ደጅ ተከፍቶ
የተጋዘው ነጻ ወጥቶ
እንሰማለን የድል ዜና
እንዘጋጅ ለምስጋና ።

በአዲስ ዘመን . . .

2. በፍጻሜው ሞት አይሆንም
ትንሣኤ አለ ለሙታንም
ያለቀሰን እንባ ሊያብስ
ከተፍ ይላል ጌታ ኢየሱስ ።

በአዲስ ዘመን . . .

3. ብቸኛ ሴት በዕንባ ያለች
መካኒቱም ትወልዳለች
የሣራ አምላክ የራሔልም
ጥቃት አይቶ ዝም አይልም ።

በአዲስ ዘመን . . .

4. ሰማያዊ ባላደራ
የወንጌል ዘር በእምነት ይዝራ
የበቀለው ሳይጨነግፍ
ይሰበሰባል በእጥፍ ።

በአዲስ ዘመን . . .

5. ውኃ ያጣ ዓሣ መሳይ
ወዝ የሌለው ደርቆ የሚታይ
ጌታ ይስጠው እንጂ ረጅም ዕድሜ
በእርሱ ያያል ልምላሜ ።

በአዲስ ዘመን . . .

በኢየሱስ ነው ነፃነቴ

በኢየሱስ ነው ነፃነቴ ዘላቂ ሕይወት መሸቴ
መዘመሬ መደሰቴ መጥላ ማደር በዕረፍቴ
የልቤ ሰላም እለና በነገር ሁሉ መርካቴ ። (2)

1. ከዚያ ከሞት መንደር ወጥቼ
ሰማያዊ ብርሃን አይቼ
ስሜ መጻፉን በሕይወት መዝገብ
ዘለዓለም ልኖር ያለ ገደብ ።

በኢየሱስ ነው ነፃነቴ . . .

2. ሁልጊዜ ደስ የምሰኝ እኔ
ተስፋ አድርጌ አይደለም ወርቄን
ኢየሱስ ስለ ወሰደው ሸክሜን
እያየሁኝ ነው ነፃነቴን ።

በኢየሱስ ነው . . .

3. ዞር ብዬ ሳየው የቀድሞውን
የሞትን አገር ጨለማውን
እውነትም ኢየሱስ ነፃነት ነው
ክብር ምስጋና የሚገባው ።

በኢየሱስ ነው . . .

4. ማዕበሉ አንዳንዴ ይነሣል
የልቤን ምሰሶ ይሰብራል
በዚህ ሁሉ ግን ደስ ይለኛል
የኢየሱስ መንፈስ ያፅናናኛል ።

በኢየሱስ ነው . . .

ኢየሱስ መልስ ነው

መልስ ነው ለመኖር በዓለም
"   " ለጥያቄህ ሁሉ
"   " እምነህ ከቀረብከው
ኢየሱስ መልስ ነው ።

1. ከየት እንደመጣህ መልስ ነው (3)
ወዴት እንደምትሄድ ጌታን መጠየቅ ነው
ለምን እንደምትኖር መልስ ነው (3)
ለሕይወትህ ትርጉም ኢየሱስ መልስ ነው ።

መልስ ነው . . .

2. መውጫ መግቢያ ጠፍቶህ መልስ ነው (3)
ትምክትህ ሲከዳህ ኢየሱስን እየው
ሕይወት ከንቱ ሲርቅ መልስ ነው (3)
ከኢየሱስ ጋር ታረቅ ኢየሱስ ፍቅር ነው ።

መልስ ነው . . .

3. ለእውቀት ለጥበብ መልስ ነው (3)
ለአእምሮህ ጥያቄ ኢየሱስ መልስ ነው
ፍቅር ትርጉም ሲያጣ መልስ ነው (3)
ጥላቻ ሲከብህ ኢየሱስን አስበው ።

መልስ ነው . . .

4. የአምልኮ መሠረት መልስ ነው (3)
የሰው ልጆች ሕይወት ኢየሱስ ትርጉም ነው
ለምስቅልቅል ዓለም መልስ ነው (3)
የሰላም መክፈቻ በኢየሱስ እጅ ነው ።

መልስ ነው . . .

አቤንኤዘር እስከ ዛሬ ድረስ

አቤንኤዘር አቤንኤዘር
እስከዛሬ ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል
እንደተለመደው ድንቅ አድርጐልናል
ባሁኑም ክፍሉ አሻግሮናል አቤንኤዘር

1. አናልፈውም ብለን ያለፍነው
የመከራው ዓይነት ብዙ ነው
መች ተሸንፈን እናውቃለን
ከአሸናፊዎች እንበልጣለን ፣
ይህ ያልፋል ብለን ያልገመትነው
የኛ ታሪካችን ብዙ ነው
እያለፍን በድል ጐዳና
አሸበረቅን በምስጋና ።
አቤንኤዘር . . .

2. በሐሩር ጊዜ የሆነው ጥላ
ከፍላጻው ሁሉ ከለላ
ልጆቹን ፊት ፊት እየመራ
ያርሰናል በጽዮን ተራራ
የድካሙ ጊዜ አብቅቶ
በብርታት ሕይወት ተተክቶ
በሽብሸባ ፊቱ ዘለናል
እስከ አሁን ድረስ አረድቶናል
አቤንኤዘር . . .

3. አሁን ከጌታ ጋር ያላችሁ
አቤንኤዘር የሆናችሁ
በፊቱ ቅረቡ በእልልታ
ስሙ ይባረክ የኛ ጌታ
ካመድ ከትቢያ ያነሣችሁ
በዚህ ጉባኤ ስንቶች ናችሁ ?
ታዲያ ለምን ነው ይህ ዝምታ ?
የታል ደስታችሁ ለዚህ ጌታ ?
አቤንኤዘር . . .

4. ይህ ያልፋል ብለን ያልገመትነው ፣ የኛ ታሪካችን ብዙ ነው
እያለፍን በድል ጐዳና ፣ አሸብረቅን በምስጋና
እንዲያ የሚከሰን ጠላታችን ፣ አሁን የታለ ከፊታችን
ኢየሱስ ስለነገሰ ፣ በጠንካራው ክንድ ተደቆሰ
አቤንኤዘር . . .

መሸሸጊያ ዋሻ

መሸሸጊያ ዋሻ መከታ ጋሻችን
ጦራችን አንተ ነህ ጠላትን መውጊያችን
አንተም ተዋጊ ነህ ስምህ እግዚአብሔር ነው
እንኮራብሃለን ደስታህ ኃይላችን ነህ ።

1. ከግብጽ ባርነት ከፈርኦን ግዛት
ብርሃን ጨልሞ ሞት በሰፈነበት
ልጆችህ ሲጮኹ ባርነት መሯቸው
አንተ ነህ ተዋግተህ ነጻ ያወጣሃቸው (2)

መሸሸጊያ ዋሻ . . .

2. በብዙ በጥቂት ማዳን የማይሳንህ
ፈጥነህም የምትደርስ ስምህን ለሚጠሩ
ጽኑ ጦር አንተ ነህ ጠላት የምትመታ
እንመካብሃለን የእኛ መከታ ።(2)

መሸሸጊያ ዋሻ . . .

3. ጠላትም ቢመጣ ጦሩን አስከትሎ
በሰረገላው ብዛት ጉልበታችን ዝሎ
ዓይናችንን ከፍተህ በእምነት ብናየው
ከጠላት የሚበልጥ ድብቅ ጦር ነው ያለው ።(2)

መሸሸጊያ ዋሻ . .

4. አቻምናን ስንፈራ ላምናው አድርሶናል
አምናንም ስንፈራ ዘንድሮ አድርሶናል
ዘንድሮን ስንፈራው ደረስን አሁን
ታዲያ ምን አሰጋን የወደፊቱን ። (2)

መሸሸጊያ ዋሻ . . .

እንደተቀበልኩት ምህረት

እንደተቀበልኩት ምህረት
እንደቸርነትህ ብዛት
እንዳገለግልህ እርዳኝ
ጌታ ሆይ ስጠኝ የመንፈስህን እሳት ።

1. እስራቴን ፈተህ ቀንበሬን ስብረሃል
ነፍሴ እንድታከብርህ ነጻ አውጥተኸኛል
ባርነት አበቃ ልጅ ነህ ብለኸኛል
በደምህ ቃል ኪዳን ያንተ አድርገኸኛል ።

እንደተቀበልኩት . . .

2. የተፍገመገመው ከውድቀት እንዲተርፍ
የደከመውን ሁሉ በቃል እንድደግፍ
አንቃኝ በግለጻ ቀስቅሰኝ ከእንቅልፍ
ታማኝ ሎሌ አድርገኝ ልብን የሚያሳርፍ ።

እንደተቀበልኩት ምህረት . . .

3. ጥበብ ለሌላቸው ለማያስተውሉ
ለተማሩም ሰዎች አውቀናል ለሚሉ
ወንጌሉን ልናገር እንዲድኑ አምነው
ለእነዚህ ሁሉ ዕዳዬ ትልቅ ነው ።

እንደተቀበልኩት . . .

4. ስንፍናዬን እርቅ በተገሳጽህ በትር
እንድተጋ እርዳኝ በጸጋህ ዙፋን ሥር
ኢየሱስ ያድናል ብዬ እንድመሰክር
ሕይወቴን ሙላልኝ በመስቀልህ ፍቅር ።

እንደተቀበልኩት ምህረት . . .

5. ወንጌል አይቆጠብ አይወሰን በከልል
እስከ ምድር ዳር ይሂድ ቃልህ ሳይከለከል
ለቅርቡ ለሩቁ ጽድቅህም ይታወጅ
ኢየሱስን አግኝቶ ፍጥረት እሰይ ይበል ።

እንደተቀበልኩት . . .

ክብር ለኢየሱስ ይሁን

1. በቀራንዮ መስቀል ላይ በደሙ የደቀቀው
ነፍሱን ስለ ኃጢአቴ መሥዋዕት ያደረገው
የሞትን ቀንበር ሰብሮ እኔኑ ሊያወጣ ነው
ማዳኑን ቀምሻለሁ ምናለ የሟመልሰው ።(2)

ክብር ለኢየሱስ ይሁን
አየን አሸናፊነቱን
ኃያል እንደርሱ የለም
ይንገስ ለዘለዓለም ።(2)

2. የተናቀ ደካማ ቢመስልም አመጣጡ
ከእሰይ ልጅ ከዳዊት ሥር የወጣ ቁጥቋጡ
ኢየሱስ አሸነፈ ፍሬው ምድርን ሸፈነ
የእግዚአብሔር ፈቃድ በእርሱ ተከናወነ ።(2)

ክብር ለኢየሱስ . . . .

3. በደሙ ኃይል ጸደቅን በስሙ ድል አገኘን
ማነው የሚቋቋመን ? ማንስ ነው የሚገታን ?
እንገሰግሳለን አሸናፊውን ይዘን
ወደ ቅድስቷ አገር በድል እንገባለን ።(2)

ክብር ለኢየሱስ ይሁን . . .

4. ክብር ምስጋና ይዘን በፊቱ እንቀርባለን
በዙፋኑ ላይ ላለው እንሰግድለታለን
ሁሉን የረታህ ጌታ ንገሥ እንለዋለን
አሜን ለዘላለም እርሱ ኃያል ነው አሜን ።(2)

ክብር ለኢየሱስ . . .

አንተው ትሻለኛለህ

1. ውዴ ከአልፍ ይሻላል
አንዱ ከሺህ ይበልጣል
ብዬ ተደፋሁ ደጅህ
ዳሰህ አቅናኝ በእጅህ ።
ተሟጋች ስለ ነፍሴ
ነህ ጠበቃዬ ዋሴ
የምትሞላ ጉድለቴን
መች ወደኸው ጥቃቴን ።

አንተው ትሻለኛለህ
የልቤን ቁስል ትፈውሳለህ
አንተው ትሻለኛለህ
ከአመድ ከትቢያ ታነሣኛለህ ።

2. ከመስቀል መስንቆዬን
ሳልገታው ተጋድሎዬን
አድሰህ አጽና ጉልበቴን
ልፈጽመው ትጋቴን ፣
ከሸንበቆ አልጠጋ
መፍትሔ መላ ፍለጋ
አንተኑ ጠብቃለሁ
ሥጋዬን ሰብቄዋለሁ ።

አንተው ትሻለኛለህ . . .

3. እንዳንተ ያለ የለም
ልዩ ነህ ለዘለዓለም
ግዛኝ ጌታ አሸንፈህ
በሀሳብህ ጠቅልለህ
በወጀብ ውስጥ በማዕበል

መንገድን ማስተካከል
በእሳትም ታልፋለህ
ጌታ ኢየሱስ ጌታ ነህ ።

አንተው ትሻለኛለህ . . .

4. ጉብዝና የዓለም ዝና
ውበት ቢሆን ቁንጅና
እንደ ጢስ በኖ ይጠፋል
ዕድሜም ሲሸሽ ይከዳል
ምንም ቢሆን እደጅህ
ካለም ተድላ ድንኳንህ
መልካም መሸሻ ጌታ
ለክፉ ቀን ለማታ ።

አንተው ትሻለኛለህ . . .